
ዓፄ ዮሐንስ



በዮሐንስ ገብረጻድቅ

መግቢያ

ይህን «ሌይ ሚዘራብል» የሚባለውን የቪክተር ሀዮጎ መጽሐፍ ለመተርጉም የተነሳሳሁት በውስጡ ብዙ የሕይወት ገጠመኞች ስላለበትና እነዚህም ገጠመኞች ትምህርት በመስጠት የሕይወት ምንነትን ያሳያሉ በሚል እምነት ነው። ከተነገረው ታሪክ ውስጥ ለማመን የሚከብዱ የሕይወት ገጠመኞች ቢኖሩም ሕይወት በአጋጣሚ የተሞላ ስለሆነ ገጠመኞቹ ከእውነት የራቁ ናቸው ብሎ ለመደምደም አይቻልም።

ፈረንሳዊው ቪክተር ሀዮጎ ይህን መጽሐፍ ከደረሰ በኋላ መጽሐፉን ለምን እንደ ጻፈው ሲጠየቅ «አምን፣ የሰው ልጅ ለግለሰቦች በጎ ፈቃድ እስከ ተተወ ድረስ በሰዎቹ ላይ የሚወሰነውን ውሳኔ ለማጥፋት እወጣለሁ፤ ባርነትን አወግዛለሁ፤ ድኅነትን አጠፋለሁ፤ ድንቁርናን ለማስወገድ አስተምራለሁ፤ የታመመን አክማለሁ፤ ጨለማ ተወግዶ ብርሃን እንዲሰፍን እጥራለሁ፤ ጥላቻን እጠላለሁ። እኔነቴ ይህ ሲሆን «ሌይ ሚዘራብልን» የጻፍኩበት ዋና ዓላማም ይኸው ነው» ሲል መልሷል። የተርጓሚውም እምነት ከዚህ የራቀ አይደለም።

ቪክተር ሀዮጎ ይህን መጽሐፍ ሲደርስ ዓላማው አንድን ታሪክ ጽፎ ለማቅረብ ብቻ አልነበረም። በተጓዳኝ ትክክለኛ ፍርድ ሰፍኖ የሰዎች እኩልነትና መብት መጠበቅ አስፈላጊነትም ለመግለጽ ነበር። የሰው ልጅ ሕይወት መዳኘት ያለበት ራሱ ባወጣው ሕግ ብቻ ሳይሆን በኅሊና ዳኝነትም ጭምር መሆን ይኖርበታል። የደራሲው መነሻ አሳብ ይህ ስለሆነ አድልዎ የተለየውና የተስተካከለ ህብረተሰብ ለመፍጠር እንደሚቻል ቪክተር ሀዩጎ በመጽሐፉ ያሳስበናል።

የዚህ ዓለም ሁለት ገጽታዎች ማለት ክፉትንና ደግነትን በማሳየት ከክፉት ደግነት እንደሚሻል በመግለጽና በተደጋጋሚ በማስገንዘብ ጽፏል። ቴናይዬን የክፋት ቁንጮ፣ ዣን ቫልዣን ለሌሎች ሰዎች የሚኖር የደግነት ተምሳሌት እንደሆነ ቁልጭ አድርጎ አቅርቧቸዋል።

መጽሐፉ ውስጥ ፍራንክ ወይም ሱስ እየተባለ የመገበያያ ገንዘብ ብዙ ጊዜ ተጠቅሷል። በዚያን ጊዜ በሞላ ጐደል አምስት ፍራንክ እንደ አንድ የአሜሪካን ዶላር ሲወሰድ ሃያ ሱስ ደግሞ አንድ ፍራንክ ነበር። ሌሎች የተጠቀሱት ሽርፍራፊ ገንዘቦች ዋጋ ከዚህ በታች የነበሩ ናቸው። በመጽሐፉ ውስጥ የተጠቀሱት ዓመተ ምህረቶች በእኛ ሳይሆን በአውሮጳውያን ዘመን አቆጣጠር ስሌት ላይ የተመሠረቱ ናቸው።

ሌላው ለአንባቢ መጠቀስ ያለበት ጉዳይ መጽሐፉን ስተረጉም የተጣቀምኩበት የአተረጓጎም ዘዴ ነው። አተረጓጎሜ የቃል በቃል ዓይነት ሳይሆን የተገለጸውን ጠቅላላ አሳብ ቀስሞ በሚገባ ቋንቋ በመጻፍ መጠቀሜን ለመግለጽ እወዳለሁ።

በመጽሐፉ ውስጥ የተጠቀሱትን አሳቦች በግልጽ ለማሳየትና እንዲገባ ለማድረግ፣ እንዲሁም ኢትዮጵያዊ ስሜትን ለማሳደር በኢትዮጵያዊ አባባሎች ተጠቅሜአለሁ። ከዚህም ሌላ ሳላበዛው እጅግ በጣም ውስን በሆነ መልኩ የራሴንም አሳብ አልፎ አልፎ አክያለሁ። ያም ቢሆን የአንባቢን ስሜት በይበልጥ ለመኰርኰር እንጂ የመጽሐፉን ይዘትና የደራሲውን አሳብ ለመለወጥ አይደለም።

በመሠረቱ ይህ መጽሐፍ ከአንድ መቶ ሰባ አምስት ዓመት በፊት የተደረሰ ሲሆን የተጻፈውም ለፈረንሳይ ማኅበረሰብ በመሆኑ አልፎ አልፎ ለፈረንሳዮች ብቻ ስሜት ሊሰጡ የሚችሉ አሳቦች አሉበት። ስለዚህ በጣም ጎልተው የሚታዩትንና የዚህ ዓይነት ስሜት ይሰጣሉ ብዬ የገመትኳቸውን አሳቦች ትርጉሜ ውስጥ አላካተትኳቸውም። ሆኖም ግን መጽሐፉ ሥረ-መሠረቱን እንዳይለቅ የተቻለኝን ጥረት ሁሉ አድርጌ አለሁ፤ የተሳካልኝም ይመስለኛል። ፍርዱን ግን ለአንባቢ በመተው አሳብ ካላችሁ በ0911 698023 መደወል ይቻላል።

ዮሐንስ ገብረ ጻድቅ

ፋንቴን

ምዕራፍ አንድ

ቱና ሰው

በ1815 ዓ.ም. ሚሴ ቻርልስ ብሮንሼኑ መሪል የሞንቴስ ሱር ሞንቴስ ሀገረ-ስብከት ጳጳስ ነበሩ። እድሜያቸው 75 ዓመት ሲሆን የሞንቴስ ሱር ሞንቴስ ሀገረ-ስብከት ጳጳስ ሆነው የተሾሙት በ1806 ዓ.ም. ነው። ጳጳሱ ወደ ሀገረ-ስብከታቸው ሲመጡ እህታቸው ወ/ት ፖፕቲስታን አብረዋቸው ነበር የመጡት። እህትዮዋ ምንም እንኳን ትዳር ባይመሠርቱም የእድሜ ባለፀጋ ስለነበሩ ወንድማቸውን በአስር ዓመት ይበልጣቸዋል።

ከጳጳሱ ቤት ውስጥ ሌላም ሴት ነበሩ። እኚህ ሴት በእድሜ የወ/ት ፖፕቲስታን እኩያ ናቸው። ሴትዮዋ ወ/ሮ ማግልዋር ይባላሉ። እኚህ ሴት ቀደም ሲል የሌላ ሰው አገልጋይ ሆነው ሠርተዋል። በዚያን ግን የወ/ት ፖፕቲስታንና የጳጳሱ ቤት ጠባቂ ሁነው ተቀጥረው ይሠራሉ።

ጳጳሱ ከሀገረ-ስብከታቸው እንደ ደረሱ በሀገሩ ደምብና ሥርዓት መሠረት ከፊልድ ማርሻል ቀጥሎ ያለው ሹመት ይሰጣቸዋል። የክፍለ-ሀገሩ መሪና የማዘጋጃ ቤቱ ሹም ከመኖሪያ ቤታቸው ድረስ ሄደው «እንኳን ደህና መጡ» በማለት እጅ ይነስዋቸዋል። አቡኑም በተራቸው ከዚያ ለተገኙ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ቡራኬ ይሰጣሉ። የከተማው ሕዝብም በነቂስ ወጥቶ አዲስ የተሾሙለትን ጳጳስ ለማየት ይጠባበቃል።

የጳጳሱ ቤት የተሠራው ከአንድ ከታወቀ ሆስፒታል አጠገብ ሲሆን ቤቱ እጅግ በጣም ሰፊና ያማረ ነው። ሆስፒታሉ የተገነባው ከረባዳ ሥፍራ ላይ ሲሆን ግቢው እንደ ጳጳሱ ቤት ስፋት የሌለው ነው። ጳጳሱ ወደዚያ በሄዱ በሦስተኛው ቀን ሆስፒታሉን ይጐበኛሉ። ከጉብኘቱ በኋላ የሆስፒታሉ አስተዳዳሪ ከቤታቸው ድረስ መጥቶ እንዲያነጋግራቸው ጋበዙት። አስተዳዳሪው ከጳጳሱ ቤት ይሄዳል። ከቤታቸው በመጣ ጊዜም «ሆስፒታላችሁ ውስጥ ስንት በሽተኞች አሉ?» ብለው አስተዳዳሪውን ሲጠይቁት «ሃያ ስድስት» አላቸው።

«ቁጥራቸው እኔ ከቆጠርኩት ጋር ስለሚገጥም አልተሳሳትኩም ማለት ነው» አሉ ጳጳሱ። ከዚያም ጳጳሱ የቤታቸውን አዳራሽ በዓይናቸው ቃኙት። አመለካከታቸው አዳራሹን በዓይን የሚለኩና የሚያከፋፍሉ ይመስል ነበር። «አዳራሹ ብቻ እስከ ሃያ አልጋ ሊይዝ ይችላል» አሉ እርስ በራሳቸው ሲነጋገሩ። ከዚያም ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ቀጥሎ ያለውን ተናገሩ።

«ወዳጄ የምለውን አጢነህ አድምጠኝ። ከዚህ አካባቢ አንድ የሆነ ስህተት የተፈጸመ ይመስላል። እናንተ የያዛችሁት ቤት አምስት ወይም

ስድስት ጠባብ የሆኑ ክፍሎች ናቸው ያሉት። ከእነዚያ ጠባብ ክፍሎች ውስጥ ሃያ ስድስት ሰዎች ይተኛሉ። እኛ ደግሞ ሦስት ሰዎች ብቻ ሁነን እያለ የያዝነው ቤት እጅግ በጣም ትልት ነው። እኛ የያዝነው ቤት እስከ ስልሳ ሰው ሊያስተኛ ይችላል። ታዲያ ይኼ ጉዳይ የአመዳደብ ችግር ያለበት አይመስልህም? ስለዚህ የእኛን ቤት አንተ ብትመሰድ፣ የአንተን ቤት ደግሞ እኛ ብንመሰድ ይሻላል።»

በሚቀጥለው ቀን ሃያ ስድስቱ በሽተኞች ወደ ጳጳሱ ቤት ተዛወሩ። ጳጳሱም ሆስፒታሉን ተረከቡ። ወሬው ከተማው ውስጥ ይኖር ከነበረው ሰው ሁሉ ጆሮ ውስጥ ገባ። በዚህ የተነሳ በጥቂት ቀናት ውስጥ የጳጳሱን በጎ ምግባር በመከተል ለበጎ ተግባር የሚውል እርዳታ ከያለበት ይጎርፍ ጀመር። በየቀኑ ከጳጳሱ ቤት በር የሚያንኳኳ ሰው ቁጥር እየበረከተ ሄደ። ሆኖም የሚመጣው ሰው ሁሉ እርዳታ ለማድረግ የመጣ ብቻ ሳይሆን ምፅዋት ለመቀበልም ነበር። ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ጳጳሱ የብዙ ችግረኞች ቀላቢ፣ ምፅዋት ሰጪና ገንዘብ ሰብሳቢ ሆኑ። ብዙ ገንዘብም ከጳጳሱ እጅ ውስጥ እየገባ ለድሃ ይሰጥ ጀመር። የሚገኘው ገቢ ግን ልክ ከደረቀ አፈር ላይ እንደሚፈስ ውሃ ገና ከመገኘቱ ወጪ ሆኖ በቶሎ ያልቃል። ጳጳሱ ገንዘብ ቢያገኙም ከተገኘው ገቢ ጥቂቱን እንኳን ለራሳቸው ለመውሰድ አልተመኙም፤ አልወሰዱምም። እንዲያውም ከነአካቴው የራሳቸውንም ገንዘብ ጭምር ይዞ ይሄድ ጀመር።

ጳጳሳትን ከስማቸው አስቀድሞ ንጽህናቸውን ለማረጋገጥ ብፁዕ ወቅዱስ እያሉ መጥራት የተለመደ ቢሆንም በዚያ አካባቢ ይገኙ የነበሩት ነዳያን ፍቅራቸውንና ቅርበታቸውን ለመግለጽና የጳጳሱን ደግነት ለማውሳት ብፁዕ ወቅዱስ በማለት ፈንታ «አባ ደጉ» እያሉ ይጠርዋቸዋል።

እኚህ ደግ ሰው በ1815 ዓ.ም. ምንም እንኳን 75 ዓመት ቢሞላቸውም ከሰልሳ ዓመት በላይ የሞላቸው አይመስሉም ነበር። ቁመታቸው እጅግም ረጅም ሳይሆን መጠነኛ ሆኖ ሰውነታቸው ደልዳላ ነው። ክብደታቸውን ለመቆጣጠር በእግር መሄድን ያዘወትራሉ። ሲራመዱም መሬት በኃይል እየረገጡ ከወገባቸው ትንሽ ጐበጥ ብለው ነው።

የልጅ ፈገግታን በተጐናጸፈ አንደበት ሲናገሩ የሰማቸው ሁሉ ከግርማ ሞገሳቸው ብዛት የተነሳ የመንፈስ እርካታን ያገኛል። ከመላ ሰውነታቸው ደስታ የሚፈልቅና የሚንፀባረቅም ይመስላል። ደስታ የተቈራኘው አካላቸውና ወተት የመሰለው ጥርሳቸው ፈገግ ያሉ እንደሆነ «ጪዋ፣ ደግና እድሜ የተቸረ ሽማግሌ» እያልን ለደጋግ ሰዎች የምንሰጠው ቅጽል ሁሉ ከእኚህ ሰው ሰውነት ላይ ጐልቶ ይታያል። ለመጀመሪያ ጊዜ ያያቸው

እንኳን ስለብቃታቸው፣ ስለደግነታቸውና ስለስብዕናቸው አይጠራጠርም። አንድ ሰው ለተወሰነ ጊዜ ከጳጳሱ ጋር ቢቆይና በአሳብ ባህር ተውጠው ቢያያቸው መንፈስ ቅዱስ ቀርቦአቸው ቀስ በቀስ መለወጣቸውን ይገነዘባል።

ግርማ ሞገሳቸው በቃላት ለመግለጽ በማይቻል መልኩ ያስፈራል። ስፈውና ከስታራው ፊታቸው፣ እንዲሁም ሻሽ የመሰለው ወጉራቸው ክብር የተጐናጸፈ ለመሆኑ በግልጽ ይታያል። ይኸው ግርማ ሞገሳቸው ከውስጥ እየፈለቀ ሲወጣ የሚያልቅ ቢመስልም የአንዐባራቂነት ኃይሉ ግን ብርታት እንዳለው አያጠራጥርም። እንዲያውም ከናካቴው አንድ ሰው ሁኔታቸውን በጥሞና ሲመለከት 'መልአክ በፈገግታ አጊጦ ያየኛል' የሚል ስሜት ይፈጥ ርበታል። እኚህ ካህን የሚያሰላስሉት ስለከበረ እንጂ ስለርካሽ ጉዳይ ላለመሆኑ ጥርጣሬ አይገባውም። ጸሎት ማድረስ፣ ምዕዋት መስጠት፣ የመንፈስ ስቃይ የደረሰበትን ማጽናናት፣ ወንድማማችነትን መስበክ፣ ራስን ለሌሎች መስዋዕት ማድረግና በእምነት ራስን መግራት የጳጳሱ የእለት ተእለት ኑሮ ሲሆን ይህም ኑሮአቸው በበጎ አሳብ፣ በምርጥ ቃላትና በበጎ ተግባር የተሞላ አደረገው።

ሁለቱ ሴቶች ሲተኙ ክረምት ይሁን በጋ፣ ብዙዕነታቸው ወደ ጓሮ ሄደው አትክልት ውስጥ በመቀመጥና ፈጣሪያቸውን በማሰብ ለአንድ ወይም ለሁለት ሰዓት ከዚያ ካልቆዩ ኑሯቸው የተሟላ አይመስላቸውም። አሳባቸውን ሰብስበውና የመንፈስ እርካታን ተጐናጽፈው የምሽቱን ሰላምና ፀጥታ ሌሎች ዓለማዊ ሰዎች ሊያገኙት ከሚችሉት እርካታ ጋር እያነጻጸሩና የከዋክብትን ብዛት እየተመለከቱ ነው ከአትክልቱ ሥፍራ የሚንሸራሸሩት። በዚያች ሰዓት አበቦች የሚለግዙትን መልካም መዓዛ እየማጉ ጥቅጥቅ ካለ ጨለማ ውስጥ እንደ በራ ሻማ ብቻቸውን በፍጥረታት መካከል በደስታ የተዋበው ነፍሳቸውን ዘርግተው ከአንድ ሥፍራ ይቆማሉ። አእምሯቸው ውስጥ ምን እንዳለ ቢጠየቁ መልሱን አያውቁትም። ሆኖም ከሰውነታቸው ውስጥ የሆነ ነገር ወጥቶ እንደሚሄድና ሌላ ነገር ደግሞ ከሰውነታቸው ላይ እንደሚያርፍ ይሰማቸዋል። ለማንኛውም አንድ ዓይነት ምሥጢር በውስጣቸው መከናወኑን ዘወትር ይገነዘባሉ።

እኚህ እድሜ የጠገቡና ፈጣሪያቸውን የቀረቡ ካህን የእረፍት ጊዜያቸውን የሚያጠፉት ቀን ቀን አትክልት በመኰትኰት ሲሆን ማታ ማታ ደግሞ በጸሎት ፈጣሪያቸውን በማመስገን ስለሆነ ከምድራዊ ዓለም ሌላ የሚፈልጉት ነገር አልነበራቸውም። ምድር በአበባ ሲደምቅና ሰማይ በከዋክብት ሲያጌጥ በተመለከቱ ቁጥር የመንፈስ እርካታ አግኝተው ልባቸው ይፈካል።

ምዕራፍ ሁለት

ወንድማች

ዘመኑ 1815 ዓ.ም. ወሩ ጥቅምት ነው። ፀሐይዋ ልትጠልቅ አንድ ሰዓት ያህል ሲቀራት አንድ በእግሩ የሚንዝ ሰው ከትንሺቱ ሞንቴስ ሱር ሞንቴስ ከተማ ይደርሳል። ከግል ቤቶቻቸው መስኮት አጠገብና ከመሥሪያ ቤቶቻቸው በራፍ የቆሙ ሰዎች ግለሰቡን ሲያዩ ለጨዋነቱ ጥርጣሬ ይገባቸዋል። ሆኖም ከግለሰቡ ይበልጥ የቁም ስቃይ ያየና የመከራ ሕይወት ያሳለፈ ሰው እንደሌለ ከገፅታው ያነባሉ።

የሰውዬው ቁመት መካከለኛና አጥንተ-ወፍራም ሲሆን በአፈጣጠሩ ግዙፍና ወፈር ያለ ነው። እድሜው የሙሉ ሰው ይመስላል። ምናልባትም አርባ ስድስት ወይም አርባ ሰባት ዓመት ይሆነዋል ሲሉ ከዚያ የነበሩ ሰዎች ገምተዋል። የከረረ ፀሐይ ጨረርና ከሰውነቱ የወጣው ላብ ያጠቁረውና ያንጋላታው ኮፍያ ፊቱን በከፊል ሸፍኖበታል። በአንድ በኩል ቀደም ሲል ከአካሉ የወጣው ላብ ፊቱ ላይ ደርቆና አዲስ የሚወጣውም ላብ ከፊቱ ላይ ሲወርድ ያየ ሁሉ ሰውዬው እጅግ የደከመው ለመሆኑ አልተጠራጠሩም።

የለበሰው ሸካራና ቢጫ ቀለም ያለው ሸሚዝ ከብዙ ቦታ ላይ በመቦጫጨቁ የደረቱን አጥንት ለፀሐይ አጋልጦ ከሲታነቱን በማሳየት ያሳጣዋል። ሸሚሱ አንደኛውን ነፋስ ይዞበት እንዳይሄድ ይመስላል በከረባትና አሮጌ መስቀል በተንጠለጠለበት ገመድ ያስያዘውና ያሰረው። የታጠቀው ሱሪ ሰማያዊ ቀለም ያለው ሲሆን እርሱም እጅግ ያረጀ ለመሆኑ የሚታይ ነው። ሱሬው ጉልበቱ ላይ ሳስቶ ሲነጣ ሌላው ጎኑ ተቀዳዷል። የሱሬው ሌላው ጎን የተቦጫጨቀና የተቀዳደደ ነው። አረንጓዴ ጨርቅ የተጣፈበትና ግራጫ መልክ ያለው አሮጌ ሰደርያም ደርቧል። በምናምን የተሞላ አዲስ አቄማዳ ከዱላ ጋር በማያያዝ በጀርባው በኩል አንጠልጥሏል። በአንድ እጁ ሌላ ትልቅ ቋር ያለው ዱላ ይዟል። የተንሻፈፈና በአንድ ጉኑ የተቀዳደደ አሮጌ ጫማ ያለ ካልሲ አጥልቋል። ፀጉሩን ከተላጨው ጥቂት ስለቆየ ጅፍ ያለ ፀጉር አብቅሏል። ጢሙም በኃይል አድጓል። ላቡና የሰውነቱ መዛል በእግር ብዙ መጓዙን ያመላክታሉ። ከላዩ ላይ የሰፈረው አዋራ ለሰውዬው መጐሳቈል ሌላ ማስረጃ ነው።

ይህ ሰው ከከተማው ውስጥ እንደ ገባ ወደ ግራ ታጥፎ ማዘጋጃ ቤት ወደሚገኝበት ሰፈር ያመራል። ከዚያም ከማዘጋጃ ቤቱ ሹም ቢሮ ገብቶ ለአሥራ አምስት ደቂቃ ያህል ጊዜ ከቆየ በኋላ ይወጣል። ቀጥሎ መንገደኛው ማረፊያ ቤት ወዳለበት ሰፈር ይጓዛል። የሄደበት ማረፊያ ቤት

በከተማው እጅግ የታወቀና ምርጥ ከሚባሉት አንደኛው ነው። በቀጥታ ወደ ማረፊያ ቤቱ ወጥ ቤት ሄደ። የወጥ ቤቱ የጓሮ በር ሰውዬው ከመጣበት ጐዳና በኩል ስለነበር መንገደኛው ወደ ማረፊያ ቤቱ የገባው በዚያ በኩል ነው።

ወጥ ቤቱ ውስጥ እንጨት ተያይዞና ድስት ተጥዶ እሳቱ በኃይል ይንቦገቦጋል። የወጥ ቤቱ ኃላፊ ኃይለኛው እሳት ከሚንድበት ርቆ በችኮላ እየተራመደ የምግቡን ሁኔታ ይታዘባል። የምግቡ ዝግጅት መመጠናቀቁን የሚጠብቁ ሌሎች መንገደኞች ቀጥሎ ከነበረው ክፍል ውስጥ ሲስቁና ሲጫወቱ ይሰማል። የሚዘጋጀው ምግብ መልካም ቃናና መዓዛ እንኳን ለሚያሸተውና ለሚቀምሰው በጐዳናው ላይ ለሚያልፈው ጭምር ከሩቅ የሚጠራ ዓይነት ስለነበር ከዚያ ቤት የገቡ ሰዎች ምን ዓይነት እንደ ነበሩ ለመገመት ያስችላል።

የወጥ ቤቱ ኃላፊ በር ሲከፈት ሰምቶ እንግዳ መግባቱን ስለተገነዘበ አንገቱን ሳያቀና «ጌታዬ፣ ምን ይፈልጋሉ?» ብሎ ሲጠይቅ «የሚላስ፣ የሚቀመስና ማደሪያ ነው የምፈልገው» የሚል መልስ ያገኛል። ከዚያም «ለእኛ ከዚህ የቀለለ ምን ነገር አለ!» ካለ በኋላ ኃላፊው አንገቱን ቀና አድርጎ ባይተዋሩን በመመልከት «ግን በቅድሚያ ይከፈላል» ይለዋል። እንግዳው ትልቅ ቦርሳ ከኪሱ አውጥቶ እያሳየው «ገንዘብማ አለኝ» ሲል መለሰለት።

«እንግዲያውስ ምን ልታዘዝ?» ሲል አስተናጋጁ በጠየቀው ጊዜ መንገደኛው ቦርሳውን መልሶ ከኪሱ ውስጥ ከተተው። ቀጥሎም ስልቻውን ከጫንቃው ላይ አውርዶ ከመሬት ላይ ወረወረው። ዱላውን እንደ ያዘ እሳት ከሚነድበት አጠገብ ሄዶ ከወንበር ላይ ቁጭ አለ። ከተማው የሚገኘው ከኮረብታ ጫፍ ላይ ሲሆን ወሩም ጥቅምት ስለነበር በጊዜው የነበረው አየር ቀዝቃዛ ነው። የቤቱ ባለቤት ከወዲያ ወዲህ እያለ መንገደኛውን አተኩሮ በመመልከት ደህና አድርጎ አጤነው።

«ምግብ ደርሷል?» ብሎ እንግዳው ሲጠይቅ «ተቃርቧል» አለ ኃላፊው።

እንግዳው ጀርባውን ለእሳት ሰጥቶ ሲሞቅ የሆቴሉ ባለቤት እርሳስ ከኪሱ ካወጣ በኋላ ከመስኮት አጠገብ ከነበረው አነስተኛ ጠረጴዛ ላይ ተቀምጦ ከነበረው የማስታወሻ ደብተር አንዲት ቅጠል ቀደደ። ከዚያም ከብጣሹ ወረቀት ላይ የሆነ ነገር ጽፎ ወረቀቱን በአቅራቢያው ለነበረውና እንደ ተላላኪም፣ እንደ ቤት ጠራጊም ያገለግል ለነበረው ልጅ እየሰጠው ወደ ልጁ ጆሮ ተጠግቶ የሆነ ነገር ሹክ አለው። ልጁ ወዲያው ወደ ማዘጋጃ ቤት ሹም ወደሚገኝበት አቅጣጫ እየሮጠ ሄደ። ይህ ሲሆን ግን መንገደኛው አላየም።

«እራት ደርሷል» ብሎ መንገደኛው በድጋሚ ሲጠይቅ «አዎን ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ምግብ ማቅረብ እንጀምራለን» አለው የቤቱ ጌታ።

ልጁ ወረቀቱን በእጁ እንደ ያዘ ተመለሰ። የሆቴሉ ባለቤት አሰቸኳይ መልስ ለመስማት እንደሚጓጓ ማንኛውም ሰው የተጣጠፈውን ወረቀት በችኮላ ከፍቶ ጽሑፉን በጥሞና ማንበብ ጀመረ። አንብቦ እንደ ጨረሰም በእንድ እጁ አገጩን ይዞ እንደ ማሰብና ሙተክዝ አደረገው። ከዚያም በእሳብ ባህር የተዋጠ ወደሚመስለው መንገደኛ ሄደ።

«ጌታዬ፣ ልረዳዎት ባለመቻሌ አዝናለሁ» አለ የሆቴሉ ባለቤት። «ያልተያዘ ክፍል ያለ መስሎኝ ነበር። አሁን እንደ ገባኝ፣ ያልተያዘ ክፍል የለንም።»

«ታዲያ» አለ መንገደኛው፤ «አልጋ እንኳን ባይኖር ከአንድ ጥግ ሳር ብጤ ተጐዝጉዞልኝ ለመተኛት እችላለሁ። ለማንኛውም አሁን በጣም ስለራበኝ እራት ቢሰጠኝ! የመኝታውን ጉዳይ ከዚያ በኋላ እንነጋገርበታለን።»

«እራትም ልሰጥዎት አልችልም» ብሎ ባለቤቱ ሲናገር «ይህስ ለነገር ነው» ካለ በኋላ መንገደኛው ከተቀመጠበት ብድግ አለ።

«እህ....እህህ፣ ታዲያ እኔ እኮ በጣም ስለራበኝ ጠኔ ይዞኛል» ብሎ ሲናገር «የሚሳስ፣ የሚቀመስ ስለሌለኝ ምንም ለማድረግ አልችልም» አለው የሆቴሉ ጌታ ሲመልስ። ሰውዬው ይህን ሲሰማ ሳቁን ለቀቀው። ወደ እሳት ማንደጃው ዞር ብሎ ከምድጃው ላይ የተጣደውን ምግብ ተመለከተ።

«ምንም የለኝም፤ ይኼ ሁሉ ምግብ እያለ!»

«ይኼ ሁሉ ምግብ የተዘጋጀው ለሌሎች ሰዎች ነው።»

መንገደኛው ተመልሶ ቁጭ አለ። ድምፁን ዝቅ አድርጎ «ሆቴል ቤት ውስጥ ነው ያለሁት። ደግሞም በጣም ርቦኛል። የትም አልሄድም፤ እኔ እንደሆነ ከዚሁ ቤት ውስጥ ነው የማድረው» ሲል ተናገረ።

የሆቴሉ ባለቤት አቀርቅሮና ንዴት እየተናነቀው «ሰውዬ ከዚህ ውጣ» ይላል። ይህን ጊዜ እንግዳው ወደሚጋየው እሳት ጠጋ ብሎ በያዘው ዱላ ትርኪሽ እንጨቶችን ወደ እሳቱ ረመጥ እያስጠጋ ሳለ «ውጣ» የሚል አንቧራቂ ድምፅ ይሰማል። መልስ ለመስጠት ፊቱን አዞረ። ሆኖም ግን የሆቴሉ ባለቤት አፍጥጦ እያየውና መልስ ለመስጠት እድል ሳይሰጠው «ቢበቃን ይሻላል፤ በቅድሚያ ሰዎችን በትህትና ማናገር ልማዴ ነው። ሆኖም ግን አንተ የእኔ ትህትና ስላልገባህ ያለ ጭቅጭቅ መንገድህን ብትቀጥል ይሻልሃል» ሲል በቁጣ ተናገረው።

መንገደኛው የሆቴሉን ጌታ እጅ ነስቶና ስልቻውን ተሸክሞ ከዚያ ቤት ወጥቶ ሄደ። አውራ ጉዳናውን ይዞ ወዴት እንደሚሄድ ሳያውቅ የሃፍረት ማቁን ተከናንቦ እንደ አዘነተኛና ከሚገባው በላይ እንደ ተዋረደ ሰው እየተሸማቀቀ ጉዞውን ቀጠለ። ያስጠጉኝ እንደሆነ በማለት ከመንገድ ዳር የነበሩ ቤቶች በር አንኳኳ። የሚያዝንለት ሰው ግን አላገኘም። ስለዚህ ፊቱን ከወዲያ ወዲህ ሳያዞር ቀጥ ብሎ ወደፊት ተጓዘ።

ጥሎት ከወጣው ሆቴል ቤት ቢመለስ ኖሮ የሆቴሉ ባለቤት ከዚያ ከነበሩ እንግዶችና ተላላፊ መንገደኞች ጋር ቆሞ በጣቱ እየጠቈመ ሲሳለቅበት ያይ ነበር። የእርሱ ወደዚያ መመለስ ደግሞ የከተማው ወሬ ስለእርሱ እንደሚሆን ከሁናቴያቸውና ከአመለካከታቸው ለመረዳት ይችል ነበር። ስለዚህ ባለመመለሱ መንገደኛው ይህን ሁሉ ጉድ አላየም። ከችግርና ከችጋር ውስጥ የሚዋትቱና የሚማቅቁ ሰዎች ወደ ኋላ ተመልሰው ያለፈውን አያዩም። ምነው ቢሉ! ሰንኳላ እድል እንደሚከተላቸው ጠንቅቀው ያውቃሉና።

ከአውራ ጎዳናው ሳይወጣ ለአጭር ጊዜ እንደ ተጓዘ ከዚያ በፊት አይቶት ከማያውቅ ሰፈር ደረሰ። በሀዘን የተጨማለቀና እጅግ የተከፋ ሰው ድካም እንደማይሰማው ሁሉ እርሱም ምንም እንኳን ብዙ ቢጓዝም የድካም ስሜት አልተሰማውም። ነገር ግን ከባድ የረሃብ ስሜት እንጀቱን ሞርሙሮታል። ሐሞቱ ሲንሰፈሰፍ ተሰማው። ጊዜው እየመሸ ስለሄደ ምድር በጨለማ ልትሸፈን ብዙም አልቀራት።

ከተባረረበት ሆቴል ቤት ጀምሮ ከኋላ ኋላው ይከተሉት የነበሩት ልጆች ድንጋይ ወረወሩበት። በቁጣ ወደ እነርሱ ዞሮ በያዘው ዱላ ሊያስፈራራቸው እንደ ወፍ መንጋ ተበተኑ። ከአንድ እስር ቤት በራፍ እንደ ደረሰ ከደወል ጋር ተያይዞ በር ላይ የተንጠለጠለ የብረት ሰንሰለት አየ። ወደ ኋላ መለስ ብሎ ደወሉን ደወለው። በሩ ተከፈተ።

ቆቡን አውልቆ «ጌቶች፣ ለዛሬ ብቻ ሊያሳድሩኝ ይችላሉ?» ሲል ራቅ ብሎ የተቀመጠውን ሰው በትህትና እጅ እየነሳ ጠየቀው።

«ይኼ እኮ እስር ቤት እንጂ ሆቴል ቤት አይደለም። የሆነ ወንጀል ሠርተህ ከመጣህ በሩን ልከፍትልህ እችላለሁ።»

የመልስ ሰጪው ድምፅ ራቅ ካለ ሥፍራ እንደ መጣ ያስታውቃል። በሩ ተመልሶ ተዘጋ። የዘበኞች ኃላፊ ነበር የተናገረው። ቀኑ እየመሸ ነው። ቀዝቃዛ አየር በአካባቢ ከነበረ ተራራ መንገደኛው ወደ ነበረበት አካባቢ በኃይል ይኳተላል። እግሩ እየከበደው ቢሄድም ባይተዋሩ ሰው መራመዱን

ቀጠለ። ከከተማው እንደ ወጣ ለማደሪያ የሚሆነው የትልቅ ዛፍ ከለላ ወይም የተከመረ የድርቆሽ ሳር እንደሚያገኝ ተሰፋ አደረገ። ቢሆንም እንዳቀረቀረ ጉዞውን ተያያዘው። ከመኖሪያ ሰፈር የወጣ ስለመሰለው አንገቱን ቀና አድርጎ አካባቢውን ቃኘ። ለካስ ከእርሻ ማሳ ውስጥ ነበር የገባው።

ከፊት ለፊቱ ከሚጥነው ጉብታ መሬት ላይ የነበረው አህል ታጭዶና ተወቅቶ ስለነበር አሁን የሚታየው ገለባ ብቻ ነው። አካባቢው ሁሉ የተላጨ ፀጉር መስሏል። ለማዩ ጨልሞ ደመና ዞሮበታል። ድቅድቅ ያለው ደመና በአካባቢው ከሚገኝ ኮረብታ ላይ ያረፈ አስመስሎታል። አልፎ አልፎ የሚታዩት ከዋክብት ብቅ ጥልቅ እያሉ ነፋስ እንደሚያወነውዘው ኩራዝ ከወዲህ ወዲያ እያሉ ይንከራተታሉ ለማለት ያስችላል። ጨረቃዋም ብትሆን ሳሳ ያለ ደመና ሲያጋጥማት ነጭ መስመር የዘረጋች ይመስል ብልጭ ድርግም ትላለች። አልፎ አልፎ መስመሩን የሚዘረጋው ጨረቃና ደፋ ቀና የሚሉት ከዋክብት አካባቢው በጨለማ እንዳይዋጥ ብርሃን ይፈነጥቁበታል። ስለዚህ መሬቱና ሰማዩ ጨርሶ አልጨለመም ነበር። አካባቢው ግን በጣም ያስፈራል።

ከጉብታውና ከተንጣለለው ሜዳ ላይ ከአንድ ቅርጸቢስ ከሆነ ዛፍ ሌላ በአካባቢው በጉልህ የሚታይ ሌላ ነገር የለም። ዛፉ መንገደኛው ከነበረበት ብዙም ሩቅ አይደለም። ባይተዋሩ ሰው ሁናቴው ስላላማረው ወደ መጣበት ተመለሰ። ጊዜው ከምሽቱ ወደ ሁለት ሰዓት ገደማ ይሆናል። ሰውዬው አካባቢውን ስለማያውቅ መንገድ እንደ መራው ዝም ብሎ ተጓዘ። የከንቲባውን ቤት እንዳለፈ ከሆነ ትምህርት ቤቱን እንዳለፈ የቤተክርስቲያን ቅጥር ገቢ ስላጋጠመው ቤተክርስቲያኑን እያየ እጁን ጨብጠ ወደ ሰማይ አንጋጠጠ። ከቤተክርስቲያኑ ፊት ለፊት የሆነ ማተሚያ ቤት አለ። ሰውዬው ድካም አወራጭቶት ስለነበር ከዚያ የተሻለ ሥፍራ ሳይፈልግ ከማተሚያ ቤቱ አጠገብ ከነበረው የድንጋይ መቀመጫ ላይ ጋደም አለ። ወዲያው እንደ ተጋደመ አንዲት አሮጊት ከቤተክርሲቲያኑ ወጥተው ወደ እርሱ መጡ።

«ወዳጄ ከዚህ ምን ታደርጋለህ?» ብለው ሲጠይቁት መጥፎ መልስ እንደ ለማቸው ሳይታወቀው «የእኔ አዛኝ፣ ቅቤ አንጓች፣ መተኛቴ ነዋ!» ሲል በቁጣና በድፍረት መለሰላቸው። ከብር የሚገባቸው አዛኝዋና ደግዋ ሴት ግጻም ላ ግርኩዝ ይባላሉ።

«እንዴ፣ ከድንጋይ ላይ!» አሉ ሴትዮዋ። «ሌሊቱን በሙሉ ከድንጋይ ላይ ተኝተህ በቀላሉ ሊነጋልህ አይችልም። ብዙ መንገድና ረሃብ እንዳንገላታህና ብርድ እንዳሰቃየህ ሰውነትህ ይመሰክራል። የሚያሰጠጋ አላገኘህም?» ሲሉ በዘዘኔታ ጠየቁት።

«ብዙ ቤት ሞክርኩ፣ የየቤቱን ደጃፍ እንኳኳሁ» ሲሳቸው ላለ አሉት። «ሁሉም ሰው ከበራፌ ሂድ አለኝ እንጂ ሊያስጠጉኝ አልፈቀዱም።

ደግሞ ሴት የሰውዬውን ጀርባ እየዳበሱ ከአደባባዩ ባሻገር የሚታየውን ከደጉ ጳጳስ ቤት አጠገብ የሚገኘውን ቤት እያሳዩ «ያንን ቤት ሞክረሃል? ብለው ሲጠይቁት «አዎን፣ እርሱንም ሞክረያለሁ» አሳቸው።

«ከዚያ ማዶ ከሚታየው ቤትስ?» ሲሉት «የለም» የሚል መልስ ሰጣቸው። «ከእዚያ ሞክር እስቲ!» ብለውት ሄዱ።

2

እኛ ደጉ ጳጳስ ከተማ ውስጥ ሲዘዋወሩ ስለቆዩና ስለደከማቸው ያን እለት ማታ ከክፍላቸው ሳይወጡ ከዚያው ቆዩ። በእለቱ ብዙ ሥራ ስለነበራቸውም «ሥራዬን ሳልጨርስ ማምሻዬን ከዚሁ አቆያለሁ» ብለው ስለወሰኑ ከዚያው አመሹ። ስለዚህ እስከ ምሽቱ ሁለት ሰዓት ድረስ ከክፍላቸው አልወጡም።

እንደ ወትሮው ከጳጳሱ አልጋ አጠገብ ከነበረው ቡፌ ጠረጴዛ ውስጥ ከብር የተሠሩ ሳህኖችን ለማውጣት መዳም ማግልዋር ከከፍሉ ሲገቡ ጳጳሱ ጉልበታቸው ላይ ብጣሽ ወረቀትና የማስታወሻ ደብተር አስቀምጠው የሆነ ነገር ሲጽፉ ነበር። ሴትዮዋ ከተመለሱ በኋላ ጥቂት ቆይቶ ገበታ እንደ ቀረበና እህታቸው እንደሚጠብቋቸው በመገመት ደጉ ጳጳስ ወደ ምግብ ቤት ሄዱ። ምግብ ቤቱ ያለበት ሥፍራ የአራት ማዕዘን ቅርጽ ያለው ዓይነት ሆኖ የእሳት ማንደጃ ምድጃም አለው። ካስፈለገም ወደ እሙራ ጎዳና የሚያስወጣ በርና በአትክልቱ በኩል ደግሞ ሰፋ ያለ መስኮት አለው።

መዳም ማግልዋር ገበታ ሠርተው እንደ ጨረሱ ጠረጴዛውን እያስተካከሉ ከመድኃኒቷ ባፕቲስታን ጋር ጨዋታ ጀመሩ። ከገበታው አጠገብ አነስተኛ ጠረጴዛ ላይ ሻማ በርቶ እየተቀጣጠለ ነው። ከእሳት ማንደጃው ውስጥ የተቀጣጠለው እሳት ከብድ ፍም ስለነበረው ክፍሉ በአሞር ጊዜ በጣም ሞቀ። የቤታቸው በር እንዴት ብሎ መቄለፍ እንዳለበት መዳም ማግልዋር ከእህትዮ ጋር ሲያወጉ ጳጳሱ ይገባሉ።

መዳም ማግልዋር ለእራት የሚሆን ሽቀጣሽቀጥ ለመግዛት ወደ ገበያ በሄዱ ጊዜ አንድ መግቢያ ያጣ ግጅራት መጪ ከተማ መግባቱንና ይህ ሰው በጊዜ ከየቤታቸው የማይገቡ ሰዎች ላይ አደጋ ሊያደርስ እንደሚችል ሲወራ ሰምተዋል። ሁለቱ ሴቶች ስለዚሁ ጉዳይ ሲያወሩ ነው ጳጳሱ ከምግብ ቤቱ የገቡት። ጳጳሱ እንደ ገቡ እህታቸው «እባኮትን፣ መዳም ማግልዋር ሾሚያወሩትን ሰምተዋል?» ሲሉ ጠየቅዋቸው።

«የምታውሩት ነገር ግልጽ ባይሆንልኝም በመጠኑ ሰምቻለሁ» አሉ ጳጳሱ። ከዚያም ፈታቸውን ወደሚንሀባሀው እሳት በማዞርና እጅጉቸውን ከጉልበታቸው ላይ በማሳረፍ እገልጋያቸውን እየተመለከቱ «ምንድነው ጉዳዩ? የሚያስፈራ ነገር አለ እንዴ?» ብለው ሲጠይቋቸው መዳም ማግልዋር እንደ መባላቸው ብዙም ሳያመነቱ ወሬውን በሚገባ እመርዋቸው።

«ያለ መጫሚያ ባዶ እግሩን የሚዘዝ ማጅራት መቺ፣ ሌባና ቀማኛ ከተማችን ውስጥ ገብቷል አሉ። ከነሞን ሳባር ሆቴል ሄዶ ማረፊያ ቢጠይቅ ከዚያ እንዲያድር ባለቤቱ አልፈቀዱለትም። ከመሸ በኋላ ደግሞ ከተማ ውስጥ ሲዘዋወር ብዙ ሰው አይቶታል። የያዘውን ስልቻ በገመድ አስሮና ትከሻው ላይ አድርጎ ነው ከበታ በታ ይዟዟር የነበረው። ያቱት ሁሉ እንዳሉት መልኩ በጣም የሚያስፈራ ነው።»

«እርግጠኛ ነሽ?» ብለው ጳጳሱ ሲጠይቁ በታሪኩ የተመሰጡና ፍርሃትም ያደረባቸው ስለመሰላቸው መዳም ማግልዋር ወሬያቸውን በኩራት ቀጠሉ።

«እመን አባታችን፣ እርግጠኛ ነኝ፣ የማወራው ስለእውነት ነው። በዛሬው ቀን ከተማችን ውስጥ እንድ ነገር እንደሚሆን የመጠራጠረው አይደለም። የዙሪያው ሰው ሁሉ ስለዚሁ ጉዳይ ነው የሚያወራው። መድሚዜል ባፕቲስታን እንደምትለው....» በማለት ሴትዮዋ ንግግርዋን ስትቀጥል የጳጳሱ እህት ጣልቃ ገብተው «እኔ ያልኩት ነገር የለም» ይላሉ። ተቃውሞውን እንዳልሰሙ መስለው መዳም ማግልዋር ልፍለፋቸውን ቀጠሉ።

«የዚህ ቤት ደህንነትም ብዙ የሚያስተማምን አይደለም። አባታችን የሚፈቅዱልኝ ከሆነ የቁልፍ ሠራተኛችን የድሮዎቹን መቀርቀሪያዎች መልሶ እንዲተመታቸው ሄጀ ልንግረው። መቀርቀሪያዎቹ ለዛሬ ብቻ ሳይሆን ለወደፊትም ደህንነታችን ይረዳሉ። በቀላሉ የሚከፈት በር እጅግ አደገኛና አስፈሪ ነው። ይቅርታ ይደረግልኝና፣ አባታችን እንደሆኑ እከሌ-ሌሊት ቢሆን እንኳን ማንኛውም ሰው ቢመጣ «ቤት ለእንግዳ ይዝቡ» የሚለት ልምድ አለብዎት። መቼም ስለዚህ ጉዳይ ፈቃድ መጠየቅ እንኳን አስፈላጊ...» እያሉ ሴትዮዋ አሳባቸውን ሳያጠቃልሉ በር በኃይል ደንኳኳል። እንደ ልማዳቸው ጳጳሱ «ይግቡ» ባሉ ጊዜ በሩ ተከፈተና አንድ ሰው ቤተሰቡ ከነበረበት ክፍል ውስጥ ገባ።

ያ የምናውቀው ማደሪያ ፍለጋ ከቤት ቤት፣ ከሥፍራ ሥፍራ ይንከራተት የነበረው መንገደኛ ነበር። ሰውዬው በሩን መልሶ ሳይዘጋ አንድ እርምጃ

ወደፊት ተራምዶ ቆም አለ። አቄማዳውን በጀርባው እንዳዘለና ዱላውን እንደያዘ ነው። የአሳቱ ውጋገን ከፊቱ ላይ ሲያርፍ ሸካራውና ጽኑው ያጐነቈለው ፊቱ የጭካኔ ምልክት እንዳለው አጐላበት። ሆኖም ያ ስሜት ወደ ውስጥ የተቀበረ እንጂ በግልጽ ወደ ውጭ የወጣ አልነበረም። ሚ ሰውነቱ ግን መናፍስት በአካል የታዩበት ነበር የሚመስለው።

መዳም ማግልዋር ለመጮህ ቢፈልጉም የሆነ ነገር አቅም አሳጣቸው። ስለዚህ አፋቸውን እንደ ከፈቱ ደርቀው ቀሩ። መድሚዜል ባጥቂስታ ደግሞ ፊታቸውን ባዞሩ ጊዜ ሰውዬው ወደ ውስጥ ሲገባ አዩ። በፍርሃት ተውጠው ከመቀመጫቸው ብድግ አሉ። ከዚያም ዝግ ብለው ፊታቸውን ወደሚነድደው እሳት አዙረው ወንድማቸውን ተመለከቱ። ከሰውዬው ዓይን ሲርቁ መንፈሳቸው ትንሽ ተረጋጋ። ጳጳሱ ግን መንገደኛውን በጥሞናና በቅንነት ነበር ያዩት። ምን እንደሚፈልግ ሲጠይቁት ሴላ ነገር ለማለት እድል ሳይሰጣቸው ፈጥኖ የያዘውን ዱላ በሁለት እጁ ተመርኩዞና ከዚያ የነበሩትን ሁሉ አንድ በአንድ ቃኝቶ ድምፁን ከፍ አድርጎ መናገር ጀመረ።

«ተመልከቱኝ! ስሜ ዣን ቫልዣ ይባላል። የተፈረደብኝ ወንጀለኛ ነኝ። ለአሥራ ዘጠኝ ዓመት ታስሬአለሁ። ከአራት ቀን በፊት ነው ከእስር የተፈታሁት። እሁን ወደ ፖንታልዬ ነው የምሄደው። ከእስር ቤት በወጣሁበት ቀን ከቱሉን ተነስቼ በእግር እየተጓዝኩ ዛሬ ከዚህ ደርሻለሁ። በዛሬው ቀን ብቻ 55 ኪሎ ሜትር ያህል ተጉዣለሁ። ማምሻዬን ከዚህች ከተማ እንደ ገባሁ ወደ ሆቴል ቤት ሂጀ ማደሪያ እንዲሰጡኝ ጠየቅሁ። ከእስር ቤት የተሰጠኝ መታወቂያ ብቻ በመያዜ መኝታ ሊሰጡኝ አልፈለጉም። ወደ ወህኔ ቤት ሂጀ እንዲያሳድሩኝ ብጠይቃቸው ከዚያም አባረሩኝ። ከከተማ ወጣ ብዬ ከዛፍ ስር ለማደር ፈልጌ ነበር። ነገር ግን ጨለማውን ፈራሁት። ደመናም ሰጣንገበበ ዝናብ ይዘንባል ብዬ ሰጋሁ። ደግ አምላክ ኖሮም ዝናቡን ያቆማል ብዬ ስላሳመንኩ አሁንም መጠጊያ ፍለጋ ወደዚች ከተማ ተመለስኩ። ከከተማው መኻል ከሚገኘው ቤተክርስቲያን ፊት ለፊት ከድንጋይ ላይ ተጋደምኩ። ከዚያ እንደ ተጋደምኩ አንዲት ደግ ሴት ቤታችሁን በመጠቈም «ከእዚያ ቤት አንኳኳ» አለችኝ። ስለዚህ በቀጥታ ወደ ቤታችሁ መጥጨ በራችሁን አንኳኳሁ። ለመሆኑ ይህ ቤት የማን ቤት ነው? ሆቴል ቤት ከሆነም ገንዘብ አለኝ። እስር ቤት ውስጥ እያለሁ ሥራ ሠርቼ ያጠራቀምኩት 109 ፍራንክና 15 ሰብ ይገርአለሁና ሂሣቢን መክፈል እችላለሁ። አሁን በጣም ስለደመኝ ለማረፍ እፈልጋለሁ። በአንድ ቀን 55 ኪሎ ሜትር መጓዝ ምን ያህል ሊያደክም እንደሚችል የምታውቁት ይመስለኛል። ደግሞም በጣም ርቦኛል። ታዲያ ማደሪያ ልትሰጡኝ ትችላላችሁ?»

«መዳም ማግልዋር» አሉ ጳጳሱ፣ «ሴላ ሳህን አምጪ» ሲሉም ደጉ የቤተክርስቲያን ሰው አዘዙ።

እንግዳው ወደፊት ራመድ ብሎ ከጠረጴዛው ላይ ተቀምጠ ይበራ ወደ ነበረው የሻማ መብራት ጠጋ አለ። ሰዎቹ ችግሩን ያላወቁለት ስለመሰለው «ቆዩ እስቲ» ሲል ጮክ ብሎ ተናገረ። ቀጥሎም «የተግባባን አልመሰለኝም። ተግባባን እንዴ? እኔ እኮ የመርከብ ቀዛፊ ባሪያና ወንጀለኛ ነኝ። ያንን አድካሚ የሆነውን መርከብ የመቅዘፍ ሥራ ስሠራ የኖርኩ ሰው ነኝ። መታወቂያዬን ልትመለከቱ ትችላላችሁ። መታወቂያዬ የወንጀለኛ መታወቂያ ነው። ሴላ መታወቂያ ስለሌለኝ በሄድኩበት ሁሉ ሰዎች አባረሩኝ እንጂ አልተቀበሉኝም። ከፈለጋችሁ መታወቂያዬን ውሰዱት፣ ምንም አልጠቀመኝም። በሄድኩበት ሁሉ ሰው እንዳያባርረኝ አልረዳኝም። ታዲያ እናንተስ ትቀበሉኛላችሁ ወይስ ታባርሩኛላችሁ? ለመሆኑ ይህ ቤት ሆቴል ቤት ነው? የምቀምሰው ነገርስ ልትሰጡኝ ትችላላችሁ? የማደሪያስ ጉዳይ እንዴት ነው? ከከብቶች ማደሪያ ጋጣ ቢሆን እንኳን አልጠየቁም» አያለ ሰውዬው ሲቀባጥር ደጉ ጳጳስ ወደ አገልጋያቸው ፊታቸውን አዞሩ።

«መዳም ማግልዋር፣ ከእኔ መኝታ ቤት አጠገብ ካለው ክፍል ውስጥ የሚገኘው አልጋ ይነጠፍ።» መዳም ማግልዋር ትእዛዙን ለመፈጸም ከከፍሉ ወጥተው ወደ ክፍሉ አመሩ። ደጉ ጳጳስ ፊታቸውን ወደ እንግዳው አዞሩ።

«ልጄ፣ ከእሳቱ አጠገብ ቁጭ በልና ሰውነትህን አሟሙቅ። በእጥር ጊዜ ውስጥ ገበታ ይቀርባል። እኛ እራታችንን እየበላን መኝታ ይዘጋጅልሃል» ሲሉት መንገደኛው አሳባቸው ምን እንደሆነ ገባው። ያ አስፈሪና ጭጋግ የመሰለው ፊቱ ተፈታ። የደስታ ውጋገንም ከፊቱ ላይ ይታይ ጀመር።

«እውነትም እነዚህ ሰዎች ማደሪያ ሊሰጡኝ ይሆን እንዴ?» ሲል ራሱን ጠየቀ። ሆኖም ግን ነገሩ ሁሉ እውነት ስላልመሰለው አሁንም የሆነ ያልሆነውን ይቀባጥር ጀመር።

«እውነት ነው? እንዴት? በእርግጥ ልታሳድሩኝ ነው? ወይስ አሳባችሁን ትቀይራላችሁ? ወንጀለኛውን? ሌሎች እንደ ቈሻሻ እያዩኝ 'አንተ ውሻ፣ ከዚህ ውጣ' ብለው አባረሩኝ። እርስዎ ግን በአክብሮት ነው የሚያናግሩኝ። አሁን ከልብዎ ነው? ከቤትዎ ውስጥ እንዳድር ፈቅደውልኛል? በእርግጥም ጥሩ ሰዎች ናችሁ። እኔ ደግሞ ገንዘብ ስላለኝ በሚገባ እከፍላችኋለሁ። ይቅርታ ብቻ! ድፍረት ባይሆንብኝ፣ የሆቴሉ ባለቤት እርስዎ ይመስሉኛል፣ ትክክል ነኝ፣ አይደል? ስምዎን ልጠይቅ፣ የጠየቁኝን እከፍላለሁ። ጥሩ ሰው ኖት። የሆቴሉ አስተዳዳሪና ባለቤት ኖት? ወይስ አይደሉም?»

«ከዚህ ቤት ውስጥ የምናር ካህን ማለቴ መነበሩኔ ነኝ» አሉ ቋጳሱ በጠማታ።

«መነኩሴ!» አለ ሰውዬው በመገረም። እ! መነበሩኔ! እንግዲያውስ፣ ገንዘብ እያስከፋሉኝማ? የተጉዳን የሚረዱ፣ የተጠቃን የሚያጽናኑ ስላሆኑ ለነፍስዎ ያደሩ ሰው ኖታ! ልክ ነኝ፣ አይደል? የዚያ በሩቁ ያየሁት ቤተ ክርስቲያን ቁሰ-ገበዝ መሆንዎ ነዋ! አዎን፣ መሆን አለብዎት። እንዴት ያለሁ ደደብ ሰው ነኝ። እንዴት ብዬ ነው ያጠለቁትን ቆብ አለማየቴ፣ ልብ አላልኩትም እኮ!» ሰውዬው በዚህ ዓይነት የባጥ የቆጡን እየቀባጠረ ስልቾውንና ዱላውን ከእንድ ጥግ አስቀምጦ መታወቂያውን ወደ ቦርሳው ከመለስ በኋላ ቁጭ አለ።

«አባታችን፣ ሰብአዊ ርህራሄና ፈሪሃ እግዚአብሔር ያደረብዎት ሰው ናት። እኔን እንደ ሌሊች ሰዎች አላንቋሻሸኝም። አባታችን የካህናት ሁሉ ምሳሌ ናት። ኤኔ በማውቀው እንደ እርስዎ ያለ ካህን ያለ አይመስለኝም። እንግዲያውማ ገንዘብ ልክፍል ብል እንኳን አይቀበሉኝም ማለት ነዋ!» ሲላቸው «የለም፣ አልቀበልህም» አሉ ቋጳሱ። «ገንዘብህን ያዘው» ካሉ በኋላ ቢጎይል ተነፈሱ። ሰውዬው ግን ልፍለፋውን ቀጠለ።

«አባታችን፣ ብዙዕ ወቅዱስ የሚባሉና ሥጋዎን ረስተው ለነፍስዎ ያደሩ ናታ! ከእዚያ አስከፊ እስር ቤት እያለሁ አንዳንድ ቀን እየመጡ የሆኑ ቋጳስ ትምህርት ይሰጡን ነበር። አንድ ቀን መጥተው ሲያስተምሩን ሰዎች 'አባታችን እያሉ ሲጠርዋቸው ሰምቻለሁ። ቋጳሱ ማርሴይ ከተባለ አገር እንደመጡና የዚያ አገር ሊቀ ጳጳስ እንደሆኑ ነግረውናል። በተጨማሪም እኚህ ሰው የጳጳሶች ጳጳስ ናቸውም ብለውናል። እዩ አባቴ፣ እንዴት ብዙ እንደምዘባርቅ! እኔ እንደሆንኩ ምኑንም አልያዝኩትም። አባታችን በመጀመሪያ ያሉኝን አልገባኝም ነበር፣ ይቅርታ ያድርጉልኝ። እኛ መሐይሞች እኮ ብዙ ነገር አናውቅም። እኛ ጳጳስ አንድ ቀን ከቤተመቅደስ ገብተው ቅዳሴ መርተዋል። አንድ ሾል ያለና ከወርቅ የተሠራ ቆብ ከሚንቀሳቀሱበት ላይ ደፍተው ሳለ የዐይ ጪረር ከሆነ ቦታ ገብቶ ካጠለቁት ቆብ ላይ ሲያርፍ እጅግ በጣም ያብረቀርቅ ነበር። በሰልፍ እንደንቆም ስለተደረገና እኛ ከነበርንበት ብዙም ብርሃን ስላልነበረ ጳጳሱ ጉልህ ሁነው አልታዩንም። ንግግር ሲያደርጉልን ግን ታይተውናል። ሆኖም በመዝከሳችን ርቀት ስለነበረ የሚሉትን ሳሙ ት ለመስማት አልቻልኩም። ጳጳስ ግሰቱ ይኸዉ ነው መሰለኝ።»

እንግዳው ሲናገር ቋጳሱ እርሱ በርግዶ የተወውን በር ሂደው ዘጉ። መጽም ግንልዋር ተጨማሪ ሳህን ይዘው መጥተው ከጠረጴዛ ላይ አኖሩ።

«መጻም ማግልዋር» አሉ ቋጳሱ፣ «አሁን ያመጣሽውን ሳህን እሳቱ ከሚነድበት ሥፍራ ተረብ አድርገሽ አኑሪው» ካሉ በኋላ ወደ እንግዳው ፊታቸውን አዙረው «የውጨዉ አየር በጣም ይቀዘቅዛል፣ ሳያበርድህ አይቀርም ልጄ» አሉት። ቋጳሱ ረጋ ባለመንፈሰና ለመሰማት በሚጋብዝ ድምፅ «ልጄ» እያሉ በጠሩት ቁጥር የሰውዬው ፊት ወጣ ይላል።

ወንጀለኛን «ልጄ» እያሉ መጥራት ግለት ባህር ላይ ቁጭ ብሎ በውሃ ጥም ለተቃጠለ ሰው አንድ ብርጭቆ ንጹህ ውሃ እንደ መስጠት ያህል እንደሆነ የሚጠራጠሩት አይደለም። የተናቀ ሰው ክብር ይጠግባል።

«ፋኖሱ በቲ ብርሃን አያወጣም» ብለው ቋጳሱ ሲናገሩ መጻም ግግልዋር ገባቸው። ስለዚህ ወደ ቋጳሱ መኝታ ቤት ሂደው ሁለት ክብር የተሠሩ ሪጀጅም የሻማ ማብሪያ አመጡ። ሻማ ለኩሰው ከሻማ ማስቀመጫ የብር እቃ ላይ ካኖሩ በኋላ ከምግብ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጥዋቸው።

«አባታችን» አለ ሰውዬው፣ «ጥሩ ሰው ናት። እኔን አልናቁኝም፣ አላንቋሸሹኝም። ቤትዎ ውስጥ ከማስጠጋት አልፈው በትህትናና በአክብሮት ያናግሩኛል። ለእኔ ክብር ብለው ተጨማሪ ሻማ እንዲበራ አደረጉ። እኔም የሕይወት ታሪኬን ሳልደብቅ ከየት እንደ መጣሁና ምን ያህል የተሰቃየሁ ሰው መሆኔን ገለጽኩሎት» ሲላቸው ከአጠገቡ የተቀመጡት ደጉ ቋጳስ ቀስ ብለው የእንግዳውን እጅ ይዘው የሚከተለውን ተናገሩ።

«ማን እንደሆንክ እንድትነግረኝ አልፈልግም። ይህ ቤት የእኔ ቤት አይደለም፣ የእግዚአብሔር ቤት እንጂ። ፈጣሪ የማንኛውም ባይተዋር ችግር፣ መከራና ስቃይ ያያል እንጂ ማንነቱን አይጠይቅም። አንተ ከባድ መከራና ስቃይ ደርሶብሃል። ብዙ ተርበሃል፣ ተጠምተሃል። ስለዚህ ቤቴ ቤትህ ሲሆን ለዚህም እንድታመሰግነኝ አልፈልግም። 'አስጠጋችም' ብለህ አትጠይቀኝ። ይህ ቤት ማረፊያ ለሚፈልግና ለተቸገረ እንጂ የማንም ቤት አይደለም። ማነው መንገደኛ? ማነው እንግዳ? እመነኝና አንተ ከእኔ ይበልጥ ቤተኛ ነህ። ከእዚህ ቤት ውስጥ ያለው ነገር ሁሉ ያንተ ነው። ያንተን ስም ማወቅ ለእኔ አስፈላጊ አይደለም። ከዚህም በላይ አንተ ሳትነግረኝ እኔ አውቄዋለሁ» ሲሉት ሰውዬው በመገረም አፉን ከፈተ።

«እውነትዎን ነው? ማን እንደሆንኩ አውቀዋል?» ብሎ ሲጠይቃቸው «አዎን፣ ስምህ ወንድሜ ነው» አሉት ደጉ ቋጳስ።

«በቃ....በቃ አባቴ» ሲል ተናገረ። «ከዚህ ቤት ውስጥ ስገባ ጠኔ ይዞ ያሰቃየኝ ነበር። አሁን ግን የደግነትዎ ብዛት ይሁን እኔ እንጃ፣ ምን እንደ ነካኝ አላውቅም። ምንም ነገር ሳልቀምስ ያ ሁሉ ረሃብ ተወግዶልኛል።»

«ከዚህ ቤት ውስጥ የምኖር ካህን ማለቴ መነኩሴ ነኝ» አሉ ጳጳሱ በዝግታ።

«መነኩሴ!» አለ ሰውዬው በመገረም። እ! መነኩሴ! እንግዲያውስ፣ ገንዘብ እያስከፍሉኝማ? የተጉዳን የሚረዱ፣ የተጠቃን የሚያጽናኑ ስለሆኑ ለነፍስዎ ያደሩ ሰው ኖታ! ልክ ነኝ፣ አይደል? የዚያ በሩቁ ያየሁት ቤተ ክርስቲያን ቄስ-ገዝዝ መሆንዎ ነዋ! አዎን፣ መሆን አለብዎት። እንዴት ያለሁ ደደብ ሰው ነኝ። እንዴት ብዬ ነው ያጠለቁትን ቆብ አለማየቴ፣ ልብ አላልኩትም እኮ!» ሰውዬው በዚህ ዓይነት የባጥ የቆጡን እየቀባጠረ ስልቻውንና ዱላውን ከአንድ ጥግ አስቀምጦ መታወቂያውን ወደ ቦርሳው ከመለስ በኋላ ቁጭ አለ።

«አባታችን፣ ሰብአዊ ርህራሄና ፈሪሃ እግዚአብሔር ያደረብዎት ሰው ኖት። እኔን እገደ ሌሊች ሰዎች አላንቋሻሹኝም። አባታችን የካህናት ሁሉ ምሳሌ ኖት። ሌኔ በማውቀው እንደ እርስዎ ያለ ካህን ያለ አይመስለኝም። እንግዲያውማ ገንዘብ ልከፍል ብል እንኳን አይቀበሉኝም ማለት ነዋ!» ሲላቸው «የለም፣ አልቀበልህም» አሉ ጳጳሱ። «ገንዘብህን ያዘው» ካሉ በኋላ ቢጎይል ተነፈሱ። ሰውዬው ግን ልፍለፋውን ቀጠለ።

«አባታችን፣ ብዙዕ ወቅዱስ የሚባሉና ሥጋዎን ረስተው ለነፍስዎ ያደሩ ኖታ! ከእዚያ አስከፊ እስር ቤት እያለሁ አንዳንድ ቀን እየመጡ የሆኑ ጳጳስ ትምህርት ይሰጡን ነበር። አንድ ቀን መጥተው ሲያስተምሩን ሰዎች 'አባታችን' እያሉ ሲጠርዋቸው ሰምቻለሁ። ጳጳሱ ማርሴይ ከተባለ አገር እንደመጡና የዚያ አገር ሊቀ ጳጳስ እንደሆኑ ነግረውናል። በተጨማሪም እኚህ ሰው የጳጳሶች ጳጳስ ናቸውም ብለውናል። አዩ አባቴ፣ እንዴት ብዬ እንደምዘባርቅ! እኔ እንደሆንኩ ምኑንም አልያዝኩትም። አባታችን በመጀመሪያ ያሉኝን አልገባኝም ነበር፣ ይቅርታ ያድርጉልኝ። እኛ መሐይሞች እኮ ብዙ ነገር እናውቅም። እኛ ጳጳስ አንድ ቀን ከቤተመቅደስ ገባተው ቅጸሊ መርተዋል። አንድ ሾል ያለና ከወርቅ የተሠራ ቆብ ከሥንቅላታቸው ላይ ደፍተው ሳለ የፀሐይ ጨረር ከሆነ ቦታ ገብቶ ካጠለቁት ቆብ ላይ ሲያርፍ እጅግ በጣም ያብረቀርቅ ነበር። በሰልፍ እንድንቆም ስለተደረገና እኛ ከነበርንበት ብዙም ብርሃን ስላልነበረ ጳጳሱ ጉልህ ሁነው አልታዩኝም። ንግግር ሲያደርጉልን ግን ታይተውኛል። ሆኖም በመከለላችን ርቀት ስለነበረ የሚሉትን ሳመ ት ለመስማት አልቻልኩም። ጳጳስ ግለት ይኸዉ ነው መሰለኝ።»

እንግዳው ሲናገር ጳጳሱ እርሱ በርግዶ የተወውን በር ሂደው ዘጉ። መዳም ማግልዋር ተጨማሪ ሳህን ይዘው መጥተው ከጠረጴዛ ላይ አኖሩ።

«መዳም ማግልዋር» አሉ ጳጳሱ፣ «አሁን ያመጣሽውን ሳህን እሳቴ ከሚነድበት ሥፍራ ቀረብ አድርገሽ አኑሪው» ካሉ በኋላ ወደ እንግዳው ፊታቸውን አዙረው «የውጪ አየር በጣም ይቀዘቅዛል፣ ሳይብርድህ አይቀርም ልጄ» አሉት። ጳጳሱ ረጋ ባለመንፈስና ለመሰማት በሚጋብዝ ድምፅ «ልጄ» እያሉ በጠሩት ቁጥር የሰውዬው ፊት ወጣ ይላል።

ወንጀለኛን «ልጄ» እያሉ መጥራት ግለት ባህር ላይ ቁጭ ብሉ በውሃ ጥም ለተቃጠለ ሰው አንድ ብርጭቆ ንጹህ ውሃ እንደ መሰጠት ያህል እንደሆነ የሚጠራጠሩት አይደለም። የተናቀ ሰው ክብር ይጠማዋል።

«ፋኖሱ በቂ ብርሃን አያወጣም» ብለው ጳጳሱ ሲናገሩ መዳም ማግልዋር ገባቸው። ስለዚህ ወደ ጳጳሱ መኝታ ቤት ሂደው ሁለት ከብር የተሠሩ ረጃጅም የሻማ ማብሪያ አመጡ። ሻማ ለኩሰው ከሻማ ማስቀመጫ የብር እቃ ላይ ካኖሩ በኋላ ከምግብ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጥዋቸው።

«አባታችን» አለ ሰውዬው፣ «ጥሩ ሰው ኖት። እኔን አልናቁኝም፣ አላንቋሸሹኝም። ቤትዎ ውስጥ ከማስጠጋት አልፈው በትህትናና በአክብሮት ያናግሩኛል። ለእኔ ክብር ብለው ተጨማሪ ሻማ እንዲበራ አደረጉ። እኔም የሕይወት ታሪኬን ሳልደብቅ ከየት እንደ መጣሁና ምን ያህል የተሰቃየሁ ሰው መሆኔን ገለጽኩሉት» ሲላቸው ከአጠገቡ የተቀመጡት ደጉ ጳጳስ ቀስ ብለው የእንግዳውን እጅ ይዘው የሚከተለውን ተናገሩ።

«ማን እንደሆንክ እንድትነግረኝ አልፈልግም። ይህ ቤት የእኔ ቤት አይደለም፣ የእግዚአብሔር ቤት እንጂ። ፈጣሪ የማንኛውም ባይተዋር ችግር፣ መከራና ስቃይ ያያል እንጂ ማንነቱን አይጠይቅም። አንተ ከባድ መከራና ስቃይ ደርሶብሃል። ብዙ ተርበሃል፣ ተጠምተሃል። ስለዚህ ቤቴ ቤትህ ሲሆን ለዚህም እንድታመሰግነኝ አልፈልግም። 'አስጠጋኝም' ብለህ አትጠይቀኝ። ይህ ቤት ማረፊያ ለሚፈልግና ለተቸገረ እንጂ የማንም ቤት አይደለም። ማነው መንገደኛ? ማነው እንግዳ? እመነኝና አንተ ከእኔ ይበልጥ ቤተኛ ነህ። ከእዚህ ቤት ውስጥ ያለው ነገር ሁሉ ያንተ ነው። ያንተን ስም ማወቅ ለእኔ አስፈላጊ አይደለም። ከዚህም በላይ አንተ ሳትነግረኝ እኔ አውቄዋለሁ» ሲሉት ሰውዬው በመገረም አፉን ከፈተ።

«እውነትዎን ነው? ማን እንደሆንኩ አውቀዋል?» ብሎ ሲጠይቃቸው «አዎን፣ ስምህ ወንድሜ ነው» አሉት ደጉ ጳጳስ።

«በቃ....በቃ አባቴ» ሲል ተናገረ። «ከዚህ ቤት ውስጥ ስገባ ጠኔ ይዞ ያሰቃየኝ ነበር። አሁን ግን የደግነትዎ ብዛት ይሁን እኔ እንጃ፣ ምን እንደ ነካኝ አላውቅም። ምንም ነገር ሳልቀምስ ያ ሁሉ ረሃብ ተወግዶልኛል።»

ጳጳሱ እንደገና አተኩረው ከተመለከቱት በኋላ «ብዙ መከራና ስቃይ ደርሶብሃል» አሉት በድጋሚ።

«ወይ ጉድ፣ ያቺ ቀይዋ ጥብቆ! የብረት ሰንሰለቱ! የእንጨት መኝታው! ቃል ቢተነፍሱ የማይሰማው የጨለማ ቤት! በታመሙ ጊዜ እንኳን ከዚያ ጨለማ ቤት በብረት ሰንሰለት ተጠፍሮ መኖሩ! ውሾች እንኳን ከዚያ የተሻለ ኑሮ ነው የሚኖሩት። አሥራ ዘጠኝ ዓመት! አርባ ስድስት ዓመቴ ነው። ከዚህ ሁሉ ስቃይ በኋላ መታወቂያዬ የወንጀለኛ ነው። ባጭሩ፣ ይኸው ነው የእኔ ታሪክ።»

«ያዙኝ» አሉ ጳጳሱ፤ «የስቃይና የመከራ ቤት ለቅቀህ ወጥተሃል። አሁን ግን እኔን ስማኝና ምክሬን ተቀበል። ያ አስፈሪና አሳዛኝ የሆነ ሥፍራ በሰዎች ላይ ጥላቻና ቁጣ አሳድሮብህ የምትለቅቀው ከሆነ አንተም ራስህ አሳዛኝ ሰው ትሆናለህ። ልብህን በበጎ ፈቃድ፣ በጨዋነትና በሰላም ሞልተህ የምትለቅቀው ከሆነ ግን ከሁላችንም በልጠህ ትገኛለህ» ብለው ሲመክሩት መጻም ማግልዋር እራት ተዘጋጅቶ መቅረቡን ተናገረች። ከተሰናዳው ገበታ ላይ ሾርባ፣ ሥጋ፣ የፈረንጅ አይብና ዳቦ ቀርቧል። የሚጠጣ የወይን ጠጅም ነበር። ጳጳሱ ፊት ላይ የደስታና የእርካታ ስሜት እየታየ «እንኳን ደህና መጣህ» በማለት በፈገግታ የተሞላ ገጻቸው ወደ እንግዳው በማዞር «እራት ቀርቧል» አሉት። ከእርሳቸው በስተቀኝ ከነበረው ወንበር ላይ እንዲቀመጥ ጋበዙት። ከእንግዳው ቀጥሎ በስተግራ በኩል መድሚዜል ባፕቲስታን ተቀመጡ። ጳጳሱ ማዕዱን ባርከው ከቀረበው ሾርባ ለራሳቸው አወጡ። ሰውዬው ከቀረበው ምግብ ላይ ተረባረበት።

«ከገዳታ ላይ አንድ ነገር የኑደለ መሰለኝ» አሉ ጳጳሱ በድንገት። ይህንንም ያሉት መጻም ማግልዋር ገበታ ሲያቀርቡ ለጊዜው ያዘጋጁት አስፈላጊ የነበሩትን ሦስት ከብር የተሠሩ ሳህኖችን ብቻ ነበር። የቤቱ ባህል እንግዳ በመጣ ቁጥር ከብር የተሠሩ ስድስቱንም ሳህኖች ከገበታው ጠረጴዛ ላይ መደርደር ሲሆን ይህም ለጉራ ሳይሆን ሌላም እንግዳ ቢመጣ ደስ ይለናል በማለት ችሮታቸውን ለማሳየት ነበር። መጻም ማግልዋር የጳጳሱ አሳብ ስለገባቸው ከመቅጽበት የተቀሩት ከብር የተሠሩ ሳህኖችን አምጥተው ገበታ ከቀረቡ ሰዎች ፊት ለፊት አኖርዋቸው።

ከእራት በኋላ መጻም ማግልዋር ከብር የተሠሩ ሳህኖችን አነሱ። ጳጳሱ እህታቸውን ተሰናብተውና አንድ የሻማ መብራት ለራሳቸው፣ ሌላውን ለእንግዳው ለመስጠት ሁለት የሻማ መብራቶችን ይዘው ተነሱ። ከዚያም «ልጄ ኑሩልህን ሳሳይህ» ሲሉት እንግዳው ተከተላቸው።

ለእንግዳው የተዘጋጀው መኝታ ከጳጳሱ መኝታ ቤት ቀጥሎ ከነበረው ከፍል ውስጥ ነው። እንግዳው ከጳጳሱ መኝታ ክፍል እያሰፈ ሳለ መጻም ማግልዋር እነዚያን የሚያማምሩ የብር ሳህኖች ከጳጳሱ መኝታ ቤት ደገኛ ከነበረው ቡፌ ውስጥ ሲያስቀምጡ ዣን ቫልዣ አያቸው። ዘወትር መጻም ማግልዋር ከመተኛታቸው በፊት ሳህኖችን አጣጥበው ከቡፌ ውስጥ ነው የሚያኖርዋቸው። እንግዳው ከመኝታ ክፍሉ እንደ ገባ መኝታው ሰው ያልተኛበት ነጭ አንሶላ መነጠፉን ተገነዘበ። የተሰጠውን ሻማ አስተካክሉ ክፍሉ ውስጥ ከነበረ አነስተኛ ጠረጴዛ ላይ አስቀመጠው።

ደጉ ጳጳስ «መልካም እንቅልፍ፣ ደህና እደር። ላሞች ሰላሉን ነገ ጠዋት ከመሄድህ በፊት ትኩስ ወተት ጠጥተህ ትሄዳለህ» ሲሉት «አመሰግናለሁ አባታችን» በማለት መለሰላቸው እንግዳው። የምሰጋና ቃሉን እንደ ሰጠ ወዲያው ከመቅጽበት እነዚያ ሁለት ሴቶች ከዚያ ቢኖሩ ውሃ ሊያደርጋቸው ይችል የነበረ ነገር ይናገራል። ጳጳሱን እየተመለከተ ገጽታውን ቀያይሮ በዚያ በሻከረ ድምፁ «አሁን ጥሩ ነው። ከመኝታ ቤትዎ አጠገብ ነው እንድተኛ ያደረጉት። ለመሆኑ በነገሩ አስበውበታል? ኑፍሰ-ገዳይ አለመሆኔን ማነው የነገሮት?» ሲል ጠየቃቸው።

«እግዚአብሔር ያውቃል» ሲሉ በእርጋታ መለሱለት። ከዚያም ምንም ሳይጨነቁና ድምፅ ሳያሰሙ ከራሱ ጋር እንደሚነጋገር ወይም በጥሞና ጸሉት እንደሚያደርስ ሰው ከንፈራቸውን ካነቃነቁና ሰውዬውን ከባረኩ በኋላ በቀጥታ ወደ ክፍላቸው ሂደው ተኙ። ከዚያ ቤት የነበረው ሰው ሁሉ ተኝቶ እንቅልፍ ወሰደው። ዣን ቫልዣ ግን በቶሎ እንቅልፍ ቢወስደውም እኩለ ሌሊት ላይ ነቅቶ እንደገና ተኛ።

ዣን ቫልዣ ገጠሬ ሲሆን የተወለደው ብሬ በመባል ከሚታወቅ ድሃ ቤተሰብ ነው። በልጅነቱ ትምህርት ቤት ገብቶ የመማር እድል ስላላጋጠመው መሐይም ነው። ካደገ በኋላ ከነበረበት አነስተኛ ከተማ ውስጥ በአትክልተኝነት ሥራ ጀመረ።

ዣን ቫልዣ በተፈጥሮው ለሰው አሳቢ እንጂ አዛኝ አልነበረም። ቤተሰቦቹ በልጅነቱ ነው የሞቱበት። እናቱ የሞቱት በሕመም ሲሆን አባቱ ግን ከዛፍ ላይ ወድቆ ነው የሞተው። አባቱም እንደ እርሱ አትክልተኛ ስለነበረ ዛፍ ለመከርከም ከትልቅ ዛፍ ላይ ወጥቶ ይወድቃል። ከቤተሰቡ መካከል በሕይወት የቀረች አንዲት እህት ነበረችው። የሚያሳዝነው የእህቱ ባል ሰባት ልጆች አስታቅፏት ነው እህቱን በሞት የተለያት። ዣን ቫልዣ ሌላ ዘመድ ስላልነበረው እህቱ ነበረች ያሳደገችው። እህቱ ባልዋ ጥሏት እስከ ጠፉ ድረስ ተንከባክባ ነበር የያዘችው። ባልዮው ሲሞት የትልቁ

ልጃቸው እድሜ ስምንት ዓመት ሲሆን የትንሹ ልጅ እድሜ ከአንድ ዓመት በታች ነበር። ጐን ቫልጐ በዚያን ጊዜ 25 ዓመት ሞልቶታል።

ጐን ቫልጐ በተራው የልጆቹን አባት ተክቶ እህቱንና ልጆችዋን ይረዳ ጀመር። የወጣት ዘመኑን ያሳለፈው አዳጋችና አድካሚ ግን ብዙ ገቢ በማያስገኝ ሥራ ላይ ተሰማርቶ ነው። ስለዚህ በጊዜ ማጣትና ድኅነት ምክንያት በአፍላ ዘመኑ የከንፈር ወዳጅ ለመያዝ እንኳን አልቻለም። እንዲያውም ከነአካቴው ለፍቅር የሚሆን ጊዜ አልነበረውም ለማለት ይቻላል። ማታ ማታ እመሻሹ ላይ ከቤቱ ተመልሶ ቃል ሳይናገር ያገኘውን ቀማምሶ ይተኛል። አንዳንድ ቀን እህቱ ልጆችዋ ሲያስቸግሯት ለጐን ቫልጐ ከቀረበው ምስኪን እራት እየቀነሰች ለልጆችዋ ትሰጥበታለች። ይህ ሲሆን በረጅም ፀጉሩ ፊቱን ሸፍኖ የተረፈችውን በዝምታ ይበላል እንጂ ለምን ተወለደብኝ ብሎ አይጨቃጨቅም። ምንም ነገር እንዳልሆነ በመቁጠርና ራሱን በማታለል ኑሮውን ይገፋል። ለነገሩ ምርጫም አልነበረውም።

ዛፎች በሚገረዙበት ወራት በቀን እስከ አስራ ስምንት ሱስ ያገኛል። ጐን ቫልጐ ልክ እንደ ጉራጌዎች ሥራ ሳይመርጥና ሳይጠየፍ ያገኘውን ሥራ ይሠራል። እህቱም እንደዚሁ ያገኘችውን ትሠራለች። ቢሆንም ራሳቸውን ያልቻሉ ሰባት ልጅ ማሳደግ ቀላል አልነበረም። እህትና ወንድም የሚያገኙት ገንዘብ ስለማይበቃቸው ቤተሰቡ ቀስ በቀስ ችግር የሚያሳድደው ቤተሰብ ሆነ። በተለይ የሆነ ዘመን ክረምት እጅግ አስከፊ ይሆንባቸዋል። በጊዜው ጐን ቫልጐ ሥራ ስላልነበረው ቤተሰቡ የሚላስና የሚቀመስ ምግብ ያጣል።

ያን ሰሞን በእስተ-አሑድ ወደ ማታ የዳቦ መጋገሪያ ቤት ባለቤት ሊተኛ ሲል የዳቦ ቤቱ መስታወት ሲሰበር ይሰማል። የባለቤቱ መኖሪያ ቤት ከዚያው ቅጥር ግቢ ውስጥ ስለነበረ በተሰበረው መስታወት በኩል አንድ ሰው እጁን አሾልክ ዳቦ ሲሰርቅ ያያል። ሌባው ዳቦዉን ይዞ ሮጠ። ሌባው መስታወቱን የሰበረው በቡጢ ስለነበር እጁ ይደማል። ስለዚህ ዳቦው የተወሰደው በሌባ ለመሆኑ ሌላ ማስፈጃ አላስፈለገም። ዳቦ ሰራቂው ሌባ ጐን ባልጐ ነበር። ይህ የሆነው በ1975 ዓ.ም. መጨረሻ ገደማ ነው።

ጐን ቫልጐ ዉለማን ተገን አድርጎ የተዘጋ ቤት ሰብሮ ለመስረቅ በመሞከሩ «ወንጀለኛ ነው» ተብሎ ተፈረደበት። የተሰጠው ብያኔ ለአምስት ዓመታት የመርከብ ቀዛፊ ሆኖ በባርነት እንዲሠራ ነበር። የጐን ቫልጐ አንገት በብረት ሰንሰለት ታስሮ ቱሉን ከተባለ ሥፍራ ወደሚገኝ አሰር ቤት ተወሰደ። የተጓዘው በእንስሳ በሚጐተት ጋሪ ስለነበር መንገዱ 27 ቀን ያህል ወሰደ። ከአሰር ቤቱ እንደ ደረሰ ጥብቆ አለበሱት። ያለፈው

ታሪኩ፣ ስሙ እንኳን ሳይቀር፣ ተለወጠ። ከዚያን ቀን ጀምሮ ስሙ ጐን ቫልጐ ሳይሆን ቁጥር 24 ሺህ 601 ሆነ። ጐን ቫልጐ ከሄደ በኋላ እህቱ ምን ሆነች? ሰባት ልጆችዋስ ምን ዋጣቸው? እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ራሱን ያስጨነቀ ሰው የለም። ለነገሩማ ጥቂት ቅርንጫፎች ከትልቅ ዛፍ ተቆርጠው ሲጣሉ ስለቅርንጫፎቹ የሚጨነቅ ማነው?

ጐን ቫልጐ አራተኛ ዓመቱን ሲያገባድድ ከአሰር ቤት አምልጦ ነፃነቱን የማግኘት እድል ያጋጥመዋል። ከአንደዚያ ያለ አስፈሪ ቦታ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ዘወትር እንደሚተባበሩ ሁሉ የእርሱም የሥራ ባልደረቦች ረድተውት አመለጠ። ለሁለት ቀናት ያህል በየጥሻውና እርሻ ውስጥ ተደብቆ ቆየ። ነገር ግን በሦስተኛው ቀን ወደ ማታ የአሰር ቤቱ ጠባቂዎች ያዙት። ለ36 ሰዓታት ያህል እህል የሚባል ነገር ከአፉ ውስጥ አልገባም። እንቅልፍም አልተኛም። ለማምለጥ በመሞከሩ ፍርድ ቤት የአሰራት ዘመኑን በሦስት ዓመት አራዘመበት። የአሰራት ዘመኑ ስምንት ዓመት ሆነ ማለት ነው።

በሰድስተኛው ዓመትም እንደገና ለማምለጥ ሞክሮ ሳይሳካለት ይቀራል። በእለቱ ማታ ስሙ ሲጠራ «አቤት» ሳይል በመቅረቱ ጥሩምባ ተነፍቶ ዘቦች ለፍለጋ ይወጣሉ። በዚያኑ እለት በአካባቢው የነበሩ ሰዎች ከመርከብ ስር ተደብቆ ስላዩት ይዙታል። ያየው ዘበኛ ሊይዘው ሲል ስለተናነቀው ወንጀሉ እጥፍ ሆነ። ዳግም ለማምለጥ በመሞከሩና ዘበኛ በማነቁ አምስት ዓመት ተፈረደበት። ስለዚህ የአሰራቱ ዘመን 13 ዓመት ሆነ። በታሰረ በአሥረኛ ዓመት እንደገና ለማምለጥ ሞክሮ አሁንም ሳይሳካለት ይቀራል። ለዚህም ሙከራው ሦስት ዓመት ተፈረደበት። አሥራ ስድስት ዓመት! በመጨረሻም በአሥራ ስድሰተኛ ዓመቱ ይመስለኛል፤ እንደገና ለማምለጥ ሞክሮ ከአራት ሰዓት በኋላ ስለተያዘ አሁንም አራት ዓመት ተፈረደበት። ከአሥራ ዘጠኝ ዓመት አሰራት በኋላ ግን ለማምለጥ ቻለ።

መርከብ ቀዛፊዎች ከሚታሰሩበት ሲገባ እየተንቀጠቀጠና እያለቀሰ ነበር። ያን ሥፍራ ሲለቅ ግን ልቡ ደንድኖ ነው የወጣው። ከእዚያ ሥፍራ ሲገባ ተሰፋ ቆርጦ ነበር የገባው። ሲወጣ ግን ተስፋቢስ ብቻ ሳይሆን ጨካኝም ሆኖ ነው የወጣው። ታዲያ የዚህ ሰው መጪረሻና የወደፊት ሕይወት ምን ሆኖ ይሆን? ታሪኩን ለማውሳት እንሞክር እስቲ። የሰውዬው ችግር በህብረተሰቡ የተፈጠረ ስለሆነ ይኸው ህብረተሰብ እነዚህን ነገሮች አጢኖ መመልከት ይኖርበታል።

3

ቀደም ሲል እንደ ተነገረው ዣን ቫልዣ አላዋቂ ሰው ነው። ግን ደደብ አይደለም። ሰውዬው በተፈጥሮው ጭምት ነው። ሰንኪላ እድሉ ደግሞ በይበልጥ እንዲጨምት አድርጎታል። ሲገረፍ፣ በሰንሰለት ሲጠፈር፣ ጨለማ ቤት ሲታሰር፣ ሰውነቱ በድካም ብዛት ሲዝል ነገሮችን በጥሞና እንዳያስተውል ሁኔታዎች አስገድደውታል። የሌሊት ቁር ሲያቄራምደው፣ የቀን ፀሐይ ሲያወራጨውና ከእንጨት ላይ ተኝቶ ዘወትር በአሳብ እየዋኘ ከጎሊናው ጋር ሲሟገት የኖረ ሰው ነው። በዚህም እሱነቱን እንደ ፍርድ ቤት ቄጥሮ ምርመራውን እርስ በራሱ ማካሄድ ከጀመረ ቆይቷል። ያለ አግባብ የተቀጣ የዋህና ቀና ሰው አለመሆኑን ዘወትር ጎሊናው ነግሮታል።

ባለፈው ሕይወቱ ሕጉዋጥ ተግባር መፈጸሙን አልካደም። አዛኝ አሠሪ እስኪያገኝ ድረስ መታገስ እንደ ነበረበት ልቦናው ያውቃል። ለእነዚያ የትም በትኖአቸው ለቀረው ምስኪን ልጆችም ይሽው ይበጅ ነበር። ስለዚህ እርሱ የፈጸመው ድርጊት የሞኝ ሰው ሥራ ነው ለማለት ይቻላል። እርቆ ለማየት የማይችል ድሃ 'ዓለምን በጉልበት አሸንፋለሁ' ብሎ ሕይወቱን በዘፈቀደ ቢመራ ወይም 'ችግርን በሊብነት እወጣለሁ' ብሎ ራሱን ቢያታልል ስህተተኛነቱን ገሃድ ያወጣል እንጂ አዋቂ አያሰኘውም።

ታዲያ በዚህ አሳዛኝ ታሪክ ውስጥ የተገለጠው ስህተት የዣን ቫልዣ ብቻ ነው? እንደ እርሱ ያሉ ትጉህ ሠራተኞች ሥራ አጥተው ሲንከራተቱና ቁራሽ ዳቦ እርቋቸው ሲለቃቀ ማየት የሚያሳዝን አይደለም? ስህተት ፈጻሚዎች ጥፋታቸውን ቢያምኑም የሚጣልባቸው ቅጣት የአውሬዎች ብያኔ መሆኑስ አግባብ ነው? ወንጀለኛ ወንጀል ለመሥራት ካለው ፍላጎት ይበልጥ ሕገ-አራዊትን አንተርሶ ቅጣትን የማከረር ባህሪይስ ትክክል ነው? የቅጣት ክብደት ወንጀልን ለማጥፋትና በውጤቱ ሁናቴዎችን ለማሻሻል ሳይሆን የተበጻዮችን ስህተት ለማጉላትና በቸልተኞች ስህተት ለመቀየር፣ ወንጀለኞችን ከሚገባው በላይ ለማሰቃየት፣ አበጻሪን በባለዕዳ ለመለወጥ ከሆነ ይህ ድርጊት ተገቢ ነው ሊባል ይችላል? ዣን ቫልዣ እነዚህን ጥያቄዎች እያሰላሰለ «እውነቱ ቢወጣ ማነው ጥፋተኛ የሚሆነው?» ህብረተሰቡ አንድ ጊዜ በምክንያት ባልተደገፈ ንድየለሽነት፣ በሌላ ጊዜ ርህራሄ በተለየው ዓይን እያየ በአባሎቹ ላይ የመፍረድ ኃይልና ሥልጣን ቢኖረውም ህብረተሰቡ ውስጥ እድል ከሚያፈራው ህብት እጅግ ዝቅተኛ የሆነውን ድርሻ የሚደርሳቸው ምስኪኖችን እጅግ አድርጎ ማሳደድና መጉዳት የጭካኔ ጭካኔ አይሆንም?

ዣን ቫልዣ እነዚህንና ሌሎችንም ጥያቄዎች ዘወትር ራሱን እየጠየቀ በህብረተሰቡ ላይ ፈርዶ የራሱን ብያኔ ይሰጣል። ብያኔው በህብረተሰቡ ላይ

የከረረ ጥላቻን ማሳደር ነበር። በሕይወት ዘመኑ የደረሰበት ፈተናና ስቃይ የህብረተሰቡ ውጤት እንደሆነ አመነ። ስለዚህ ምናልባት አንድ ቀን እድል ቢገጥመው ህብረተሰቡን እንደሚበቀል ለራሱ ቃል ይገባል።

የህብረተሰቡ አባሎች ሕይወቱን አበላሹበት። ከቁጡ ፊታቸው ሌላ ያሳዩት ነገር አልነበረም። ማንም ቢሆን ለመላላጥ ካልሆነ በስተቀር ፍቅር ያሳየው የለም። በሕፃንነቱ ከእናቱና ከእህቱ ከተለየ ጀምሮ ሁሉም ሰው ርህራሄ በተለየው መልኩ ክፉ ተናገረው እንጂ በጥሞናና በሰላም አላነጋገሩትም። ስለዚህ በስቃይ ላይ ስቃይ እየታከለበት በሂደ ቁጥር ሕይወት ጦርነት መሆኑን ሰር በሰደደ መልኩ ተገነዘበ። በጦርነቱም እርሱ እንደ ተሸነፈ አመነ። ይህም ከጥላቻ በስተቀር ሌላ የተሻለ ነገር አሳስተማረውም። እስር ቤት እያለ ይህንኑ ትምህርት ለማጠናከርና ከዚያም ሲወጣ ይዞት እንደሚወጣ ወሰነ። ዣን ቫልዣ በዚህ ሳያበቃ ለስቃዩ ምክንያት የሆነውን ህብረተሰብ ለፍርድ ከማቅረብ አልፎ ህብረተሰብን የፈጠረ አምላክን ጭምር አወገዘ። ቀደም ሲል እንደ ተነገረው ዣን ቫልዣ በተፈጥሮው ክፉ ሰው አልነበረም። ከእስር ቤቱ ሲደርስ ልቡ ቀና ነገር ነበር የሚያስበው። ከእዚያ ውስጥ እያለ ግን ሕብረተሰብን ጠልቶ እርሱም ክፉ ሰው እንደሆነ አመነ።

ከታሰረበት ቱሉን ከተባለ ሥፍራ እንደ እርሱ ያሉ ምስኪኖች የሚማሩበት ትምህርት ቤት ሲከፈት ትምህርት ቤቱን የከፈቱት ራሳቸውን ለሌሎች መስዋዕት በሚያደርጉ ሰዎች ነበር። አንዳንድ ጊዜ ትምህርትና ንቃት ለተንኰልና ለክፋት በር የሚከፍቱ መሆናቸውን ዣን ቫልዣ ቢያውቅም በአርባ ዓመቱ ትምህርት ቤት ገብቶ መጻፍና ማንበብ ተማረ። ይህ ሰው በእነዚያ 19 የስቃይና የባርነት ዓመታት ውስጥ ነፍሱ አንድ ጊዜ እየሞተና በሌላ ጊዜ ሕይወት እየዘራ ነበር የኖረው። የሕይወቱ ግድግዳ በአንድ በኩል ብርሃን ሲገባው በሌላ በኩል ጨለማ ቦርቡሮበታል። ለማንኛውም አንድ መዘንጋት የሌለበት ነገር አለ። ይኸውም ዣን ቫልዣ ቱሉን እስር ቤት ውስጥ ከነበሩት ሰዎች ሁሉ በአካል ጥንካሬና ጉልበት እጅግ የላቀ እንደ ነበር ነው። ከባድ ሥራ በመሥራት፣ ጠንካራ የሆነ ሽቦ በመጠምዘዝና ክብደት ያለውን ነገር በማንሳት የአራት ሰዎች ጉልበት አይስተካከለውም። አንድ ጊዜ የቤት ጥገና ሥራ እየተካሄደ ሳለ ተንጠልጣይ ግንቡን ደግፎ የያዘው ብረት ሾልኮ ቤቱ ሊፈርስ ሲል በአጋጣሚ ከዚያ የነበረው ዣን ቫልዣ ሰዎች እስኪደርሱለት ግንቡን ብቻውን ደግፎ በማቆሙ ከዚያ የነበረ ሰው ሁሉ በጣም ተገርሟል። ቅልጥፍናውና የሰውነቱ መታዘዝም ጉልበቱን የሚያስንቅ እንጂ የሚያንስ አልነበረም።

የወንጀለኞች የዘወትር ሕልምና ምኞት ከእስር ለማምለጥ የሚያስችል እቅድ ማውጣት ሲሆን ይህም አንዳንድ ጊዜ ጉልበት ከችሎታ ጋር ይለጣቸዋል። በአለቀፍና በዝንቦች እየቀኑ የሚኖሩት እስረኞች እንደነርሱ መብረር ይፈልጋሉ። ዣን ቫልዣም የዚህ ዓይነቱ ቅናት ስላደረበት የሚይኖክረው ነገር አልነበረም። ከማዕዘንና ከቋጥኝ ላይ እየዳኸ መውጣት፣ በጀርባ መንሸራተት፣ ከረጅም ከፍታ መዝለልና የመሳሰሉትን መፈጸም የነውዬው የእለት ተእለት ተግባር ነበሩ። አንዳንድ ጊዜ እርሱ የሚሠራቸው እንደነርሱ ቀን እንዴት ብሎ እንደ ወጣ ሳይታወቅ ከፎቅ ቤት ጣራ ላይ ወጥቶ ይታያል።

ዣን ቫልዣ ብዙ አይናገርም። ዘወትር መኰሳተርን ስለሚያበዛ ጥርሱን አሳይቶ አያውቅም። የእስረኞች የጭንቀት ድምፅ ስሜቱን ይነካው እንደሆነ እንጂ ከዚህ ሌላ ስሜቱን የሚቀሰቅስበት ነገር የለም። አጢኖ የተመለከተው ሁሉ ዘወትር በአስፈሪ የአሳብ ባሕር የተዋጠ ለመሆኑ ከፊቱ ላይ ለማንበብ ይችላል። ዣን ቫልዣ ሁልጊዜም ብቅ ጥልቅ በሚልና ባልተጋላ ሕይወት ታፍኖ በተያዘ እውቀት አማካይነት በጭላንጭል ለማየት የሚሞክር ግዙፍ አካል እንደ ተጫነው ይሰማዋል። ስለዚህ ከዚያ ይቅርታቢስና አስፈሪ ሆኖ ከተጫነው ነገር ለማምለጥ አንገቱን ቀና አድርጎ ዓይኖቹን ለመግለጥ ሲሞክር ሥልጣኔ ብለን የምንጠራው ነገር ያስኛቸው መልክም ነገሮች፣ ሕጎች፣ አስከፊ የሰው ገጽታዎችና ሥራቸው ተከማችተውና ከቁጣና ከሩርሃት ጋር ተደባልቀው በአሳብ ይመጡበታል። ሆኖም እነዚህ ነገሮች ቀስ እያሉ ከእርሱ እየራቁና ለሻቅበው ወደ ላይ ሲወጡ፣ ከፊቱም ሲሰወሩ ይመለከታቸዋል።

ዣን ቫልዣ በዚህ ዓይነት ተጨባጩ ዓለም ውስጥ እየኖረ አስፈሪ በሆኑ መናፍስት ተሞልቶና እነዚያም አስፈሪ መናፍስት እውን ሆነውና እነሱ ውስጥ ሰርጸው ገብተው እያሰቃዩት የኖረ ሰው ነው። እስር ቤት ውስጥ እያለ አንዳንድ ቀን ድንገት ሥራውን አቁሞ ያስባል፣ ይተክዛል፣ ይቁዘማል። ቀደም ሲል የነበረው፣ ከበስተጓላ የዋገቀው የማመዛዘን ችሎታው ጨርሶ ጠፍቶ በእርሱ ላይ የደረሰው ነገር ሁሉ ከሥነሥርዓት ውጪ በሆነ መልኩ የተፈጸመና በአካባቢው የሚያየው ነገርም ያልሆነና የማይሆን ነገር እንደሆነ አድርጎ ይቁጥረዋል። ብቻውን ሲሆን «ይኼ የገጠመኝ ነገር ሁሉ ሕልም ነው» እያለ ለራሱ ይነጋገራል። አንድ ቀን ከእርሱ ጥቂት ርቆ የቆመውን የእስር ቤቱ ኃላፊ አተኩሮ ባየው ጊዜ ያ ሰው መንፈስ እንጂ የእውነት ሰው አልመሰለውም። ሆኖም መንፈስ መሰሉ የታየው ፍጡር በድንገት ወደ እርሱ መጥቶ በዱላ ይጠልዘዋል።

ለዣን ቫልዣ የምናየው ዓለም ከእውነተኛነት የራቀ አጠራጣሪ ዓለም ሲሆን ከነአካቴው ለእርሱ «ወሐይ የለችም፣ ከረምትና በጋ አይፈራረቁም፣ ጠፈር የሚባል ነገርም የለም» ብሎ ያምናል ብንል ከእውነት አንርቅም። ለእርሱ የሁሉም ነገር መጀመሪያና መጨረሻ የሰው ልጅ ያወጣው ሕግና ሕግ አውጪውን ሰው መጥላት ነው። በዚህም ምክንያት ማን፣ ምን ላይባል በሕይወት ያለን ፍጡር ሁሉ ማጥፋት የዘወትር ምኞቱ ሆነ።

የዚህ ዓይነቱ ጥላቻ በመለኮት ኃይል ካልተገታ በስተቀር እጅግ አደገኛ የሆነ ሁናቴን ይፈጥራል። በዚህም ዣን ቫልዣን «እጅግ አደገኛ ሰው» ብሎ መናገሩ ስህተት አይሆንም። ይህ ሰው ከዓመት ዓመት ቀስ እያለ በሚያስፈራ መልኩ ልቡ እየደነደነና እየጨከነ ሄደ። ይህን ደንዳና ፍጡር አተኩረው ሲመለከቱት የደረቀ ዓይን እንዳለው ለመገንዘብ ይቻላል። ዣን ቫልዣ እስር ቤት ውስጥ ለአሥራ ዘጠኝ ዓመት ሲታሰር አንድም ቀን እምባ አውጥቶ ሲያለቅስ አልታየም።

4

ከቤተክርስቲያን አናት ላይ የተሰቀለው ግዙፍ ሰዓት ስምንት ሰዓት ሆኖ ሲደውል ዣን ቫልዣ ከእንቅልፉ ይነቃል። ጥሩ እንቅልፍ ወስዶት ከአራት ሰዓት በላይ ተኝቷል። ጥሩ እንቅልፍ ስለተኛም ድካሙ ሁሉ ተወግዶለታል። ከዚያ በፊት ለዚህን ያህል ጊዜ እረፍት አግኝቶ አያውቅም። በእካባቢው ከሰፈነው ጨለማ ዘልቆና ዓይኑን ገልጦ ለማየት ሞከረ። ለማየት ስላልቻል እንቅልፍ እንደገና እንዲወስደው ዓይኖቹን ጨፈነ። አእምሮ ቀኑን በሙሉ በተለያዩ ነገሮች ከተበጠበጠና የተለያዩ ነገሮች ከተመላለሱበት እንድ ጊዜ እንጂ ዳግመኛ ለመተኛትና እንቅልፍ ሊወስድ እንደማይችል ሁሉ ዣን ቫልዣንም ዳግም እንቅልፍ ሊወስደው አልቻለም። እንቅልፍ መጀመሪያ ሲመጣ ብዙ ያዳፋል። ያ እንቅልፍ ካለፈ ግን ቢለማመጡት እንኳን በዓይን አይዞርም። ስለዚህ ዣን ቫልዣም እንደገና እንቅልፍ ሊወስደው ስላልቻለ ብዙ በማሰብ ቈዘመ። ብዙ ዓይነት አሳብም ኮነሲናው ውስጥ ተፈራረቀ። ከጭንቅላቱ ውስጥ ከገቡት አሳቦች መካከል ብዙዎቹን አራግፎ ሊጥላቸው አንዱ አሳብ ግን እየተመላለሰ አስቸገረው።

እነዚያ መዳም ማግልዋር ከጠረጴዛው ላይ የደረደረቻቸው የሚያማምሩ ከብር የተሠሩ ስድስት ሳህኖችና ትልቁ የብር ጭልፋ በዓይኑ እየዞሩ እረፍት አሳጡት። ዳግም በዓይነ-ኅሊናው ሲያያቸው በጣም ወደዳቸው። ከጳጳሱ መኝታ ቤት ከአልጋቸው ራስጌ በኩል ካለው ቡፌ ውስጥ ሴትዮዋ

ሲታሰቀምጣቸው እይቷል። ከብር የተሠሩ ጥንታዊ ቅርሶች በመሆናቸው ከሞልፋው ጋር እስከ 200 ፍራንክ እንደሚያወጡ ልቦናው ነገረው።

ጎሊናው ከወዲህ ወዲያ እየዋለለ አንድ ሰዓት አለፈ። በአሳብ እየዋተቱ አንድ ሰዓት ማሳለፍ፣ ያውም ሌሊት በጨለማ፣ ምን ያህል ረጅም ጊዜ እንደሆነ የደረሰበት ያውቀዋል። ዘጠኝ ሰዓት ለመሆኑ የቤተክርስቲያኑ ደወል ነገረው። ዣን ቫልዣ ዓይኑን በድንገት ገልጦ ከአልጋው ዘልሉ ወረደ። ስልቻውን በዳስሳ ፈለገና በእጁ እንደ ያዘው ከአልጋው ጠርዝ ቁጭ አለ። ሳይታወቀው ብዙ ተቀመጠ። የቤተክርስቲያኑ ሰዓት በየአሥራ አምስት ደቂቃና ግማሽ ሰዓት ደወል እየደወለ ባይቀስቅሰውማ እስኪነጋ ድረስ ከዚያው በተቀመጠ። ደወሉ «አይዞህ፣ በርታ» የሚለው መሰለው። ተነስቶ ቆመ። ለመራመድ ግን አመነታ። እንደ ምንም ብሎ አንድ እርምጃ ወደፊት ተራምዶ የሚሰማ ድምፅ ካለ በጥሞና አዳመጠ። ሁሉም ነገር ጸጥ ብሏል። ቀስ ብሎ በጥንቃቄ እየተራመደ ወደ መስኮቱ ሄደ።

ሌሊቱ ጥቅጥቅ ባለ ጨለማ የተዋጠ አልነበረም። ጨረቃዋ በሩቁ ትታያለች። ሆኖም ደመና ዙሮባታል። ጨረቃዋን ደመና በጋረዳት ቁጥር ዣን ቫልዣ የነበረበት ክፍል ትንሽ ይጨልማል። ከክፍሉ ውጪ የነበረው አካባቢ በጉልህ ሲታይ እርሱ የነበረበት ክፍል ግን የደበዘዘ ነበር። መስኮቱ አጠገብ ደርሶ መስኮቱን ሲያጠነው በቀላሉ ሊከፈት እንደሚችል አወቀ። መስኮቱን ከፈተው። ሆኖም ከባድ የሆነ ብርድ በመስኮት በኩል ገብቶ ሰላቀዘቀዘው መስኮቱን መልሶ ዘጋው። መስኮቱ የመሰታውት ስለነበር እንደ ተዘጋ ግቢውን በዓይኑ ሲቃኝ ግቢው በእነስተኛ ግምብ መከለሉን ተመለከተ። ከግምቡ ውጭ ረጃጅም ዛፎች ይታያሉ። በሁለቱ ዛፎች መካከል ያለውን ርቀት ሲያጤን ርቀታቸው ተመሳሳይ ስለሆነ ምናልባት ግዘጋኝ ቤቱ የተከላቸው ዛፎች መሆናቸውን በመገመት «ከአጥሩ ውጪ ያለው ሥፍራ አውራ ጐዳና መሆን አለበት» ሲል ደመደመ።

ከውሳኔ አሳብ ላይ እንደ ደረሰ በቆራጥነት ወደ አልጋው ተመለሰ። ከጀያም አቆማዳውን ከፍቶ ከውስጡ የሆነ ነገር ፈለገ። አንድ ነገር አውጥቶ ከአልጋው ላይ አስቀመጠ። ሚማውን ኪሱ ውስጥ ከተተ። አልጋው ላይ ያስቀመጠው እቃ ሌላ ቀሪዎቹን እቃዎች አሰሮ ትከሻው ላይ አኖራቸው። ቁልቁን አጠለቀና ዱላውን አነሳ። ያሰረውን እቃ መልሶ ከመስኮቱ ሰር አስቀመጠው። ወደ አልጋው ተመልሶ ከአልጋው ላይ ያኖረውን እቃ አነሳ። እንዳቱ የያዘው እቃ በአንድ ፊቱ እንደ ጠር የሾለ ሚፍ ሲኖረው በሌላው ሚፉ ጫር መሳይ ነገር ያለው ውፍራም ብረት ሲሆን በዚያ ውድቅት ጨለማ ብረቴን ለምን ሥራ እንዳዘጋጀው ለመለየት አስቸጋሪ ነበር።

ጹላ ነው ወይስ የእቃ ማንሻ? አይታወቅም። ቀን ቢሆን እንኳን የማዕድን ሠራተኛ መቆፈሪያ ነው ለማለት ይቻል ነበር። በወቅቱ ቱሉን ከተባለ አካባቢ በሚገኙ ኮረብታዎች ላይ ድንጋይ እንዲፈልጡ የተፈረደባቸው ወንጀለኞች ይቀጠሩ ነበር። ብዙውን ጊዜ ወንጀለኞቹ አሁን የተገለጠው መሣሪያ ዓይነት የድንጋይ መፍለጫ እንደሚይዙ ይታወቃል።

ዣን ቫልዣ ያን ብረት በቀኝ እጁ ያዘ። ትንፋሹን ውጦ በዝግታ በመራመድ ወደ ጳጳሱ መኝታ ክፍል አመራ። ከመኝታ ቤታቸው አጠገብ ሲደርስ በሩ አለመቀርቀሩን ተገነዘበ። 'አባታችን በራቸውን ሳይቆልፉ ነው የሚተኙት' አለ በልቡ። ቀጥሎም ጆሮውን አቅንቶ አዳመጠ። ድምፅ የሚሉት ነገር የለም። ሲፈራ ሲቸር በሩን ከፈት አድርጎ በጣቶቹ ሚፍ ቀስ ብሎ ገፋው። ያደረገው ጥንቃቄ ከድመት ጥንቃቄ ይበልጣል። በሩ ምንም ዓይነት ድምፅ ሳያሰማና ለመንቀሳቀሱ እንኳን በሚያጠራጥር መልኩ በዝግታ በመከፈቱ ከመጀመሪያው ይበልጥ በጥቂቱ ተከፈተ።

ለአጭር ጊዜ ከበሩ አጠገብ ቆም አለ። አሁን ግን ድፍረቱና ፍላጎቱ በይበልጥ ስለተሰባሰበለት ከቀድሞ በበለጠ ጉልበት በሩን ገፋ አደረገው። በዚህ ጊዜ የበሩ ማያያዣ የዛገ ብረት ረዘም ያለ የሚሰቀጥጥ ድምፅ አሰማ። ልቡ የተሰነጠቀ መሰለው። ህውልት ይመስል ከቆመበት እንደ እንጨት ደርቆ ሳይንቀሳቀስ ተገትሮ ቀረ። ለመንቀሳቀስ አቅም አነሰው፤ ድፍረትም አልነበረውም። ጥቂት ደቂቃዎች አለፉ። በሩ ወለል ብሎ ተከፍቶ ስለነበር ወደ ውስጥ ተመለከተ። የተንቀሳቀሰ ነገር የለም። አዳመጠ፣ የሚንቀሳቀስ ነገር ከዓይኑ፣ የሚጮህ ድምፅ ከጆሮው አልደረሰም። የበሩ አሰቃቂ ድምፅ ግንኑም አልቀሰቀሰም። ስለዚህ የመጀመሪያው አደጋ አለፈ ማለት ነው። ልቡ ግን በጣም ፈርቷል። ሆኖም ያሰበውን ላለመፈጸም አሳወላወለም። የተመኘውን በቶሎ ለመጨረስ ቈረጠ። አንድ እርምጃ ወደፊት በመራመድ ከክፍሉ ውስጥ ገባ። ክፍል ውስጥ ጸጥታ ሰፍኗል። ከወንበርና ከጠረጴዛ ጋር እንዳይጋጭ አሁንም በጥንቃቄ ተራመደ። ከክፍሉ ውስጥ ጳጳሱ ጥግ ይዘው ተኝተው በኃይል ሲተነፍሱ ሰማ። ከአልጋቸው አጠገብ ሲደርስ ከሰበረበት ቆም አለ። ከአሰበበት በቶሎ የደረሰም መሰለው።

አንዳንድ ጊዜ የምንሠራውን ሥራ ለመደገፍና ለማራገብ ተፈጥሮ ከእኛ ጋር ታብራለች። ለግማሽ ሰዓት ያህል ከባድ ደመና ጨረቃዋን በመጋረድዋ አካባቢው ጨልሞ ነበር። አሁን ግን ልክ እንደ ተማከረ ሰው ዣን ቫልዣ ከጳጳሱ አልጋ አጠገብ እንደ ቆመ ደመናዋ ለጨረቃ ቦታዋን ለቀቀች። የጨረቃ ብርሃን በመስኮት በኩል ገብቶ ከጳጳሱ የገረጣ ፊት ላይ አረፈ። እንቅልፍ ጭልጥ አድርጎ ወስዷቸዋል። የሌሊቱ ብርድ ከባድ ስለነበር ወፈር

ያለ ልብስ ለብሰውና በጀርባቸው ተዘርረው ነው የተኙት። ስንቱን ደግ ሥራ ቢታማኝነት የሠራውና ነዳያን የሳሙት አንደኛው እጃቸው ካልጋው ጠርዝ አልፎ ወደ መሬት ተንጠልጥሏል። ሌላው እጃቸው ከደረታቸው ላይ በማረፉ የጽድስና ቀለበታቸው እንደ ንጋት ኮከብ ያበራል። ጳጳሱ ከዚያ ተኝተው ሲያይዋቸው መላ አካላቸው የተሰፋ፣ የደስታና የእርካታ ግጎደር እንደሆነ ይናገራል። በቃላት ለመግለጽ የሚያዳግት፣ ግን ከወዲት እንደ መጣ የማይታወቅ ብርሃን ከግንባራቸው ላይ አርፎ እንደ ፀሐይ አበራ፣ የሚምበገበግም መሰለ።

የጨረቃዋ ከሰማይ ላይ መንጣለል፣ የምድር በከፊል የተኛች መምሰል፣ የግቢው እርጭ ማለትና የከፍሉ ፀጥታ እኚህ መለኮት የቀረባቸውን ሰው 'እከብራቸው እንጂ አትደፈራቸው' የሚያሰኝ እንደ ነበር የሚጠራጠሩት አይደለም። ዓይናቸውን ጨፍነው እንደ ተኙ የነበራቸው ግርማ ሞገስ እንዲሁም የተስፋ ምንጭ የሆነውና በጨርቅ ያልተሸፈነው ግንባራቸው አተኩረው ሲመለከቱት በፍርሃት ያርበደብዳል። በዚህም የተነሳ ዣን ቫልዣ በፍርሃት ተውጠና ሐውልት መስሎ፣ ያንን ባለቋሩን ብረት በእጁ ይዞ ከእኚህ ደግ ሰው ፊት ድምፅ ሳያሰማ ቆመ። በሕይወት ዘመኑ እንደዚያ ያለ አጋጣሚ ደርሶበት አያውቅም። የገጠመው ነገር አዲስ በመሆኑም የበለጠና የከፉ ፍርሃት አሳደረበት። የተብከነከነና የተቅበጠበጠ ጎሊና ያሰበውን ከፉ ተግባር ለመፈጸም ከዚያ ቆሞ ሳለ ንጹሁ ነፍስ እንቅልፍ ወሰዶት ከዚያ ተኝቷል።

ዣን ቫልዣ ከዚያው ከነበረበት ቆሞ አካባቢውን ካጤነና ጥቂት ካሰላሰለ በኋላ ቆቡን አውልቆ በግራ እጁ ያዘ። የብረት ዱላውን በቀኝ እጁ እንደ ያዘ ነው። ጳጳሱ ግን አሁንም ኩተኙበት አልተነቃነቁም። ዣን ባልዣ ቆቡን መልሶ በችኮላ አጠለቀው። ከዚያም ወደ ጳጳሱ ሳያይ ከአልጋቸው አጠገብ በግለፍ ቡፈው ወደ ነበረበት ሄደ። የቡፈው ቁልፍ አሳዩ ላይ ስለነበር የቡፈውን በር ከፈተ። በመጀመሪያ ያየው እነዚያ ከብር የተሠሩና የሚያማምሩ ሳህኖችን ስለነበር ሳህኖቹን ከነጭልፋው ይዞ ወደ በሩ አመራ። የእግሬ ኮቴ ይሰማል በሚል ብዙም ሳይጨነቅ በፍጥነት እየተራመደ ከከፍሉ ውጣ። የሰረቀውን እቃ ከአቁማዳው ውስጥ ከተታቸው። ከዚያም ከቪቴ ወጥቶና በአትክልቱ መካከል አቋርጠ ሄዶ አጥሩን በመዝለል ኮንቢው ከወጣ በኋላ መንገዱን ቀጠለ።

ፀሐይዋ እንደ ወጣች ጳጳሱ በጠዋቱ ከአትክልት ውስጥ ይንሸረሸራሉ። መጻም ማግልዋር እየሮጡ እርሳቸው ከነበሩበት መጥተው «አባታችን፣ ሰውዬው ሄዷል! የብር ሳህኖቻችንም ተሰርቀዋል» አሉ። ሴትዮዋ ይህን ሲናገሩ ከአትክልቱ መሃል የጫማ ኮቴ ተመለከቱ። ኮቴውን ተከትለው ግምቡን ሲያዩ የአጥሩ ድንጋይ በአንድ በኩል መሸረፉን ተገነዘቡ። ይህን ጊዜ «አባታችን አዩ፣ በዚያ በኩል ነው የወጣው። ምን ዓይነት ቀበኛ ሰው ነው፣ ሳህኖቻችንን ሰርቆ ይሂድ» አሉ በመቄጨት። ጳጳሱ ለተወሰነ ጊዜ ዝም አሉ። ከዚያም አንገታቸውን ቀና አድርገው ሴትዮዋን እየተመለከቱ «ጥንትም ቢሆን እኮ ሳህኖቹ የእኛ ነበሩ እንዴ?» ብለው ሲጠይቁ መጻም ማግልዋር መልስ አልሰጡም። ለጥያቄያቸው መልስ ስላላገኙ ጳጳሱ ንግግራቸውን ቀጠሉ።

«መጻም ማግልዋር፣ ሳህኖቹ የነዳያን ሀብት ሆነው ሳለ እኛ ያላግባብ ለረጅም ጊዜ አስቀመጥናቸው። ይህ ሰው ማነው? ከነዳያን አንዱ መሆኑን አትርሺ» ሲልዋቸው «ይገርማል፣ እኔም ሆንኩ እህትዎ ግድ የለንም። ሴቶች እንደ መሆናችን መጠን ለእኛ ለውጥ አያመጣም። ለብፁዕነትዎ ገበታ ሲቀርብ ግን በየትኛው ሳህን ሊቀርብ ነው!» ሲሉ አጉረመረሙ።

ጳጳሱ በመገረም ሴትዮዋን አተኩረው እየተመለከቱ «እንዴት እኮ! የቆርቆሮ ሳህን ቢሆን እንኳን ይበቃል። ለመሆኑ ሌላ ሳህን የለንም?» ብለው ሲጠይቋቸው መጻም ማግልዋር አንገታቸውን ነቀነቁ። «ለማንኛውም «የቆርቆሮ ሳህን እኮ ሽታ ያመጣል» በማለት አሳብ ሲያቀርቡ «እንግዲያውስ ከብረት የተሠራ ሳህን ካለ እርሱ ሊሆን ይችላል» አልዋቸው።

መጻም ማግልዋር ፈገግ ብለው «እርሱስ ቢሆን ብረት፣ ብረት ማለቱ ይቀራል!» በማለት ሲናገሩ «እንግዲያውማ» አሉ ብፁዕነታቸው፣ «የእንጨት ወይም የሸክላ ሳህን መፈለግ ነዋ!» ሁለቱ ከተወያዩ ጥቂት ጊዜ በኋላ ባለፈው ሌሊት ዣን ቫልዣ አብሮ ከቀረበበት ጠረጴዛ ላይ ቁርስ ተዘጋጀ። ቁርስ እየበሉ ሳለ ምንም ዓይነት አስተያየት ላልሰጡት እህታቸውና ለሚያኑረመርሙት ለመጻም ማግልዋር ሻይ ውስጥ ጸቦ ነክሮ ለመብላት ማንኪያ ወይም ሹካ የማያስፈልግ መሆኑን በመግለጽ ሳቅ አሉ። ጳጳሱ ስለሰጡት አስተያየት እህትና ወንድም ሲተያዩ በር ተንኳኳ።

ጳጳሱ «ይግቡ» ባሉ ጊዜ በሩ ተከፈተ። ለዓይን የሚያስፈሩና ለቢቱ እንግዳ የሆኑ ሦስት ሰዎች ገቡ። ሦስቱ ሰዎች የአራተኛውን ሰው አንገት ጫምደደው ይዘዋል። ሦስቱ ፖሊሶች ሲሆኑ አራተኛው ሰው ዣን

ቫልዣ ነበር:: የፖሊሶቹ አዛዥ ወደፊት ተራምዶ በወታደር ደምብ ላፋፏሱ የከብር ሰላምታ ሰጥቶ «ብዑዕነትየ..» ሲል እስከዚያች ደቂቃ ድረስ አኩርፎና ድምፅ ሳያሰማ ዝም ያለውና አቀርቅሮ የቀረው ዣን ባልዣ ያዛዡን ንግግር አቋርጠ ጣልቃ በመግባት ሃፍረት እየተሰማው አንገቱን ቀና አደረገና «አባታችን፣ የደብሩ አለቃ ብቻ አይደሉማ!» አለ::

«ዝም በል» አለ ፖሊሱ በመጮህ:: «ብዑዕ አባታችን እኮ ናቸው:: የብዑዕነታቸውን ማዕረግ እንኳን አታውቅም?» ብሎ ዣን ቫልዣን ሲጠ ይቀው ብዑዕነታቸው እድሜያቸው በፈቀደላቸው ፍጥነት ከገበታው በቶሎ ተነስተው ወደ ሰዎቹ ጠጋ አሉና «መጣሃ» ሲሉ ተናገሩ ወደ ዣን ቫልዣ እያዩ:: «እንደገና በመገናኘታችን እጅግ በጣም ነው ደስ ያለኝ:: ግን እኮ የሻማ ግብሪያዎቹንም ሞምር ሰጥቼህ አልነበረም እንዴ? ምነው ትተሃቸው ሄድክ? እነርሱም እኮ ከንጹህ ብር የተሠሩ ስለሆኑ ብትሸጣቸው እስከ 200 ፍራንክ ያስገኙልሃል:: ከነህኖቹ ነጥለህ ለምን እነርሱን አስቀረህ?» በማለት ሲጠይቁት ዣን ቫልዣ ግራ ስለተጋባ አፉን ከፍቶ ብዑዕነታቸውን አፍጥጦ ተመለከተ:: የሚሰማው ነገር እውነት ለመሆኑ ማመን አቃተው::

«አባታችን» አለ አዛዡ፣ «እንግዲያውስ ይህ ሰው ያለው ትክክል ነዋ! እኛ ስንይዘው እንደ ገመትነው የሚሸሽ ሰው መስሎን በጥርጣሬ ያዝነው:: እነዚህን የመሰሉ የብር እቃዎች መያዙ ደግሞ በይበልጥ አጠራጠረን::»

«እና ተነጋገራችኋላ!» አሉ ብዑዕነታቸው የሞቀ ፈገግታ እያሳዩ:: «ብትናንትው ቀን ሌሊቱን ለማላለፍ ካስጠጉት ሽማግሌ የተሰጠው እቃ ለመሆኑ ገልጸላችኋላ! እናንተ ግን በመጠራጠር ያዛችሁት:: ወደ እኔም ይዛችሁት መጣቹ:: ተሳስታችኋል፣ እቃዎቹ የራሱ ናቸው::»

«ጉዳዩ ይህ ከሆነማ ሰውዬውን በነፃ ልንለቅቀው እንችላለና!» ብሎ አዛዡ ሲናገር «ያለ ጥርጥር» ሲሉ ብዑዕነታቸው መለሱለት:: በዚህ ጊዜ ፖሊሶቹ ዣን ቫልዣን በነፃ ለቀቁት:: እርሱ ግን ወደ ኋላ በማፈግፈግ «አሁን በእርግጥ በነፃ ሊለቁኝ ነው?» ሲል እጅግ በጣም ዝቅተኛ በሆነ ድምፅ ራሱን ጠየቀ:: ቅዠት እንጂ በውን የሆነ ነገር አልመሰለውም:: «ሰው የለም እንዳይባል ሰው አለ:: እንዴት ያለ ግራ የሚያጋባ ነገር ነው!» ሲልም የሆነውን ለመቀበልና ለማመን ነበደው::

«ልትሄድ ትችላለህ፣ ነገር አይገባህም? ሂድ እኮ ነው የምልህ» እያለ የፖሊሱ አዛዥ ሲናገር «ወዳጄ፣ ከመሄድህ በፊት እነዚያን የሻማ ግብሪያዎችም የእንተ ሰለሆኑ ውሰዳቸው» አሉት ብዑዕነታቸው:: ከዚያም ያን ጻዲ ወደ ምንብ ጠረጴዛው ሂደው የሻማ ማብሪያዎቹን አምጥተው

ለዣን ቫልዣ ሰጡት:: ሁለቱ ሴቶች በእጅጉ ተገርመው ከእዚያው ከገበታ ጠረጴዛ አካባቢ አቀርቅረው ቀሩ፣ ቃል አልተነፈሱም:: ዣን ቫልዣ ሰውነቱ ርድዖ ቀጥ ብሎ ሰመቆም አቅም አጣ:: እንደ ምንም ብሎ የሻማ ማብሪያዎቹን ሲቀበል ፊቱ የአውሬ እንጂ የሰው አልመሰለም::

«አሁን» አሉ ብዑዕነታቸው፣ «በሰላም መሄድ ትችላለህ::» ከዚያም ፊታቸውን ወደ ፖሊሶቹ አዙረው «ልጆቼ፣ ወደ ሥራችሁ ተመለሱ» ሲልዋቸው ፖሊሶቹ ከእዚያ ወጥተው ሄዱ::

ዣን ቫልዣ ራሱን ስቶ ከመሬት እንደሚዘረር ሰው ተንገዳገደ፣ ግን አልወደቀም:: ጻዲሱ ወደ እርሱ ጠጋ ብለው ዝቅ ባለ ድምፅ ቀጥሎ ያለውን ነገሩት::

«አትርሳ፣ 'እቃዎቹን ሽጬ የማገኘው ገንዘብ እውነተኛና ታማኝ ሰው ለመሆን እጠቀምበታለሁ' ብለህ ቃል የገባህልኝን እስከ እድሜ ልክህ እንዳትዘነጋው::» ዣን ቫልዣ መቼ ቃል እንደ ገባላቸው ማስታወስ አቅቶት በመደናገር ከነበረበት ዝም ብሎ ቆመ::

ጻዲሱ «ቃል የገባኸውን እንዳትረሳ» በማለት በድጋሚ አጥብቀው አሳሰቡት:: ቀጥለውም «የእኔ ልጅ ዣን ቫልዣ፣ ከእንግዲህ አንተ ለአሳፊውና ለጠፊው ዓለም ሳይሆን ለደግነት የተመረጥክ ሰው ነህ:: ነፍስህን ነው የምገዛልህ:: የአንተን ነፍስ የምሰጠው የሁሉም ጌታና የበላይ ለሆነው ለአንድ አምላክ ነው::»

ዣን ቫልዣ አገር ጥሎ እንደሚሸሽ ሰው 'እግሬ አውጪኝ' እያለ በመሮጥ ከእዚያ ወጥቶ ሄደ:: ብዙም ሳይቆይ ከተማውንም ለቅቆ ወጣ:: ከገጠር መንደር እስከ ደረሰ ድረስ የሚጠራውን ሰው ሳያውቅ እየተጣራ ብዙ ተጓዘ:: ወዴት እንደሚሄድም ሳያውቅ መንገዱ እንደ መራው ጉዞውን ቀጠለ:: ከነጋ ጀምሮ እህል የሚባል ነገር አልቀመሰም:: ሆኖም ግን የረሃብ ስሜት አልተሰማውም:: ቁጣ ቁጣ ብሎታል:: በማን ላይ ወይም በምን ምክንያት እንደ ተቆጣ ግን ራሱም አላወቀውም::

«የሚቀጥለው ገጠመኝ ምን ይሆን?» እያለ ሲያስብ የገጠሩን አየርና የልጅነት ጊዜውን አስታወሰ:: የልጅነት ሕይወቱን መለስ ብሎ ካየ በጣም ቆይቷል:: ብዙ፣ እጅግ በጣም ብዙና የተለያዩ አሳቦች ከጭንቅላቱ ውስጥ ተፈራረቁበት:: ሆኖም ነፍስ እንደሚያወዛውዘው ቅጠል እየተወዛወዘ መንገዱን ቀጠለ::

6

ፀሐይ እሽቄልቋላ ከአድማስ ውስጥ ልትገባ ስትል ዣን ቫልዣ ጥቅጥቅ ካለ ጫካ ውስጥ ከሆነ ጉብታ መሬት ላይ ቁጭ ብሏል። የአልፕስ ተራራ በሩቁ ይታያል። ከጫካው ወጣ እንዳለ ቀጭን የእግር መንገድ አጋጥሞት ከመንገዱ ዳር ቁጭ ብሎ ሲያሰላስል ደስ የሚል ድምፅ ይሰማል። ድምፁ ወደ መጣበት አቅጣጫ ፊቱን ሲያዞር አሥራ ሁለት ዓመት ገደማ የሚሆነው ልጅ የቦነ ዜማ እያዜመ ወደ እርሱ ሲመጣ ተመለከተ። ልጁ ሳጥን መሳይ ነገር ተሸክሟል። ወደፊት ጥቂት ተራምዶ ቆም አለ። ከዚያም በእጁ የያዘውን ሳንቲም ወደ ሰማይ እያሳነ ይጫወት ጀመር። የልጁ ሀብት ምናልባትም ያቺ ነጭ ሽሊንግ ብቻ ሳትሆን አልቀረችም።

ልጁ ጨዋታውን አቁሞ ዣን ቫልዣ ከተቀመጠበት ሲደርስ የሰውዬው ከዚያ መኖር ሳይገነዘብ አሁንም ቆም አለ። በፊት እንዳደረገው አሁንም የያዘውን ሳንቲም ወደ ሰማይ አሳነው። ሳንቲሙ ተመልሶ ሲመጣ አምልጦት ከመሬት ወድቆ ዣን ቫልዣ ወደ አረበበት ተንከባለለ። ዣን ቫልዣ ያቺን ነጭ ሽሊንግ በእግሩ ረገጠ ያዘበት። የልጁ ዓይን ሳንቲሙን ተከትሎ ሄዶ ስለነበር ገንዘቡ የት እንደ ገባ አይታል። ልጁ ሳይፈራ በቀጥታ ወደ ሰውዬው ሄዶ «ጌታዬ ገንዘቤን» አለ የዋህነትና ገርነት በተሞላበት አንደበት።

«ስምህ ማነው?» ብሎ ዣን ቫልዣ ሲጠይቀው «ትንሹ ዣራቬ ነው ጌታዬ» በማለት መለሰ።

«ሳላሮልህ፣ ቶሎ ብለህ ከዚህ ጥፋ» አለው ዣን ቫልዣ በቁጣ።

«ሽሊንጌስ?» ብሎ ልጁ ሲጠይቅ ዣን ቫልዣ እንዳቀረቀረ ቀረ። «ገንዘቤን» አለ ልጁ እምባ እየተናነቀው። «ሽሊንጌን!»

ዣን ቫልዣ ምንም ነገር እንዳልሰማ ሰው ፀጥ አለ። ልጁ የሰውዬውን ሽሚዝ ኮሊታ በአንድ እጁ ያዘ። በአንድ እጁ ሳንቲሙን ለማስለቀቅ የሰውዬውን እግር ለማንሳት ሞከረ።

«ገንዘቤን አፈልጋለሁ፣ ሽሊንጌን» ብሎ ከሪኝ በኋላ ትንሹ ዣራቤ ግልቀስ ጀመረ። በዚህ ጊዜ ዣን ቫልዣ አንገቱን ቀና አደረገ። ከተቀመጠበት ግን አልተነሳም። በእሳብ የተዋጠና የተጨነቀ ሰው ለመሆኑ ገጽታው ይናገራል። ልጁን በመገረም አተኩሮ ተመለከተው። ዱላውን ሳብ አድርጎ «አንተ ማነህ? እህ! ምንድነው የምትፈልገው? እስካሁን አልሄድክም እንዴ?» ሲል በሚያስፈራ ድምፅ ጮኸበት። ሳንቲሙን እንደ ረገጠ

ከመቀመጫው ብድግ ብሎ ተነስቶ «ራስህን ብትጠብቅ ይሻልሃል» አለው። ልጁ በፍርሃት ተውጦ በተራው ቀና ብሎ አየው። ሰውነቱ ይንቀጠቀጥ ጀመር። ከጥቂት ሰኮንዶች መርበትበት በኋላ ልጁ 'እግሬ አውጪኝ' ብሎ ሸመጠጠ። ሦር ብሎ ለማየት ወይም ጩኸት ለማሰማት እንኳን አልደፈረም። ሆኖም ጥቂት እንደ ተጓዘ ትንፋሽ አጥሮት ቆም አለ። ግን ብዙ አልቆየም፣ መንገዱን ቀጠለ።

ፀሐይዋ ጠለቀች። ዣን ቫልዣ ከተቀመጠበት አካባቢ ብርሃን ለጪለማ ሥፍራዋን ለቀቀች። ቀኑን በሙሉ እህል የሚባል ነገር አልቀመሰም። ምናልባትም ትኩሳት ብጤ ሳይሞካከረው አልቀረም። ልጁ ከሄደ ጀምሮ ከተቀመጠበት ነቅንቅ አላለም። በኃይል ነው የሚተነፍሰው። ከተቀመጠበት ጥቂት ራቅ ብሎ ከነበረው የሸክላ ስባሪ ገል ላይ ዓይኑን ተከለ። ስለገሉ ይመራመር ጀመር። ሆኖም ግን የሌሊቱ ቁር በድንገት እየተሰማው ስለሄደ መላ ሰውነቱ ተንቀጠቀጠ። ቆቡን ሳብ አድርጎ ግንባሩን ሸፈነ። የሸሚዙን አዝራር ለመቆለፍ ጣቶቹ አዝራር ፍለጋ ላይ ታች አሉ። ብድግ ብሎ አንድ እርምጃ ወደፊት ከተራመደ በኋላ መለሰ ብሎ ዱላውን ለማንሳት ጉንበስ አለ።

በእግሩ ረግጦት የነበረው ሽሊንግ በማብረቅረቁ ዓይኑ ወደዚያ ተሳበ። ኮረንቲ እንደ ያዘው ሰው ተሸማቀቀ። ጥርሱን በማኝጨት «ምንድነው ነገሩ?» ሲል ራሱን ጠየቀ። ወደኋላ መለስ ብሎ ሳንቲሙን በእግሩ በመርገጥ እንደገና ሸፈነው። ሳንቲሙ ዓይን አብቅሎ የሚያየው መስለው። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ እግሩን መነጨቀና ጉንበስ ብሎ ሳንቲሙን አነሳ። ቀና ብሎ አካባቢውን ተመለከተ። ጋራና ሸንተረሩ ሁሉ የሚያየው ስለመሰለው በፍርሃት ተውጦ መጠጊያ እንደምትፈልግ ድኩላ ዓይኑ ከወዲያ ወዲህ ተቅበዘበዘ። ለመነቃነቅ ስላልቻለ ከቆመበት ተገትሮ ቀረ። ወደ ግራና ቀኝ ቢያይ ምንም ነገር የለም። ጊዜው እየጨለመና አየሩ እጅግ እየቀዘቀዘ ሄደ። ሰማዩ በጭጋግ ተሸፈነ።

'ወይ ጣጣ' ካለ በኋላ ልጁ ወደሄደበት አቅጣጫ ተጓዘ። ወደ ሰላሳ ያህል እርምጃ እንደ ተራመደ ቆም ብሎ አካባቢውን ቃኘ። አሁንም ምንም ነገር የለም። ድምፁን ከፍ አድርጎ 'ዣራቬ' ሲል ተጣራ። ከዚያም ድምፁን አጥፍቶ አዳመጠ። እንደገናም ተጣራ፣ መልስ የለም። አገሩ ጭር ያለና ጭጋጋም ቢሆንም አካባቢው በሞላ ጐደል ጉልህ ሆኖ ታየው። ነገር ግን ከዝምታና ከራሱ ጥላ በስተቀር የሚንቀሳቀስ ፍጡር የለም። ዣን ቫልዣ መንገዱን ቀጠለ። የሚወስደውን እርምጃ ፍጥነት በመጨመር እንደ መሮጥ አለ። አልፎ፣ አልፎ ቆም እያለ በሚያስፈራ ድምፅ 'ዣራቬ' እንደ መሮጥ አለ። አልፎ፣ አልፎ ቆም እያለ በሚያስፈራ ድምፅ 'ዣራቬ'

እየለ ይጋገም ተጣራ። እንደ እውነቱ ከሆነ ልጁ ቢሰማው እንኳን በፍርሃት ሰለሚዋተ ይደበቅል እንጂ መልስ አይሰጠውም ነበር። ነገር ግን ወእርግጥም ልጁ ርቆ ሰለሄደ አልሰማውም።

ዣን ቫልዣ ልጁ በሄደበት አቅጣጫ መንዙን ቀጠለ። እየተገላመጠ፣ እየሮኸ፣ እየተጣራ ረጅም መንገድ ሄደ። ግን ማንም አልሰማውም፣ ማንንም አላገኘም። በደረቱ እየተንቆቀቀ የሚሄድ ወይም ድምፁን አጥፍቶ የተደበቀ ሰው ያለ እየመሰለው ከአንዴም ሁለቴ፣ ከሁለቴም ሦስቴ መንገዱን ለቅቆ ወደ ጥሻው ዞር እያለ ሰው ፈለገ፣ በጥሞናም ተመለከተ። ነጅ ግን ሰው የመሰለው ነገር ሁሉ ጠጋ ሲለው ቁጥቋጦ ወይም ድንጋይ ሆኖ አገኘው። በመጨረሻ ሦስት መንታ መንገዶች ከሚገናኙበት ደረሰ። ሰለደህ ከመሃል መንገድ ላይ ተከዘ ቆመ። በዚያን ሰዓት ጨረቃዋ ብቅ ብላለች። ለማየት እስከ ቻለ ድረስ አርቆ ተመለከተ።

'ዠራቪ፣ ትንሹ ዠራቪ፣ ዠራቪ' በማለት ሦስት ጊዜ ድምፁን ከፍ አድርጎ ተጣራ። የገደል ማሚቶ እንኳን ድምፁን ሳያሰማ ጨክቱ ከጭጋጉ ውስጥ ተውጦ ቀረ። 'ትንሹ ዠራቪ' ሲል በደከመ ድምፅ አጉረመረመ። ያ የመጨረሻው ሙከራ ነበር። ይኸኔ በዓይን የማይታይ ኃይል በዱላ እንደ መታው ሰው በድንገት እግሩ ተሳስሮ ጉልበቱ እጥፍጥፍ አለበት። ፀጉሩን ወእጁ ጨብጦና ፊቱን ጉልበቱ ላይ አሳርፎ ከቋጥኝ ድንጋይ ላይ በመቀመጥ 'ምን ዓይነት አድለቢስ ሰው ነኝ' ሲል ጮኸ። ልቡ እያበጠ የሚደ መሰለው። አሁንም እጅግ በጣም አምርሮ አለቀሰ። ከአሥራ ዘጠኝ ዓመት ወዲህ እንደዚያ ሲያለቅስ የመጀመሪያው ነበር።

ዣን ቫልዣ ብዙ አለቀሰ። ከሕፃናት መባበትና ከሴቶች መርበትበት ይበልጥ በፍርሃት ተውጦ ከዓይኑ የደም እምባ የወጣ እስኪመስለው ድረስ አምርሮ በማልቀሰ አንጀቱን አርር፣ ድብን አደረገው። እያለቀሰ ሳለ ከጎሲናው ውስጥ የጸለረው ብርሃን እየፈካ ሄደበት። ያ ብርሃን የተለየ ብርሃን ነበር። ሆኖም ብርሃኑ እጅግ አስፈራው፣ እጅግም አሳደደው። ያስፈው ሕይወቴ፣ በመጀመሪያ የሠራው ወንጀል፣ የረጅም ጊዜ ስቃዩ፣ ጨካኙ ዓለም፣ የደነደነው ልቡ፣ ከአሰር ቤት ማምለጡ፣ የጳጳሱ ቤት ወረራ ላይ ያደረገው የጎሊና ጸጸት፣ የመጨረሻው አሳፋሪ ድርጊቱ ግሰተ ኪሑንን ልጅ ኘንጠባ መዝረፉ ጳጳሱ ይቅርታ ካወረዱለት በኋላ የተረጋመ አሪቃቂና አሳፋሪ ወንጀል ለመሆኑ፣ ሁሉንም ወደ ኋላ ተመልሶ በዓይነ-ህሊናው በጉልህ አያቸው፣ ተመለከታቸው። እነዚያ ሁሉ ገጠመኞች በዓይነ-ፅሥሩው ውስጥ እየተመላለሱ ከዚያ በፊት ታይቶት በማይታወቅ መልኩ ቁልጭ ብለው ታዩት። ያለፈውን የሕይወት ምዕራፉን በአሳብ

በተመለከተው ጊዜ እጅግ አስቀያሚና አስከፊ መሆኑን ሲረዳ ለመሸከም እጅግ ከበደው። ይህ ብቻ አይደለም፣ የነፍሱም መኩነን ቁልጭ ብሎ ስለታየው ይህ እንደሚሆን አልተጠራጠረም። ሆኖም ግን የተሰፋ ጭላንጭል ከነፍሱ ጨርሶ እንዳልተለየ ቢገነዘብም ከዚያ የተሰፋ ጭላንጭል ይመለከተው የነበረው የሰይጣን ጥላ ሆኖ አገኘው። ይህም በመሆኑ አምርሮ ከማልቀስ ሊቆጠብ አልቻለም።

ከለቅሶው በኋላ ምን ሆነ? ዣን ቫልጎርስ ምን አደረገ? ወዴትስ ሄደ? ማንም አላወቀም። ነገር ግን በዚያን አለት ምሽት ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ገደማ በዚያ በኩል ያለፈ ባለጋሪ ከእኛ ደግና ቸር ጳጳስ ቤት በራፍ ከመንገዱ ጠርዝ ፈቀቅ ብሎ ከሚገኝ ዛፍ ጥላ ስር ተንበርክኮ በስሜት ይጸልይ የነበረ ሰው ማየቱን ተናግሯል።

ምዕራፍ ሦስት

አንዳንዴ ኃላፊነትን ከመሸከም ወደ ሌላ አሳልፎ መስጠት

በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ፖሪስ አጠገብ ከሚገኘው ሞንትፌርሜ ከተባለ ሥፍራ አንድ አነስተኛ ሆቴል ቤት ነበር። ይህ ሆቴል ዛሬ የለም። ሆቴል ቤቱ በጊዜው ዘቴናድዬ በመባል የሚታወቁ ባልና ሚስት ንብረት ሲሆን ቡላንገር ከሚባል ቀጭን መንገድ ላይ የተሠራ ሆቴል ነበር። ከሆቴል ቤቱ በራፍ ላይ የተንጠለጠለ አንድ ትልቅ ስእል ነበር። ስእሉ ላይ ሜዳሊያ የተሰካበትና በደም ተበክሎ የተበጫጨቀ የጄኔራል ልብስ የለበሰ ሰው የሆነ ሽክም ተሸክሞ ይታያል። ከስእሉ ባዶ ሥፍራ ላይ ቁስ መሳይ ነገር በብዛት ነበረበት። ከምስሉ ስር 'የዎተርሉ ጦር ሜዳ ጀግናው የሃምሳ አለቃ' የሚል ጽሑፍ ተጽፎበታል። ይህም ጽሑፍ እንደ ሆቴል ቤቱ ስም ይታወቃል። ይህ ስእል በጥቅሉ የሚያመላክተው የጦር ሜዳን ውሎ ሳይሆን አልቀረም።

ከሆቴል ቤቱ በራፍ ጋሪዎች መቆማቸው፣ የተሰባበሩና ደከምከም ያሉ የጋሪ ክፍሎች መንገድ መዘጋታቸው የተለመደ ትርዒት ነበር። ጊዜው የፀደይ ወራት ሲሆን ዓመተ-ምህረቱ 1818 ነው። የጋሪዎችና የተሰባበሩ የጋሪ እቃዎች መንገድ ዘግተው መቆምና የዚያ ለየት ያለ ስእል ከዚያ መነጠልጠል በዚያ መንገድ ያለፈ የማንኛውም ሰው ዓይን መሳባቸው

የሚያስደንቅ ነገር አልነበረም። አንድ ቀን የሆነ ጋሪ ትላልቅ ግንዴላዎችን ጭኖ ከዚያ ቦታ ለተወሰኑ ቀናት መቆሙን ብዙ ሰዎች ተናግረዋል። ታዲያ 'ያ ጋሪ ከዚያ ሥፍራ ምን ይሠራ ነበር?' ተብሎ ቢጠየቅ 'ከዚያ የተገተረውማ መንገድ ለመዝጋትና የትጉህ ሠራተኞችን ሥራ ለማወክ ነው' የሚል መልስ ሊያሰጥ ይችላል። ከዚህ የእቃ መጫኛ ጋሪ ስር የተንጠለጠለው ወፍራም ሰንሰለት መሬት ሊነካ ምንም ያህል እንዳልቀረው የሚታይ ነበር። አንዲት ሁለት ዓመት ተመንፈቅ የሆናት ሴት ልጅ ከእርስዋ በእድሜ የምታንሰውንና አንድ ዓመት ተኩል ገደማ የሞላትን ሌላ ልጅ ከጭንዋ ላይ አሳርፋ ከሰንሰለቱ ላይ ቁጭ ብላለች። ሕፃናቱ ከጅዋጅዌ ላይ የወጡ ያህል ደስ አላቸው። እናታቸውም አቀማመጣቸውን በመደሰት አተኩራ ተመለከተቻቸው።

ላንድ አፍታ በጨረፍታ ላያት እንኳን እጅግ የምትቀፍ፣ አስቸሎት አተኩሮ ለተመለከታት ግን አንጀት የምትበላና ኑሮ ያጎሳቆላት ሌላ ሴት ከሆቴሉ በራፍ ቁጭ ብላለች። ሰንሰለቱ ላይ የተቀመጡት ልጆች ደስ ብሏቸው ሲጫወቱ 'ምናልባት የጋሪው ፈረስ ደምብሮ ይጉዳቸው ይሆን' እያለች እናት አሁንም እንደ ማንኛዋም እናት ማሰብዋና መጨነቅዋ አልቀረም። ያቺን ምስኪን ግን ከመጤፍ የቈጠራት አልነበረም። ሰንሰለቱ በተንቃንቅ ቁጥር ሲጢጥ እያለ የሚያስፈራ ድምፅ ያወጣል። ሆኖም ድምፁ ሕፃናቱን አልረበሻቸውም። የማታ ጀምበር ጨረር ከልጆቹ ግምባር ላይ በማረፉ ልብ ብሎ ለተመለከታቸው አንጀት ይበላሉ። «እሜቴ፣ ደስ የሚሉ ልጆች ነው ያለዎት» የሚል ድምፅ የልጆቹ እናት ትሰማለች።

ከሆቴል ቤቱ በራፍ የተቀመጠችው ሌላዋ ሴትም ልጅ ታቅፋ ነበር። በጀርባዋ ከባድ የሚመስል እቃ አዝላለች። የታቀፈቻት ልጅ ሁለት ወይም ሦስት ዓመት ቢሆናት ነው። በአለባበስ ከሁለቱ ሰንሰለት ላይ ከተቀመጡት ልጆች ብዙም አትለይም። ሻሽ መሳይ ጨርቅ ከፀጉርዋ ላይ አስራለች። የተቦጫጨቀ ቀሚስዋ ቀዳዳ እስከ ጭንዋ ሊደርስ ምንም ያህል አልቀረው። ዝቃታዋ ግን ጤነኛ ለመሆኑ በሩቁ ይታያል። መልክዋ ድምቡሽቡሽ ያለ ሰለሆነ ንክሰኝ፣ እቀፋኝ የምታሰኝ ልጅ ናት። ዓይኖችዋ ትላለቅ ሰለነበሩ እንቅልፍ ቢወስዳትም ሙሉ ለሙሉ አልተሸፈኑም። ለስለስ ካለው የእናትዋ ከንድ ላይ ተመችቷት ስለተኛች እንቅልፍ ሳይጠ ግብ ቢቀሰቅሱት እንደማይለግ ማንኛውም ሕፃን እርሷም ቢቀሰቅሰዋት እንኳን አትሰማም። እናትዬዋ የተከፋች ምስኪንና ሥራ ፍለጋ ወደ ከተማ የመጣች የገጠር ሴት ለመሆንዋ በሁኔታዋ ለማወቅ ይቻላል። ላያት ዐእደሚ ልጅ ናት። ተፈጥሮ ውበት ቢቸራትም፣ 'ሰው ኑሮውን

ይመስላል' እንዲሉ፣ በዚያ ሁናቴዋ ውበትዋ ጉላ ብሎ አልወጣም። ፀጉርዋ ሥማ እንደሆነ ቢያስታውቅም ተንጨባሯል። የተቀዳደደ ሻሽዋ ተፈትቶ ሊወድቅ ብሎ ከወደ ኋላዋ ተንጠልጥሏል። የደላው ሲሰቅ ኑሮ ጥርሱን ያሳያል እንጂ የተከፋ ስለማይሰቅ ስለጥርሶችዋ ለመናገር አይቻልም። ቀደም ሲል ብዙ ለማልቀስዋ ንይኖችዋ ይመሰክራሉ። ሰውነትዋ በመነዛ እንደ ደከማት ለማወቅ አያስቸግርም። አካልዋ ስለገረጣ ምናልባትም ላትታመም አልቀረችም። ጭንዋ ላይ የተኛችዋን ልጅ አተኩራ በፍቅር ዓይን ታያታለች። ልጅዋን ደግፋ የያዘችበት እጅዋ በሥራ ብዛት ለመሸሙ ጉልቶ የሚታይ ነው።

ሩሀሩህ ልብ ያላቸው ሁሉ የማያልፏት ዓይነት ሴት ስለነበረች ገጽታዋን ሲያዩ እጅግ አዘኑላት። ማን ትሁን፣ ከየት ትምጣ አለመታወቁ ግን በመጠኑ ያስገርማል። አፈጣጠርዋ እንደ አረም ስለሆነ አባትዋንና እናትዋን ማንም አያውቅም። እርስዋም ብትሆን የማን ልጅ እንደሆነች አታውቀውም። ስምዋ ፋንቲን ይባላል። ወላጆችዋን ስለማታውቅ የአባት ስም የላትም። የክርስትና ስምም አልወጣላትም፣ ምክንያቱም ባካባቢው ቤተክርስቲያን ማለት ምን እንደሆነ አይታወቅም። ፋንቲን ብሎ ስም ያወጣላት የሆነ በዚያ ያለፈ መንገደኛ ነው ይባላል። ይህ ሰው ሕፃን እያለች መንገድ ወድቃ ዝናብ ሲመታት አይቶ ነው 'ፋንቲን' የሚል ስም ያወጣላት። ፋንቲን ማለት ባገሩ ቋንቋ ውሃ፣ ምንጭ ወይም ፏፏቴ እንደ ማለት ነው። ስለዚህች ሴት ከዚህ ይበልጥ የሚያውቅ ሰው ስለሌለ ስላለፈው ታሪክዋ ከዚህ በተጨማሪ ለመናገር ይከብዳል። ሆኖም «ፋንቲን ለሰቃይ ወደዚች ዓለም የመጣችው በዚህ ዓይነት ነበር» ብሎ ለማጠቃለል ግን ይቻላል። የኋላ ኋላ እንደ ተደረሰበት አስር ዓመት ገደማ ሲሆናት ከከተማ ወጣ ብሎ ወደሚገኝ መንደር ሥራ ፍለጋ ሄዳለች።

በአሰራ አምስት ዓመትዋ አሁንም ሥራ ፍለጋ ወደ ፖሪስ መጥታለች። ወደ ፖሪስ ከመጣች በኋላ በአጋጣሚ ጥርሶችዋ ሲታዩ ከውተት የነጡ ለመሆናቸው ታወቀ። ቢጠፋ፣ ቢጠፋ የእንጨት መፋቂያ አላጣችም ማለት ነው። ምናልባትም ስታገባ የተሰጣት ሳይሆን አይቀርም፣ የሚያምሩ ጌጦች አንገትዋ ላይ አሰራለች። ሥራ አግኝታም ለተወሰነ ጊዜ ከሠራች በኋላ የገዛቻቸው ሊሆኑም ይችላሉ። ሴት ናትና ማጋጌጥዋ አይቀርም።

ለመኖር ሆድ እንጀራ እንደሚርበው ሁሉ ልጅዋን እንደዚያ በሰቀቀንና በጉጉት የምታያት የፍቅር ረሃብዋን ለማርካት ይሆናል። ይህ ስሜት ለሕፃንዋ የእናት ፍቅር ሲሆን ለእናትዋ ግን የስሜት መግንፈል ነበር። እናትና ልጅ ከተቀመጡበት አቅራቢያ የሚያልፉ መንገደኞችና ተማሪዎች ቁጥር እጅግ

ብዙ ቢሆንም ሕፃን ሆና ሕፃን የታቀፈችዋን ሴት አይቶ ያናገራት የለም። ሥሉም ዝም ብለው አለቋት እንጂ ከመጤፍ የቈጠራት አልነበረም። ሕፃንዋ እንደ ተወለደች አባትዋ ሚስቱንና ልጁን ጥሎ ከአገር ኩብልሏል። እባት ቤተሰቡን ጥሎ ከጠፋ በኋላ ለመመለሱ የታወቀ ነገር የለም። ይህም በመሆኑ ሴትዮዋ በብቸኝነት ዓለም ውስጥ እየዋዠቀች ስለነበር ተስፋ ከሚፈጥረው የተሻለ ዓለም ራቀች። በአንድ ወቅት ተሳስታ ከማይሆን ነገር ውስጥ ስለገባች በጸጸት ትሰቃይ እንጂ በአፈጣጠርዋ ገራምና ትምክህት የማይታይባት ሴት ለመሆንዋ ገጽታዋ ይመሰክራል። ሆኖም ከገጽታዋ ላይ የሚነበበው ገራምነትዋ ብቻ አልነበረም። ተስፋ መቁረጥዋ፣ ቀባሪና ጠዋሪ የሌላት መሆንዋና ከባድ ችግር ውስጥ መዘፈቅዋም ይታያል። ነገር ግን ፋንቲን ቆራጥና ጠንካራ ሴት ነበረች።

ፋንቲን ወደ ትውልድ አገርዋ የመመለስ ፍላጎት አደረባት። ከዚያ የምታውቀው ሰው አግኝታ ሥራ ይሰጠኛል ወይም ይፈልግልኛል በሚል ተስፋ ነበር ወደ አገርዋ ለመመለስ የፈለገችው። አገርዋ ሁና የፈጸመችው ስህተት መንገድ ቢዘጋባትም ስሜትዋን ተቆጣጥራ አሳብዋንና ፍላጎትዋን ለመፈጸም ቆረጠች። ስለዚህ በሃያ ሁለት ዓመትዋ ልጅዋን አዝላ ከፖሪስ ከተማ ወጣች። እናት ከልጅዋ በስተቀር ሌላ ሀብት፣ ሕፃንዋም ከእናትዋ ሌላ ምንም ነገር አልነበራቸውም። ፋንቲን በደከመ አቅምዋ ለልጅዋ በማዘን ሲጓዙ ታዝላታለች፣ ሲቀመጡ ታቅፋታለች። እናት በሽታዋ ሲጠ ናባት አልፎ አልፎ ነጭኛ ያስላታል።

ተሰደት ላይ የፀሐይ ቃጠሎን ለማሳለፍ ጥቂት ካረፉ በኋላ ጉዞአቸውን ቀጠሉ። ፀሐይ ቈልቈል ስትል አሁን ከነበሩበት በመድረሳቸውና በጣም ስለደከማቸው ነበር ከሆቴሉ በራፍ ያረፉት። እነዚያ ሁለት ልጆች ከጋሪው ወፍራም ሰንሰለት ላይ ቁጭ ብለው በደስታ ሲጫወቱ በማየትዋ ፋንቲን ከአሳብ ባህር ውስጥ ተዘፈቀች። ሁለቱ ልጆች ፊት ላይ ደስታ ይነበባል። ያም ሥፍራው የተቀደሰና የተባረከ እንደሆነ አሳመናት። ሆቴል ቤቱም በረከት ያልተለየውና መንፈስ ቅዱስ የቀረበው መሆኑን ገመተች።

ሁለቱ ልጆች በአርግጥም ተደሳች ነበሩ። ፋንቲን ልጆቹ ላይ በማፍጠጥ አደነቀቻቸው። ለዚህ ነው «ደስ የሚሉ ልጆች ነው ያለዎት እሜቴ» ለማለት የደፈረችው። የሁለቱ ልጆች እናት ቀና ብላ ካየቻት በኋላ ስለሰጠችው አስተያየት አመሰገነቻት። ልጅ የታቀፈችው ልጅ የተቀመጠችው ከሴትዮዋ ምግብ ቤት በራፍ ስለነበር ሁለቱ ሴቶች ጨዋታ ጀመሩ።

«መዳም ቴናድዬ እባላለሁ» አለች የሁለቱ ልጆች እናት። «ሆቴል ቤቱ የባለቤቴና የእኔ ነው።»

መዳም ቴናድዬ ሽበት ጣል ጣል ያደረባትና እንደ ወታደር ግስት አንገትዋን የደፋች ብትሆንም አተኩረው ሲመለከትዋት ግን ጠባዩ ብልሹ መሆንዋን መገመት አያዳግትም። ሕፃን ልጅ ታቅፋ ኩምሽሽ ብላ ከተቀመጠችው እናት አጠገብ የቆመችውና እንደ ነጋዴ የፈረጠመና ደልዳለ ሰውነት ያላት ሚስስ ቴናድዬ በትኩረት ሲያይዋት ለጓደን ትከብዳለች። ለረጅም ዘመናት ሆቴል ቤት ውስጥ ከገባና ከጠጣ ሰው ጋር መጫጫሀና ከወዲህ ወዲያ መሯሯጥ ይህን የመሰለ ባህርይ ማስታቀፉ አይቀሬ ነው። መዳም ቴናድዬ ወንዱውንድ ብጤ ሆና ሰውነትዋ ደልዳላ ቢሆንና ሽበት ቢወራትም አሰኝዚህም በአድሚ የገፋች ሴት አይደለችም። አድሚዋ በግምት ከሰላሳ ዓመት ብዙም አያልፍም። ምስኪንዋ ሴት 'አሁን እኔና እርስዖ እኮል ቆመን እንሄዳለን' ብላ ሳታስብ አልቀረችም።

አንዱ ቁሞ ብሎ ሌላው ከአጠገብ ቆሞ ቁልቁል እያየ ሲያፈጥ ትንሽ ማስፈራቱ አይቀርም፣ ያውም ግዙፍና ጠንካራ ሰውነት ያለው ሰው ሲሆን። ለማንኛውም መንገደኛዋ ሴት ታሪክዋ ውስጥ ትንሽ ቅመም እየጨመረች አወራታት። ጨዋታዋ ውስጥም በአንድ ወቅት ሥራ እንደ ነበራትና ባልዋ እንደ ሞተ ነገረቻት። በወቅቱ ፖሪስ ውስጥ ሥራ ለማግኘት ስላልቻለች ትውልድ አገርዋ ውስጥ እድልዋን ለመሞከር እንደምትሄድ ገለጸችላት። ልጅዋን አዝላ ከፖሪስ ከተማ የተነሳቸው ጎሕ ሲቀድ መሆኑን፣ በእግር ብዙ በመጓዝዋ ስለደከማት ጥቂት ለማረፍ ከሆቴሉ በረንዳ ጥላ ስር ቁጭ ማለትዋን፣ ድካሙ ሲጠናባት መንገድ ላይ ለአሟር ርቀት ልጅዋ በእግርዋ በመጓዝዋ ሕፃንዋ በጣም እንደ ደከማትና እንደ ተኛች አስረዳቻት።

እናት ይህን እንዳለች የልጅዋን ጉንጭ ምጥጥ አድርጋ በመላምዋ ሕፃንዋ ከእንቅልፍዋ ነቃች። ስትነቃና እነዚያን የሚያማምሩ ዓይኖችዋን ስትገልጥ ምን አየች? ምንም። የሁለት ዓመት ሕፃንስ ምን ያያል! ግን እኮ አንዳንድ ጊዜ ኮስተር፣ አንዳንዴም ቂጣ እያሉ ሕፃናት የማያዩት ነገር የለም ይባላል። ምሥጢሩ የማይታወቀው ያ ዓይን አይደለም እንዴ ገራምነታቸውን የሚያሳየው! ምናልባትም እኮ እነሱ መልአክ፣ እኛ ግን ለዎች እንደሆንን ይታያቸው ይሆናል። እናትዋ ብትቂጣትም ሕፃንዋ መሳቅዋን ቀጠለች። ከመቅጽበትም ከእናትዋ ከንድ ሾልካ ከመሬት ወረደች። ወዲያው ከጋሪ ስር ወደሚጫወቱ ልጆች ሮጣ ሄደች። ምን እንዳለች ሳይታወቅ በመንተባተብ የሆነ ነገር ስትናገር መዳም ቴናድዬ «አብራችሁ ተጫወቱ» ስትል ልጆችዋን አዘዘቻቸው።

በዚያ እድሜ መተዋወቅና መግባባት በጣም ቀላል ነው። የመዳም ቴናድዬ ልጆች አፈር እየፈጩና ጉድጓድ እየቈፈሩ አፈር በመሙላት

ከአዲስዋ ልጅ ጋር ደስ ብሏቸው ይጫወቱ ጀመር። ሕፃንዋም ተግባቢና ተጫዋች ልጅ ነበረች። የእናት ደግነት ከልጅዋ ላይ ይነበባረቃል ይባላል። ስለዚህ እርስዋም ስንጥር መሳይ ነገር ከመሬት አንሰታ ለሞተ ዝንብ መቅበሪያ የሚሆን ጉድጓድ መቆፈር ጀመረች። የመቃብር ቄሩሪን ሥራ ልጆች ሲሠሩት ማየቱ ደስ ይላል። ሁለቱ ሴቶች ጨዋታቸውን ቀጠሉ።

«ልጅሽን ማን ብለሽ ነው የምትጠሪያት?» ብላ ስትጠይቅ «ኮዜት» ስትል መለሰችላት። ቀጥላም «እድሜዋ ስንት ነው?» በማለት ስትጠይቃት «ሦስተኛ ዓመትዋን ይዛለች» አለቻት።

«የትልትዋ ልጂ እኩያ ናት ማለት ነዋ!» አለች መዳም ቴናድዬ።

ሦስቱ ልጆች ደስ ብሉአቸው ሲጫወቱ የሆነ አስደናቂ ነገር ይከሰታል። ኮሚቆፍሩት ጉድጓድ ውስጥ ትልቅ ትል ብቅ ስላለ ልጆቹ በጣም ደነገጡ። በፍርሃት ቀና ሲሉ የሦስቱ ልጆች ግምባር ይጋጫል። ሆኖም ግምባራቸውን ሳያላቅቁ በመገረምና በአጉንቻት ትሉን ተመለከቱ።

«እናንተ ልጆች ምን ሆናችሁ?» ስትል መዳም ቴናድዬ ጠየቀች። ከዚያም ወደ ፋንቲን ዞር ብላ «ልጆች እኮ ለመተዋወቅና አብሮ ለመጫወት ጊዜ አይወስድባቸውም። እያቸው እስቲ! ሦስቱም ከአንድ እናት ማኅፀን የወጡ አይመስሉም» በማለት መዳም ቴናድዬ ተናገረች። የሴትዮዋ አነጋገር በተጠንቀቅ ላይ የነበረውን የሴሳይቱን እናት አሳብ መዘርገፍ ምክንያት ሆነ። ፋንቲን የመዳም ቴናድዬን እጅ አጥብቃ ያዘች።

«ልጂን ያላድጉልኛል?» በማለት ስትጠይቃት «ምን አልሽ?» አለቻት በትክክል መስማትዋን ለማረጋገጥ።

«ልጂን ያላድጉልኛል?» ብላ በድጋሚ ስትጠይቃት «ነገሩን ጥቂት ግብላላት አያስፈልግ ብለሽው!» ስትል መለሰችላት።

«ብወር ስድስት ፍራንክ እከፍሎዎታለሁ» ብላ ስትናገር ከቤት ውስጥ አንድ የሆነ ጉርነን ያለ ድምፅ ተሰማ። «ከሰባት ፍራንክ በታች አይሆንም። የስድስት ወር ሂሣብም በቅድሚያ ነው የሚከፈለው። ስድስት ጊዜ ሰባት አርባ ሁለት ፍራንክ መሆኑ ነው» ሲላት «እከፍላለሁ» አለች እናት።

«አንዳንድ ነገሮችን ለማሟላት በተጨማሪ አሥራ አምስት ፍራንክ ያስፈልጋል» አለ ሰውዬው ቀጠለና። በዚህ ጊዜ መዳም ቴናድዬ ጣልቃ ገብታ «እንግዲህ በድምሩ ሃምሳ ሰባት ፍራንክ መሆኑ ነው» ስትላትም «አዎላለሁ» አለች ምስኪንዋ እናት። «አሁን በእጂ ያለው ሰማንያ ፍራንክ ብቻ ነው። ተረው ገንዘብ እንደ ምንም ብሎ አገሬ ያስገባኛል። ከዚያ ደግሞ ሥራ አላጣም። የሆነ ገንዘብ እንዳፈራሁ ተመልሺ ሙዋቹ ልጂን እወስዳታለሁ» ስትል የዚያ ሰውዬ ድምፅ ዳግም ተሰማ። «ለመሆኑ የሲላት ልብስ አላት?» ብሎ ሲጠይቅ «ባለቤቴ ነው» አለች ሴትዮዋ።

«በሚገባ፣ ደግሞም ለአርስዋ ያልሆንኩ ለማን ልሆን ነው! ባለቤትዎ እንደሆኑ እኔም ጠርጥሬአለሁ። ኤኔው ፈትዬ ያሠራሁላት ወፍራም ልብስ አላት። የሌሊት ብቻ ሳይሆን ከለበሰችው ልብስ ሌላ ቀን ቀን የምትለብሰው ሌላም ሁለት ቀሚስ አላት» ብላ ስትመልስለት «እንግዲያውስ ልብሶችዋን ትተሽ ነው የምትሄጂው» አለ ሰውዬው ጭካኔ በተሞላበት አንደበት።

«ይጣቸውማ አልሄድም» አለች ምስኪንዋ እናት። «ልጂን ራቁትዋን ጥያት ብሄድማ ሰው ጉድ ይላል» ስትል ሰውዬው ኩሰበረበት ወደ ውጭ ወጣ አለ። ከዚያም «ይኼ ጥሩ ነው» አለ እጅግ ዝቅ ባለ ድምፅ። የልጅ ጥሎ መሄድ ስምምነት በዚሁ ተጠናቀቀ። ያን እለት የከዜት እናት ከእዚያው አደረች። ገንዘቡን ከፍላ የልጅዋንም ልብስ ሰጠች። በግራቱ ፋንቲን የቀራትን ጨርቅ ቋጥራና በቶሎ እንደምትመለስ ቃል ገብታ የእግር ጉዞዋን ቀጠለች። ምንም እንኳን በጥሞና የተፈጸመ ስምምነት ቢሆንም የወለደቻትን ልጅ ጥላ ለምትሄድ እናት ግን ቀላል ውሳኔ አልነበረም። አንጀትን ከሁለት የሚከፍል ውሳኔ እንደነበረ ማንም ሊክድ አይችልም።

ፋንቲን ወደ አገርዋ ለመሄድ እንደ ወጣች የእነቴናድዬ ጉረቤት መንገድ ላይ ታያታለች። ሴትዮዋ እነቴናድዬን 'እንዴት አደራችሁ' ለማለት ከቤታቸው ጉራ እንዳለች ወዲያው «ይገርማችኋል፣ ወደቢህ ሰመጣ አንዲት ሴት መንገድ ላይ አየሁኝ። ሴትዮዋን ብታይዋት እጅግ በጣም ታሳዝናለች። ልብዋ ከሁለት የሚከፈልና የሚፈርጥ እስከሚመስል እያለቀሰች ነው ጉዞዋን የቀጠለችው» አለች። የእነቴናድዬ ጉረቤት ከሴታቸው ከመምጣትዋ አስቀድሞ ሰውዬው ባለቤቴን ሲያናግር «ይኼ ገንዘብ እኮ ከሰማይ እንደ ወረደ የሚቆጠር ነው» ይላታል። «ነገ እኮ ለማዘጋጃ ቤት አንድ መቶ አሥር ፍራንክ እንድንከፍል የታዘዘበት የመጪረሻው ቀን ስለሆነ የዚያ ክፍያ ማሚያ ይሆነናል። '50 ፍራንክ ስለጉደለብኝ ዘቦት አባቴ ነው የማመጣው' እያልኩ ስጨነቅ ነበር። በልጆቻችን ስበብ ይህቺን ሴት ደህና አድርገሽ አጠመድሽልኝ» ባሳት ጊዜ «ያውም ምንም ሳይታወቅብኝ» አለች ማዳም ቴናድዬ እየሳቀች።

3

ወጣመድ ውስጥ የገባ አይጥ ማምለጫ አጥቶ ይቅበዘበዛል። በድመት ጥቅር የተያዘ አይጥ ግን ከዚያ ይበልጥ ይቅበዘበዛል፣ ከፋኙም ይጨነቃል። ለመሆኑ እነሚስስና ሚሪ ቴናድዬ ምን ዓይነት ሰዎች ይሆኑ? ምድባቸው እውቀት ኖሯቸው ግን ጊዜ ከጣላቸው ሳይሆን የተናቁ ሆነው ጊዜ ካነሳቸው ሰዎች ውስጥ የሚመደቡ ናቸው። ጊዜ ያነሳቸው ሰዎች ጥፋት ሲፈጽሙ የሠርቶ-አደሩ ትጋት ወይም የቡርዣው ከብር የተጐናጸፉ ባይሆኑም ስህተታቸው ጊዜ ከጣላቸው ላይ ተደፍድፎ እነርሱ ከጥፋቱ ነፃ ይወጣሉ። ይህም በመሆኑ ባልና ሚስት ማለት እኑቴናድዬ መደባቸው ከተናቁ ሰዎች መካከል ቢሆንም ጊዜ ስላነሳቸው ብቻ እንደ ታላላቅ ሰዎች ይከበራሉ።

ማዳም ቴናድዬ ጨካኝና የአረመኔነት ባህሪ የተጠናወታት ሴት ስትሆን ሰውዬው በዋል-ፈሰስና መሳቢስ የሆነ ፍጡር ነው። ሁለቱም ትንሽ ቀዳዳ ካገኙ ተንኰል ከመሥራት ወደ ኋላ አይሉም። እንደ ትል ከብርሃን ወደ ጨለማ፣ እንደ አባያ በሬ ወደፊት ከመራመድ ወደ ኋላ ማፈግፈግ፣ እንደ እባብ ከቀና አስተሳሰብ ተንኰል ወደ መሸረብ፣ ከሰፈው ጠባብ መንገድን የሚመርጡ ዓይነት ሰዎች ናቸው። ሆኖም ተንኰልና ምቀኝነት ለኑሮ መሳካት ዋስትና ሊሆን ስለማይችል ሰዎቹ በሆቴል ቤታቸው ብዙም አልተጠቀሙም። ፋንቲንን ያመሰግኑና ሳያስቡት በድንገት ሃምሳ ሰባት ፍራንክ አገኙ። ይህን ገንዘብ በማግኝታቸው ሆቴል ቤታቸው ከመታሸግ ዳኑ። ነገር ግን አሁንም ቢሆን በሚቀጥለው ወር ተጨማሪ ገንዘብ ያስፈልጋቸው ስለነበር ሴትዮዋ የከዜትን ወፍራም የሌሲት ልብስና ቀሚሶች ወደ ገበያ ወስዳ በስልሳ ፍራንክ ሽጠቻቸው። ያም ገንዘብ ሲያልቅ ኮዜትን ለኑፍሳችን ብለው ያስጠግዋት እንጂ ጥቅም ያገኙበት መሆኑን ረስተው አጅግ በጣም ጨከኑባት። ቦግልዋ የነበሩትን ልብሶች ሸጠው የልጆቻቸውን የተቦጫጨቁ ልብሶች አለበሰዋት። ሰውሽ እንደሚሰዋ አጥንት ከሆቴል ቤቱ በላተኛ የወዳደቀ ትርፍራፊ እንድትበላ አስገደድዋት። ምድብዋ ከሰው ሳይሆን በር ላይ ተኝቶ ዓይን ዓይን ከሚያይ ውሻና ከተመጋቢ አግር ስር ድምፅ እያሰማ ኮሚሄድ ድመት ጋር እኩል ሆነ። ምግብ እንደ ውሻና ድመት ብገበቴ መሳይ ነገር ተደርጎ መሬት ተጣለላት።

እናትዋ አገርዋ ከገባች በኋላ እዚህ ግባ የማይባል ሥራ አገኘች። ሥራዋ ላይ ሆና በየወሩ ለእመሚር ቴናድዬ ደብዳቤ ጻፈችላቸው። በደብዳቤ ዋም ከልጅዋ ደኅንነት በስተቀር ሴላ የምትጠይቀው ነገር አልነበራትም። ባልና ሚስት በመልስ ደብዳቤያቸው ከዚት ተመችቶአት እንደምትኖርና ጤናዋም ይህና እንደሆነ ገልጸው ነበር የጻፉላት።

አንዳንድ ልቦች በአንድ ጉናቸው ጥላቻን ካላቱ ፍቅር መንተራስ የማይሆንላቸው አለ። ሴትዮዋ የራስዋን ልጆች በእጅጉ ነው የምትወደደው። የልጆችዋ ፍቅር ኮዜትን እጅግ አድርጋ እንድትጠላ ገፋፋት። ኮዜት ያለ አግባብ ስትነሳፍ፣ ስትሰደብ፣ ስትመናጨቅ፣ ስትገረፍና ስትጠላ እኩዮችዋ የሆኑት የቴናድዬ ልጆች በፍቅር ሲታቀፉ፣ እሹሩሩ ሲባሉና የማይገባቸውን ምስጋና ሲቸራቸው ኮዜት በማየትዋ ነገሩ ሁሉ ግራ አጋባት እንጂ ሊገባት አልቻለም። የሰው ልጅ ፒኮሳኔ፣ የዚህ ዓለም ውጣ ውረድ፣ የእግዚአብሔር ምህረትና ሽረት ምን እንደሆኑ ለማወቅም እድሜዋ አልፈቀደላትም።


ማዳም ቴናድዬ ኮዜት ላይ በጣም ጨከኑች። ልጆችዋ ኢፖኒንና አዜ ለማም እንዲሁ ጨከኑብት። የሞካኔው መጠን ይለያይ እንጂ በዚያ አድሜ ልጆች ቤተሰቦቻቸው የሚያደርጉትንና የሚፈጽሙትን ነው የሚከተሉት። ፃመት አለፈ፣ ሌላውም ተደገመ። ጊዜ እያለፈ ሲሄድ 'እነግዳም ቴናድዬ ምን ዓይነት ደግና ሩህሩህ ሰዎች ቢሆኑ ነው! እነርሱ ለራሳቸው ምስኪኖች ሆነው ሳለ መጠጊያ የሌላትንና እናትዋ ጥላት የሄደችዋን ልጅ ይረዳሉ፣ ያሳድጋሉ' እያሉ የሰፈር ሰዎች ያወሩ ጀመር። ይህን ያሉት የኮዜት እናት ልጅዋን የረሳቻት ስለመሰላቸው ነው። ከዓመት ዓመት የኮዜት ቀመት እየጨመረ ሲሄድ መከራና ስቃይዋም እንዲሁ እየጨመረ ሄደ።

ኮዜት የሁለቱ ልጆች ጥፋት ማስተባበያ ሆና ቀረች። በቅጡ አምስት ፃመት ሳይሞላት የቤቱ አሽከርና አገልጋይ አደረግዋት። ቤት ትጠርጋለች፣ ግቢ ታጸዳለች፣ እቃ ታጥባለች፣ ከባድ የሆነ ነገር ሳይቀር ትሸከማለች፣ ጉዳያቸውን ሁሉ ለመፈጸም ትላላካለች። የኮዜት እናት ከሦስት ዓመታት በኋላ ሞንትፌርሜ ወደ ተባለ ከተማ ብትመለስና ልጅዋን ብታያት አታውቃትም ነበር ለማለት ይቻላል። ያኔ እናትዋ ጥላት ስትሄድ ድምቤሽቤሽ ያለች፣ 'ግመጡኝ፣ ንከሱኝ፣ እቀፉኝ ታስብል ነበር። ዛሬ ከመጠን በላይ ተጐሳቁላ፣ ጠቁራና መንምና፣ አጥንቶዋ ገጥጠ፣ ፊትዋ ገርጥቶ ሲያይዋት የሚሸሽዋት ዓይነት ልጅ መሰለች። 'እድለቢስ፣ ገጸፋ' እያሉ ነው ባልና ሚስት የሚጠርዋት።

እድልዋ ዝግምተኛ፣ ችግርዋ ፉንጋ እንድትመስል አደረግዋት። ዓይኖችዋ፣ ምንም እንኳን ቢጐደጉዱም ከቦታቸው አልጠፉም። ቢሆንም ሊያይዋቸው አጅግ ያስፈራሉ። ዓይኖችዋ ሰቃይ እንዳንዣበባቸውና በአፈጣጠራቸው ትላልቅ ሰለነበሩ ያዘሉትም የሰቃይ መጠን እንዲሁ ትላልቅ እንደ ነበር በግልጽ ይታያል። ዓይኖችዋ ዘወትር እምባ ያቀርራሉ።

በከረምት ቡትቶ ለብሳ አፈር ላይ ስትተኛና በበጋ በደባደቦ ተሸፋፍና በጠራራ ፀሐይ ከቁመትዋ የሚበልጥ መጥረጊያ ይዛ ደጃፍ ስትጠርግ ማየት

ልብ ላለው የሚዘገንን ትርኢት ነበር። ሆኖም ሰዎች 'እያለቢሰና ገላ
እያሉ ይጠርዋታል። ጠዋት ጠዋት ገና በቅጡ ሳይነጋ መንፈሰዋ እየፈራ
እየተባ፣ መላ ሰውነትዋ እየተንቀጠቀጠ ነበር ከመኝታዋ የምትነሳው
ከነፈር የምታመጣው ነገር ካለ ጉረቤቶች ሳይነሱ ትሂድና አስከሚነሱ
ትጠብቃለች። ወደ ዝያ ሄዳ የምትገዛውም እቃ ካለ ዝያ ተኛች እቃቸውን
ሳያወጡ እርስዋ ቀድማ ትገኛለች።



ምዕራፍ አራት

ደጉ ሰው

የዚያች ምስኪን ልጅ እናት ምን ሆነች? ሞንትፈርሜ ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች 'ልጅዋን ከድታ የትም ጥላት ጠፉች' እያሉ ሲናገሩ ሰምተናል። ለመሆኑ የት ነው ያለችው? ምን እየሠራች ነው? ፋንቲን ልጅዋን ከነቴናድዬ ቤት ትታ ከሄደች በኋላ ከትውልድ አገርዋ በደህና ደርሳለች። ከእሁን በፊት እንደ ተነገረው ይህ ታሪክ የሆነበት ዘመን 1818 ዓ.ም. ሲሆን ሴትዮዋ ወደ ትውልድ አገርዋ የተመለሰችው አገሩን ለቅቃ በወጣች በአሰራ ሁለተኛው ዓመት ነው። ስትመለስ አገሩ ብዙ ተለዋውጠ ነው ያገኘችው። የእርስዋ ኑሮና ሕይወት እያሽቄለቄለ ሲሄድ የትውልድ አገርዋ ከተማ እጅግ እያደገና እየተሻሻለ መሄዱን ነው የተገነዘበችው። በተለይ በመጨረሻዎቹ ሁለት ዓመታት ከተማው ትልቅ መሻሻል ነበር ያሳየው። ፋብሪካ ተመርተው የሚወጡ እቃዎቹ ዋጋ ቢንርም ቁጥራቸው በርከት ያለ መለስተኛ ፋብሪካዎች ተቋቋመው ነው ያገኘችው።

አንድ ከየት እንደ መጣ የማይታወቅ ሩህሩህና ለአካባቢው ሕዝብ ብዙ የሚጨነቅ ሰው በ1815 ዓ.ም. መጨረሻ ገደማ መጥቶ አሰደናቂ የሆነ የፈጠራ ሥራ በመሥራቱ ንሮ የነበረውን የእቃዎች ዋጋ ዝቅ እንዲል አደረገ። ሰውዬው ሦስት ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ አገር ያወቀው ሀብታም ሆነ። ከእርሱ ፋብሪካ ውስጥ ይሠሩ የነበሩ ሰዎች ደግሞ ጥሩ ደመወዝ ስለሚከፈላቸው እነርሱም ጥሩ ኑሮ ለመኖር ቻሉ። ይህ ሰው ከዚያች ከተማ ሲገባ ከየት እንደ መጣ አይታወቅ እንጂ ምንም ገንዘብ ይዞ እንዳልጣ ሁሉም ያውቀዋል። ቢሆንም እርሱ በወጠነውና ባፈለቀው የፈጠራ አሳብ እርሱ ብቻ ሳይሆን አገሩ ሁሉ ከዘረበት። ይህ ሰው ከከተማው ሲገባ አልባበሱም ሆነ አነጋገሩ የሚቁን እንደ ነበር ማንም የሚናገረው ነው።

በታህሳስ ወር ለንይን ያዝ ሲያደርግ ከከተማው ሲያርስ የለበሰው ልብስ የተቦጫጨቀ፣ እግሩና እጁ በሥራ ብዛት የሻከረ ሲሆን በእንድ እጁ ምርኩዝ መሰይ ነገር፣ በሌላኛው እጁ በጨርቅ የተጠቀለለ እቃ ይዞ ነበር። በእለቱ እርሱ ከከተማው ሲገባ ባንድ አነስተኛ የእሳት ቃጠሎ ተነሰቶ ስለነበር በቀጥታ ቃጠሎው ወደ ተነሳበት ሰፈር ይሄዳል። ልክ እርሱ ሲደርስ ሁለት ትንንሽ ልጆች በእሳቱ ወላፈን ተከብበው ያያል። ይኼኔ በድፍረት እሳቱ ውስጥ በመግባት ልጆቹን ያወጣል። እንዳጋጣሚ ሆኖ ልጆቹ የባለሥልጣን ልጆች ነበሩ። በዚያ ግርግር የከተማው ሹሞች የመታወቂያ ወረቀት ሳይጠይቁት ከሕዝብ መካከል ገብቶ ተቀሳቀሰ። ስለፈጸመው በጎ ተግባር ሰው ሁሉ አመሰገነው። በዚህም ሰው ሁሉ 'አባባ ደጉ ማንደላይን' እያለ ጠራው። እድሜው በግምት ሃምሳ ዓመት ይሆናል። አሳብ ስለሚያጠቃው ዘወትር ትክዝ ከማለቱ በስተቀር ስለዚህ ሰው በጊዜው ከዚህ ይበልጥ ማውራት አይቻልም።

ብቻ እርሱ በፈጠረው ጥበብ ሳቢያ በገፍ ለሚመረቱ እቃዎች ምስጋና ይግባውና የብዙ ሰው ሕይወት ተሻሻለ። ከተማዋም የነጋዴዎች መናኸሪያ ሆነች። እቃዎቹ ከአገር ውጪ ወደ አሰፓኝ እየተላኩ ብዙ ጥቅም አሰገኙ። የእቃዎቹ ጥራት እንግሊዝና ጀርመን አገር ከሚመረቱትና ተመሳሳይነት ካላቸው እቃዎች የተሻሉ ሁነው በመገኘታቸው ተወዳጅነት አተረፉ። ስለዚህ ገበያው ደራ፣ የሚገኘውም ጥቅም ከፍ አለ። በሁለተኛው ዓመት አባባ ማንደላይን ሌላ ዘመናዊ የሆነ ፋብሪካ ከፈተ። ከፋብሪካው አንደኛው ክፍል ሴቶች ብቻ ተሰማሩበት። ከእዘያ ከተማ ውስጥ ሥራ ያጣ ሁሉ ሥራ አገኘ።

አባባ ማንደላይን ከመምጣቱ በፊት ብዙ ሰው ሥራ ስላልነበረው ከተማይቱ ውስጥ ብዙም እንቅስቃሴ አይታይም ነበር። አሁን ግን ሁሉም በየፊናው የሚፍጨረጨርበት መንገድ ስለተከፈተለት ከተማው ሞቅ ብሎ ሁሉም ነገር ተንቀሳቀሰ። የኢኮኖሚው መንቀሳቀስም የተፈለገው ነገር ሁሉ በየሥፍራው እንዲገኝ ረዳ። ሥራ መፍታትና ችግር ከከተማው ተወገደ። አብዛኛው ነዋሪ መጠነኛ የሆነ ገቢ ስላገኘም ሁሉም እንዳቅሙ በደረጃው ደስ ብሎት መኖር ቻለ። አባባ ማንደላይን ለሁሉም ሰው ሥራ ከማስገኘቱም አልፎ ሠራተኛ ሁሉ 'ታማኝና አውነተኛ ሰው ሆኖ ሕይወቱን እንዲመራ' አስጠነቀቀ።

ተደጋግሞ እንደ ተጻፈው በዚህ አጋጣሚ የአባባ ማንደላይንም ሀብት የተትረፈረፈ ሆነ። የሚገርመው ግን ይህ ሰው ለሀብትና ለግል ምቾት ይህን ያህል ደንታም አልነበረው። ከሀብቱ ይልቅ ስለሌሎች ሰዎች ደኅንነት እጅግ ያስባል፣ ይጨነቃል። ስለራሱ ደኅንነትና ምቾት ሲል የሚያጠፋው

ወደ ስድስት መቶ ስልሳ ሺህ ፍራንክ ሲሆን በዚያው ዓመት ለከተማው እድገትና ለተቸገሩ ድሆች መርጃ ያወጣው ገንዘብ ደግሞ ወደ አንዩ ሚሊዮን ፍራንክ የሚጠጋ ነበር::

ከተማው ውስጥ የነበረው ሆስፒታል የተሟላ ክፍልና አልጋ ስላልነበረው ለሕመማን ምሚሆን አሥር ተጨማሪ አልጋዎች እንዲገዙ እጁን ዘረጋ:: ከተማው የሳይንሳውና የታችኛው ተብሎ ከሁለት የተከፈለ ሲሆን እርሱ ይናርበት የነበረው የታችኛው ክፍል ብዙ የጉደለው ነገር ነበር:: በዚያ አካባቢ የነበረው ትምህርት ቤት አንድ ብቻ ሲሆን እርሱም ቢሆን ለመፈራረስ አንድ ሰንበት የቀረው ነበር:: ስለዚህ አባባ ማንደላይን የግሉን ገንዘብ ወጪ አድርጎ ሁለት አዳዲስ ትምህርት ቤቶችን አሠርቶ አንደኛው ትምህርት ቤት ሴቶች፣ ሌላውን ወንዶች እንዲማሩበት አደረገ:: አራት ተጨማሪ መምህራንም ቀጥሮ መንግሥት ከሚከፍለው ደመወዝ እጥፍ አደረጋላቸው:: ይህን ያየ ጐረቤቱ አባባ ማንደላይን የሠራውን ሥራ በማድነቅ «ነርስና አስተማሪ እኮ ምርጥ የአገር ገንቢዎች ናቸው» አለ ይባላል:: በአካባቢው ሚሪና ደጋፊ ለሌላቸው ሰዎች ማደሪያ እንዲሆን ትልቅ ቤትም አሠርቷል:: ቀደም ሲል ያቋቋመው ፋብሪካ መሃል ከተማ ውስጥ ስለነበር ከፋብሪካው በሚወጣ ጭስ ምክንያት የሚጐዱ ሰዎችን ለመታደግ አስቦ ተጐጂዎች መድኃኒት በነፃ ለመውሰድ እንዲችሉ በዚያው አካባቢ የመድኃኒት ቤት ከፈተላቸው::

ይህ ሰው በ1817 ዓ.ም. የሠራው በጎ ተግባር በመላ ፈረንሳይ ስለተሰማ በጊዜው የነበረው ንጉሥ አባባ ማንደላይንን የከተማው ከንቲባ አድርጎ ሊሾመው ነው ተብሎ ተወራ:: የተወራው ወሬ አሉባልታ ሆኖ አልቀረም:: ከጥቂት ቀናት በኋላ የአባባ ማንደላይን መሾም በጋዜጣ ታትሞ ወጣ:: አባባ ማንደላይን ግን ሹመቱን የማይቀበለው መሆኑን አስታወቀ::

ደጉ ሰው ከከተማው በገባ በአምስተኛው ዓመት ማለት በ1820 ዓ.ም. ለሕዝብ ቀቅም ብሎ ያሠራው ነገር እጅግ በጣም የገዘፈ በመሆኑ ንጉሡ እንደሻ ሲሾሙት አሁንም 'ሹመቱን አልቀበልም' አለ:: ግን የከተማው ፖሊስ አዛዥ «ሹመቱን ተቀብሎ የንጉሡን ትእዛዝ ማክበር አለበት» ሲል አቀባቀቀ ተናገረ:: ከተማው ውስጥ የሚኖሩ ታላላቅ ሰዎችና መኳንንትም ከቪቴ ድረስ እየመጡ ሹመቱን እንዲቀበል ተማጠኑት:: የወዝ አደሮችም አባባ ከዚህ የተለየ አልነበረም:: ስለዚህ ሰዉ ሁሉ ሹመቱን እንዲቀበል ሰለወተወተው ሹመቱን ተቀብሎ የከተማው ከንቲባ ሆነ:: ሰዉ ሁሉ ሹመቱን እንዲቀበል የገፋፋው አንዲት የኑሮ ደረጃዋ ዝቅተኛ የሆነ አሮጊት ከፈረር ሰፈር እየሠረች 'ጥሩ ከንቲባ ማግኘት እኮ ጥሩ ነገር

ነው፣ መልካም ሥራ የሚሠራ ሰው አይወድላችሁም፣ እያለች ሕዝቡን በመቀስቀሷ ነው ይባላል::

የሕዝቡ ቁጥር አነስተኛ በሆነበት ከተማ ማንኛውም ወሬ ስለማይደበትና ያቺ ሴት ያለችው ነገር በአጭር ጊዜ ከተማው ውስጥ ስለተሰራጨ ነበር ሕዝቡ ደጉን ሰውዬ የደገፈው:: ቢሆንም ቀን እየገፋ ሲሄድ፣ ምንም እንኳን ቁጥሩ አነስተኛ ቢሆንም ተቃዋሚ አልጠፋም:: ይህ መቼም የሕይወት እውነታ ነው:: በራሳቸው ጥረትና ችሎታም ሆነ በሌሎች ድጋፍ ሥልጣን የጨበጡ ሰዎች ተቃዋሚ አያጡም:: መሴይ ማንደላይንም ከዚህ ሊርቅ አልቻለም:: ነገር ግን ተቃውሞያቸው ብዙም አልቆየም:: በተሰይም ደጉ ሰው ሹመቱን ከተቀበለ በኋላ በሕዝቡ ዘንድ የነበረው አድናቆትና ክብሬታ ጨመረ እንጂ አልቀነሰም:: ለምን ቢሉ፣ ሰውዬው የተጣላን ያስታርቃል፣ የታመመን ይጠይቃል፣ ከዚህ ዓለም በሞት የተለየን ይቀብራል፣ ሰው በተራው ዳኛ አድርጎ ሾመው:: የዓለም ሕግ ልቡ ላይ የተጻፈ ይመስል የሚበይነው ፍርድ የተመሳገደ፣ የማያጠው ምክር የተጣመመ አልነበረም:: ነገሩ ሁሉ ፊት ለፊት እንጂ ወደ ኋላ አያውቅም:: በዚህም የተነሣ ከሰድስትና ከሰባት ዓመታት በኋላ ስሙ በሚኖርበት ክፍለ ሀገር ብቻ ሳይሆን በመላ ፈረንሳይ እጅግ ገነነ:: ነገር ግን አንድ ሰው ብቻ ሊሰቀው ስላልቻለ መሴይ ማንደላይን የሚሠራውንና የሚያደርገውን ሁሉ አጥብቆ ይከታተላል:: መከታተል ብቻ ሳይሆን ክፉኛ ይጠምደዋል:: ዘወትርም በቀና መንፈስ ስለማያየው ሁሌም ይጠራጠረዋል:: ስሜቱም ብቻ ሳይሆን መላ አካሉ ማንደላይንን ይጠላል::

መሴይ ማንደላይን መንገድ ላይ ባለፈ ቁጥር ሰው ሁሉ በፍቅር ዓይን ሲያየው ያ ቀጠን ብሎ ከቁመቱ ዘለግ ያለውና የወታደር ልብስ የሚለብሰው ሰው ግን በዓይነ-ቁራኛ ይጠብቀዋል:: ከዓይኑ እስከ ተሰወረ ድረስ አተኩሮ ከመመለከትና መሴይ ማንደላይንን ከማጤን አይቆጠብም:: ግምባሩን እየጸጠረ 'ይህ ሰው ማነው? በእርግጥም ኩነን ቀደም አይቼዋለሁ:: ታዲያ የት ነው የማውቀው? ሰው ሁሉ ያደንቀዋል፣ ይወደዋል:: እኔ ግን እጠራጠረዋለሁ፣ ወንጀለኛም ይመስለኛል' ብሎ የሚናገር ይመስል ካጠገቡ ሰው ሳይኖር ከንፈሩን ያኝቃንቃል:: ደጉን ሰው ባየ ቁጥር ከአሳቡ ጋር ግብግብ ለመግጠሙና ለመጋፋቱ ያስታውቅበታል:: ሰውዬው መከሳተርን የመሰለ ዓይነት ሰው ስለነበር እንኳን በዓይኑ-ቀራኛ እያየ ሲከተል ቀርቶ ለአንድ አፍታ ሲያይ እንኳን 'ይህ ሰው ከእኔ ነገር አለው?' የሚያሰኝ ዓይነት ፊትና አመለካከት ያለው ነው:: ስለዚህ ሳይወዱ በግድ ሞንቀትን ከልብ ውስጥ በማሳደር የጎሊና መረበሽን አንሳል ውስጥ ይቀብራል:: ሰውዬው ፖሊስ ሲሆን ስሙ ዣቬር ይባላል:: ተራ ፖሊስ

ላይሆን የከተማው ፖሊስ አዛዥም ነው። መሴይ ማንደላይን ወደዚያች ከተማ ሊመጣ ዣቬር ከዚያ አልነበረም። አንዳንድ የፖሊስ መኰንኖች የተለየ መልክ አላቸው፣ አንዳንዶቹም ከአልቅናቸው ጋር የተቈራኘ ክፋት እንዳላቸው ገጽታቸው ላይ ይታያል ይባላል። ዣቬር ይህ ዓይነቱ ገጽታ ቢኖረውም የዚያን ዓይነት ክፋት ነበረው ለማለት ግን ያስቸግራል።

ዣቬር ከእስር ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ነው የተወለደው። እናቱ ጠንቋይ ሲሆኑ አባቱ የወህኒ ቤት ሠራተኛ ነበሩ። አባቱ የአካባቢው ህብረተሰብ ቤተሰባቸውን ከማኅበራዊ ሕይወት ያገልላል የሚል እምነት ሰለአዘሯቸው ያ እምነታቸው ዣቬር ላይ ተሰፋ የመቁረጥ ስሜት አሳድሮአል። ዣቬር የአውን ልጅ ከዜሉት ኰሉ አንደኛው ወገን ህብረተሰብን የሚያጠቃ ሲሆን ሌላው ወገን ከዚያ ጥቃት የሚከላከል ነው ብሎ ያምናል። ይህ ሰው በቅንነትና በሥነሥርዓት መጠበቅም በጽኑ ያምናል። ሆኖም ጎሳን ተንተርሶ ሰውን መፈረጅ ይጠላል። ዣቬር ፈልንና አምኖበት ነው የፖሊስ ኃይል አባል የሆነው። በሥራውም የተመሰገነ ፖሊስ ስለአዘር በአርባ ዓመቱ ለአሥተኛ ግዕረግ ታጭቶ የፖሊስ አዛዥ ሆኗል። በወጣትነት ዘመኑ ደቡብ ኦርሊዓንዝ ኮሚገኝ ወህኒ ቤት ውስጥ አንዲሠራ ይመደባል።

አፍንጫው እንደ አጠና ቀጥ ያለ ነው። ከግራ ተቀኝ ያለው ሪዙን በጣም ስላሳደገው ጉንጮቹን ሸፍኖበታል። ድንገት የሳቀ እንደሆነ ስስ ከንፈሮቹ ተገልጠው የሚያሳዩት ጥርሶቹን ብቻ ሳይሆን ድዶቹንም ጭምር ነው። ደግነቱ ዘወትር መኰሳተርን እንጂ ሳቅ የሚሉትን ነገር አያውቅም። ከአፍንጫው ግራና ቀኝ የሚገኘው ሰውነቱ በብዛት የተሸበሸበ ስለሆነ ሲቆጣ ነዛርን፣ ሲሰቀ ደግሞ የአደን ውሻን ያስመስለዋል። ከዚህ በተረፈ ጭንቅላቱ ትንሽ፣ አገጩ ሰፊ ሲሆን ፀጉሩን ወደፊት ስለሚያበጥረው ከግምባሩ እስከ ቅንድቡ ያለው ሰውነቱ በፀጉር የተሸፈነ ነው። ፊቱ የሚያርበደብድና የኰሰታራዎች ሁሉ አሰቃ ስለሚመስልም በጥቅሉ 'ዣቬር ባለጨገን ፊት' ነው ለማለትያስል ይቻላል።

ይህ ሰው በዜሉት ዓይነት አመለካከት ሰውነቱን የወጠረ ሰው ነው። በመወረቱ ሁሉንም አመለካከቶች ከስህተት የወጡ ቀላል አመለካከቶች ሲሆኑ ዣቬር ግን እጅግ በጣም ስላጋንናቸው እንደ ከባድ ነገር ነበር የሚያያቸው። አመለካከቶቹ ባለሥልጣንን ማክበርና ሕግ የሚተላለፉትን ግለያድና መቅጣት ናቸው። በዣቬር ዓዕዳ ሊብነት፣ ሰው መሣደልና የመሰሰሉት ወንጀሎችን መፈጸም ሕ.ሥ ለንደ ሰማረር አድርጎ ነው የሚቈተረቸው። በሁሉም መሰል የተሰማሩ የመንግሥት ሠራተኞች ማለት ከአገር መሪ እስከ ተራ ሠራተኛ ድረስ ያሉት ሁሉ የእርሱን አመለካከት

መቀበል እንዳለባቸው ያምናል። ሕግ የሚጥሱትን ከፋኖ ስለሚጠላ እነርሱን ተከታትሎ ማጥፋትና መስመር ማስያዝ ተገቢ እርምጃ እንደሆነ ሲደነገ ሕግ ማስከበርና ሥርዓት ማስያዝ ለእርሱ ትልቅ ቁም ነገሮች ናቸው።

«የመንግሥት ባለሥልጣንን ማታለል አይቻልም። ሕግ አስከባሪ ዳኛም ስህተት አይሠራም። ደግሞም ማምለጫ ቀዳዳ ከሌለው ስህተት ውስጥ ከተዘፈቁ ነፉ ሰዎች በጎ ተግባር አይጠበቅም» ይላል ዣቬር። 'ሰው የሠራው ሕግ መጣስ የለበትም' ብለው የሚያምኑ ወግ አጥባቂዎችን በፍቅር ያከብራል። እንደ ጦር የሚወጋው ዓይኑ ሰው ላይ እንዲተከል የሚገፋፋው ያ እምነቱ ነበር። ይህም በመሆኑ 'ኑቱ መጠበቅ' በሚል ፍልስፍና ዘወትር ሕይወቱን ያንፃል። ጎሊናው ሕግን በማስከበርና የእለት ተለት ተግባርን በጽኑ መከታተል ላይ ያተኰረ ሲሆን ቁሶች ለትጻሲ እንደሚተጉ ሁሉ እርሱም ለስለላ ተዋር ይተጋል። ይብላኝለት እርሱ መጻፍ ውስጥ ለሚወድቅ። የገዛ አባቱን እንኳን ከእስር ቤት ሲያመልጥ ቢያየው ሮጦ ሂዶ ያሲዘዋል። አንድ ጊዜ እናቱ ቲኪት ስታጭበረብር ሰላያት ለአለቆች አሳልፎ ሰጥቷታል።

ዣቬር ይህን የመሰለ ሥራ በሚሠራበት ጊዜ ታላቅ ጀብዱ እንደ ሠራ ሰው መንፈሱ ይረካል። ሕይወቱ በብቸኝነትና በግላዊነት የተሞላ ሲሆን ከዓለማዊ ምቾት የራቀ ነው። የእርሱ ደስታ ወንጀለኞችን ተከታትሎ ማደን እንጂ ዳንኬራ መርገጥና ሙዚቃ መስማት ብዙም አያስደስተውም። ዣቬር ማለት ይህ ሲሆን መሴይ ማንደላይንን ከመጠን በላይ ስለሚጠራጠረው ዓይኑን ከእርሱ አያነሳም። ሆኖም በነውጪው ላይ የተጨበጠ ማስረጃ ሊያገኝ አልቻለም። ይህ ሰው እንደሚከታተለውና በከፉ ዓይን እንደሚያየው መሴይ ማንደላይን ያውቃል። ነገር ግን ከምንም አልቆጠረውም። ዣቬርን ብዙም አልቀረበውም፣ ብዙም አልሸሸውም። በየጊዜው ሊያፈጥበት እሞ እንዳላየ ሆኖ አለፈው እንጂ ዣቬር ምን እንደሚፈልግ ለማወቅ ዋያቄ አልጠየቀም። እንዲያውም ከነአካቴው ሌሎችን በሚያደበት ዓይን አያየና ደግነት በተሞላበት አንደበት አያነጋገረ አረጋጋው። የመሴይ ማንደላይን ሁናቴ ዣቬርን ግራ ያጋባዋል። ሆኖም በአንድ አጋጣሚ የዣቬር ሁኔታ መሴይ ማንደላይንን እጅግ ያስቄጣል። ጉዳዩ እንዲህ ነበር።

አንድ ቀን መሴይ ማንደላይን ከአንዲት መንደር ውስጥ ከወዲያ ወዲህ እያለ ሲንሸራሸር ፈጅኽት ይሰማል። ፊቱን ሲያዞር ሰዎች ተሰብስበው ሲያይ ወደዚያ ይሄዳል። ቀረብ ሲል ደብተራ ፎሽለማ የሚባሉ ሽማግሌ እቃ የሚነ ጋሪ ተጭኖአቸውና ከመሬት ወድቀው ይመለከታል። የጋሪውም ፈረስ ወድቆ እግሩ ስለተሰበረና ጋሪው ከአነጂቀው ስለተጫነው እርሱም